አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 35889 | ቅዳሜ ነሐሴ 30 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር

## የጳጉሜን ቀናት

ጳጉሜን 1 የእመርታ ቀን | ጳጉሜን 2 የማንሠራራት ቀን | ጳጉሜን 3 የጽናት ቀን | ጳጉሜን 4 የኀብር ቀን | ጳጉሜ የነገ ቀን

# እውቅና የተቸረው የትውልድ ግንባታ

- የነገን ትውልድ ታሳቢ ያደረገውን የአዲስ አበባ “የቀዳማይ ልጅነት እንክብካቤ ፕሮጀክት” የተለያዩ ሀገራት በተሞክሮነት እየወሰዱት መሆኑም ተጠቁሟል

6




ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዓለም አቀፉ Act For Early Years ኢኒሼቲቭ “የቅድመ ልጅነት እድገት ሻምፒዮን” ተብለው እውቅና ተሰጥቷቸዋል

## መዲናዋን አዲስ መልክ ያላበሱ የልማት ስራዎች

7



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ አበባን ገፅታ ከቀየሩ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት በከፊል

## ጳጉሜን እና የቱሪዝም ዕድሎች

20




ግራፊክስ - በእዮብ ተፈራ

የ13 ወር ፀጋ ባለቤትነት የሚፈጥረውን መልካም አጋጣሚ የቱሪስት መስህቦችን ለማስተዋወቅ መጠቀም ይገባል

## ከጥበብ ጓዳ የሚቀዳ በጎነት

11



ፎቶ፦ ኤ አይ ቻት ጂፒቲ

ኪነ ጥበብ አስተዋፅኦ ባደረጉባቸው የበጎ አድራጎት ስራዎች ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል

# የኢትዮጵያ ማንሰራራት እርካቦች

- ኢትዮጵያ በኃይል፣ በግብርና፣ በሎጂስቲክስና በመሠረተ ልማት ዘርፎች ያከናወነቻቸው ፕሮጀክቶች ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ማንሰራራትና እድገትን እውን እያደረጉ መሆናቸውን ተጠቁሟል

በቶለሳ መብራቴ

ታዋቂው የልማት ፖሊሲ እና ኢኮኖሚክስ ምሁር ደቡብ ኮሪያዊው ሃጁን ቻንግ (ዶ/ር)፣ የሀገራት ፈጣን የኢኮኖሚ ማንሰራራት እና ዘላቂ እድገት የሚረጋገጠው በመንግስት ስትራቴጂካዊ አመራርና አቅጣጫ ሰጪነት በሚከናወኑ መዋቅራዊ የትራንስፎርሜሽን ስራዎች እንደሆነ ያስረዳሉ።

እንደ ደቡብ ኮሪያ ያሉ ሀገራትን ተሞክሮ በማጣቀስ ቻንግ እንደሚያስረዱት፣ አስተማማኝ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ በተለይም አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት እና ዘመናዊ የሎጂስቲክስ አውታር



ፎቶ ከገፀ ድር

የከተማዋ የመንግስት ሰራተኞች የኢትዮ ኮደርስ ስልጠና በመውሰድ ላይ ይገኛሉ

# ጥረት የለወጠው ህይወት

- በአዲስ አበባ ከተማ በሴፍቲኔት መርሃ ግብር 730 ሺህ 57 ዜጎችን በተለያዩ ምዕራፎች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል

በሽዋርካብሽ ቦጋለ

በከተማዋ በተዘረጋው የሴፍቲኔት መርሃ ግብር ተጠቃሚ ከሆኑ እናቶች መካከል በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ዙልፋ መሃመድ አንዷ ናቸው። ወደ ፕሮግራሙ ከመቀላቀላቸው በፊት የነበራቸው የኑሮ ሁኔታ እጅግ ከባድ ነበር፤ ከአንድ ልጃቸው ጋር የዕለት ጉርሳቸውን ለመሸፈን የማይፈነቅሉት ድንጋይ አልነበረም። የነገ ተስፋቸውን ለማለምለም የተለያዩ የጉልበት ሥራዎችን ከመሥራት አልፈው፣ ከሰው ተበድረው በቤታቸው ፈሳሽ ሳሙና (ላርጎ) አምርተው መሸጥ ቢጀምሩም፣ ያገኙት ገቢ የተበደሩትን ለመመለስ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል




አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## አዲስ አበባ ነገን ዛሬ እየሠራች ነው!

የአንድ ሀገር እውነተኛ ሀብት የሚለካው በተፈጥሮ ጸጋ ብቻ ሳይሆን፣ በምታፈራቸው ብቁ፣ ጤናማ፣ በፈጣራ የተካኑና አምራች ዜጎች ጭምር ነው። የዚህ መሠረት የሚጣለው ከዛሬ ብዙ ዓመታት በኋላ ሳይሆን፣ ልጅ በእናቱ ማኅፀን ከሚገኝበት ጊዜ ጀምሮ ነው። የዓለም ጤና ድርጅትም ከእርግዝና እስከ ሦስት ዓመት ያለው ወቅት የአዕምሮ እድገት በእጅጉ ፈጣን የሆነበት ወሳኝ የሕይወት ወቅት መሆኑን፣ የሕፃን አዕምሮ እድገትም 80 በመቶ ያህል እንደሚፈጠር ያስረዳል። ስለዚህ ለሕፃናት ጤና፣ ምግብ፣ ፍቅር፣ ደህንነት፣ ጨዋታና ትምህርት ዛሬ የምንሰጠው ትኩረት ለነገ የምንገነባው የሰው ሀብት መሰረት ነው።

ይህን እውነታ የተረዱ ሀገራት በቀዳማይ ልጅነት ላይ ያፈሰሱትን መዋዕለ ንዋይ እንደ ወጪ ሳይሆን እንደ የወደፊት ሀብት ይቆጥሩታል። የኖቤል ተሸላሚው የምጣኔ ሀብት ምሁር ጄምስ ሂክማን የመሩት ጥናት ጥራት ያለው የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም በአንድ ልጅ ላይ የሚደረግን መዋዕለ ንዋይ በረዥም ጊዜ እስከ 13 በመቶ ዓመታዊ ተመላሽ ሊያስገኝ እንደሚችል ያሳያል። ይህ ትርፍ በገንዘብ ብቻ የሚለካ አይደለም፤ በተሻለ ትምህርት፣ በጤና፣ በሥራ ዕድል፣ በምርታማነትና በማኅበራዊ ደህንነት የሚመለስ የትውልድ በረከት ነው። የኢትዮጵያ ሁኔታም ይህን ትኩረት የበለጠ አስፈላጊ ያደርገዋል፤ የዩኒሴፍ የ2024 እ.ኤ.አ መረጃ እንደሚያሳየው፣ በሀገራችን ከ5 ዓመት በታች ሕፃናት 39 በመቶ ያህሉ በመቀንጨር የሚጠቁ ሲሆን፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተሳትፎም 50 በመቶ ገደማ ነበር።

እዚህ ላይ በአዲስ አበባ የተጀመረው ጉዞ ልዩ ትርጉም ይኖረዋል። ከተማዋ ችግሩን በማየት ብቻ ሳትቆም፣ “የነገ ተስፋ ሕፃናት ለአዲስ አበባ” በሚል ርዕይ ከልጅ ልደት በፊት ጀምሮ እስከ ስድስት ዓመት ድረስ የጤና፣ የምግብ፣ የእንክብካቤ፣ የትምህርትና የጨዋታ አገልግሎቶችን በተቀናጀ መልኩ ለማዳረስ እየሠራች ነው። የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ከስድስት ዓመት በታች ሕፃናትንና 330 ሺህ በኢኮኖሚ ተጋላጭ ቤተሰቦችን ለመድረስ በማለም እየተተገበረ ነው። ይህ ማለት ከተማን በመንገድና በሕንፃ ብቻ ሳይሆን፣ በሰው ልጅ አቅም እየገነቡ እንዲቀጥሉ እየተሰራ ስለመሆኑ የሚያመላክት ነው። የተጀመረው ሥራ በቁጥር የሚታይ ለውጥ አምጥቷል። በ2015 ዓ.ም 11 ብቻ የነበሩት የሕፃናት ማቆያ ማዕከላት በ2018 ዓ.ም ከ1 ሺህ 155 በላይ መድረሳቸው፣ የልጆች መጫወቻዎችም ከ20 ወደ 5 ሺህ ማደጋቸው የለውጡን ስፋት ያሳያል።

ከዚህ የበለጠ የሚያኮራው ግን የአዲስ አበባ ልምድ ከከተማዋ ወሰን አልፎ ትኩረት ማግኘቱ ነው። የቀዳማይ ልጅነት ልማት ተሞክሮ ለሌሎች ከተሞችና ፖሊሲ አውጪዎች ሊያነሳሳ የሚችል ሞዴል ነው። ከዚህም በላይ ሰሞኑን የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዓለም አቀፉ “Act for Early Years” ኢኒሼቲቭ “Early Childhood Development Champion” ተብለው መሸለማቸው፣ ከተማዋ ለቀዳማይ ልጅነት እድገት የምትሰጠው ትኩረት በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እያገኘ መሆኑን ያሳያል። እውቅናው ዩኒሴፍ እና ዩኔስኮን ጨምሮ ከተለያዩ አጋር ተቋማት ጋር በተያያዘ መሆኑ የጉዳዩን ዓለም አቀፋዊ ክብደት ያሳያል።

ይሁንና ይህ እውቅና የመጨረሻ የስኬት መዳረሻ ሳይሆን ተጨማሪ ሥራ የሚጠይቅ የኃላፊነት ምልክት ነው። የአዲስ አበባ ነዋሪዎችም የዚህ ታሪክ ተመልካቾች ሳይሆኑ ተሳታፊዎች ናቸው። ልጅን በተገቢው መመገብ፣ መንከባከብ፣ ማነቃቃት፣ ማንበብን እንዲወዱ ማድረግ፣ እንዲጫወት ዕድል መስጠትና ከጥቃት መጠበቅ የቤተሰብ ብቻ ሳይሆን የማኅበረሰብ ጉዳይም ነው። ዛሬ በልጆቻችን ላይ የምናደርገው እያንዳንዱ ጥረት ነገ በተማረ፣ በጤናማ፣ በፈጠራ ችሎታ በበለፀገና ለሀገሩ አስተዋጽኦ በሚያደርግ ዜጋ መልክ ይመለሳል። ነገ የሚያምር ከተማና የበለፀገች ሀገር ከፈለግን፣ የነገ ተስፋችንን ዛሬ መንከባከብ አለብን፤ አዲስ አበባም ይህንን ነገ ዛሬ እየሠራች ነው!

## የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ሀገራዊ ቁጭት የሚፈጥረው የቆዳና ሌጦ ብክነት

**በቶሌራ ከቦሌ አራብሳ**

ዓለም አቀፉ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ገበያ በየዓመቱ በመቶ ቢሊዮን ዶላሮች የሚቆጠር ግዙፍ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚያስተናግድ ዘርፍ ነው። በዘመናዊ የኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ፣ በጥራት ቁጥጥርና በተደራጀ የግብይት ሥርዓት የታገዙ ሀገራት ከዚህ ዘርፍ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማፍራትና የሥራ ዕድል በመፍጠር ላይ ይገኛሉ። እንደ ጣሊያን፣ ቻይና፣ ብራዚልና ቬትናም ያሉ ሀገራት የጥሬ ቆዳ አቅርቦታቸውን ወደ ላቀ የተጠናቀቁ የፋሽንና የኢንዱስትሪ ምርቶች በመቀየር በዓመት በአማካይ ከ10 እስከ 35 ቢሊዮን ዶላር የሚደርስ ገቢ እንደሚያገኙ መረጃዎች ያመላክታሉ። በተለይም ጣሊያን ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የቆዳ ቦርሳዎች፣ ጫማዎችንና አልባሳትን ለዓለም ገበያ በማቅረብ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ልታጠናክርበት ችላለች።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ በከብት፣ በበግና በፍየል ሀብት ከአፍሪካ አንደኛ እንዲሁም ከዓለም በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀስ ብትሆንም፣ ከዘርፉ የምታገኘው ገቢ ግን እጅግ አነስተኛና የሚያስቆጭም ጭምር ነው። ሀገራችን ባላት ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ልክ ከዓለም አቀፉ የቆዳ ገበያ ማግኘት የሚገባትን ድርሻ ማግኘት አልቻለችም። ይልቁንም በየዓመቱ በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር የውጭ ምንዛሬ ልታስገኝ የምትችለው የቆዳና ሌጦ ሀብት በየአካባቢው ተጥሎ ሲበላሽ ማየት የተለመደ ክስተት ሆኗል። ይህ አጋጣሚ ለኢንዱስትሪው እድገትና ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ትልቅ ማዕቀብ ሆኖ ቀጥሏል።

ለዚህ አሳዛኝ እውነታ በርካታ መዋቅራዊና አሰራራዊ ችግሮች በምክንያትነት ይጠቀሳሉ። የመጀመሪያውና ዋናው ችግር በቄራዎችና በባህላዊ እርድ ወቅት የሚፈጸም የጥራት ጉድለት፣ የቆዳ መላጥ፣ የመበሳትና የመቆረጥ አደጋ ሲሆን፣ ይህም የጥሬ ቆዳውን የገበያ ዋጋ ያወርደዋል።

በተጨማሪም ያልተደራጀና ደላሎች የተቆጣጠሩት የግብይት ሰንሰለት፣ የጥሬ ቆዳ አሰባሰብና ማጓጓዣ ሥርዓት ዘመናዊ አለመሆን እንዲሁም የቆዳ ፋብሪካዎች የውጭ ምንዛሬ፣ የኬሚካልና የመለዋወጫ እጥረት ገጥሟቸው በሙሉ አቅማቸው ማምረት አለመቻላቸው ዘርፉን ጎድቶታል።

ይህንን ሀገራዊ ቁጭት ወደ አስተማማኝ የኢኮኖሚ ጥቅም ለመቀየር የተቀናጀ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። በቅድሚያ ከእርድ አፈጻጸም ጀምሮ የጥራት ቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር፣ ለቆዳ ሰብሳቢዎችና ለቄራ ሰራተኞች በቂ ስልጠና መስጠትና ዘመናዊ የቆዳ መላጫ መሳሪያዎችን ማቅረብ ይገባል። አርብቶ አደሩና አርሶ አደሩ ከቆዳና ሌጦ ሽያጭ ተገቢውን ጥቅም የሚያገኝበት ቀጥተኛና ግልጽ የገበያ ትስስር መዘርጋት አስፈላጊ ነው።

ሀገሪቱ ጥሬ ቆዳ ከመሸጥ ይልቅ እሴት የተጨመረባቸውን የቆዳ ውጤቶች እንደ ጫማ፣ ቦርሳና አልባሳት አምርታ ለውጭ ገበያ እንድታቀርብ የሀገር ውስጥ አምራቾችን በብድር፣ በቴክኖሎጂና በውጭ ምንዛሬ ማገዝ ወሳኝ ነው። የቆዳና ሌጦ ዘርፍን ማዘመን ከተቻለ የሥራ ዕድል ከመፍጠሩ ባሻገር የሀገራችንን የውጭ ምንዛሬ እጥረት በዘላቂነት ለመቅረፍ ትልቅ ሚና ይጫወታል።


በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
እዮብ ተፈራ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ጓዴ
ለይላ መሀመድ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ
ቶለሳ መብራቴ

# የኢትዮጵያ... ከገጽ 1 የዞረ

የኢንዱስትሪና የንግድ ዘርፉ የጀርባ አጥንት መሆናቸውን ይጠቁማሉ።

በሌላ በኩል፣ ቻንግ (ዶ/ር) ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀምና ድጋፍ በመስጠት በግብርናው ዘርፍ የሚደረግ ኢንቨስትመንት በምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና ድንገተኛ ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን እንዲሁም አደጋዎችን የመቋቋም አቅምን ለመገንባት ወሳኝ መሆኑን ይጠቅሳሉ። በቻንግ (ዶ/ር) እይታ፣ አገራት በኃይል፣ በሎጂስቲክስ፣ በከተሞች እድሳት እና በምግብ ዋስትና መካከል የተቀናጀ ስትራቴጂ ሲተገበሩ ሁለንተናዊና ዘላቂ የሆነ የኢኮኖሚ ማንሰራራት ማረጋገጥ እንደሚቻል ይገልጻሉ።

አንድ ሀገር ከጥገኝነት ተላቅቆ ወደ ዘላቂ ብልፅግና በሚያደርገው ጉዞ፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የኢነርጂና የሎጅስቲክስ ሉዓላዊነትን መጎናጸፍ እንዲሁም ግዙፍ መሠረተ ልማቶችን መገንባት የማንሰራራቱ ዋነኛ ምሰሶዎች ናቸው። ኢትዮጵያ በራሷ አቅምና በሕዝቦቿ የተቀናጀ ርብርብ እያከናወነቻቸው የምትገኘው ስልታዊ ፕሮጀክቶች፣ ይህንን የኢኮኖሚ ማንሰራራትና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እውን ለማድረግ የተቀመጠውን ጽኑ መሠረት በግልጽ ያሳያሉ። ከኃይል ማመንጨት እስከ ምግብ ዋስትና፣ ከማዕድንና ኢንዱስትሪ ልማት እስከ ዘመናዊ የአቪዬሽንና የከተሞች ማደስ ድረስ የተዘረጉት እነዚህ ጥረቶች፣ ሀገሪቱ ወደ አዲስ የልማትና የብልፅግና ምዕራፍ እያደረገች ያለችውን ሽግግር ያረጋግጣሉ፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሀገሪቱ በራሷ አቅምና በሕዝቦቿ የተቀናጀ ተሳትፎ እውን ያደረገችው የማንሰራራት ዋነኛ ማሳያ ነው። ግድቡ ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ ወደ ሥራ በመግባቱ ሀገሪቱ ከዚህ ቀደም ካላት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም ከእጥፍ በላይ በማሳደግ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችንና የቤተሰብ ፍላጎቶችን በበቂ ሁኔታ እንድታሟላ አግዟል። ከዚህም ባለፈ እንደ ሱዳን፣ ጂቡቲ፣ ኬንያ እና ሶማሊያ ላሉ የጎረቤት ሀገራት ኤሌክትሪክ በመሸጥ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከማስገኘቱም በላይ የምስራቅ አፍሪካን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ትስስር ያጠናክራል። ከምንም በላይ ግን ያለ ምንም የውጭ ብድር በሀገር ውስጥ ገንዘብና እውቀት የተገነባ በመሆኑ ሀገራት የተፈጥሮ ሀብታቸውን በራሳቸው አቅም የመጠቀም መብታቸውን በተግባር ያረጋገጡበት ታሪካዊ ፕሮጀክት ነው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የልማት ጥናት መምህርና ተመራማሪ ፕሮፌሰር ደገፋ ቶለሳ እንደሚገልጹት፣ የግድቡ ግንባታ መጠናቀቅ የኃይል ፍላጎትን ከመመለስ በላይ የውስጥ አቅምን በመረዳት ግዙፍ ፕሮጀክቶችን ከውጭ ፋይናንስ ጥገኝነት በጸዳ መልኩ ማጠናቀቅ እንደሚቻል ያሳየ ታሪካዊ ምዕራፍ ነው። ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተሰበሰበ ሀብትና በሙያተኞች እውቀት "በይቻላል መንፈስ" የተገነባ በመሆኑም እንደ ሁለተኛው የዓድዋ ድል የሚወሰድ ሀገራዊ ኩራት ሆኗል።

በተመሳሳይ፣ በሱማሌ ብሔራዊ ክልል በኦጋዴን የተገነባው የተፈጥሮ ጋዝ ፋብሪካ ከውጭ የሚገባውን ፈሳሽ ጋዝ በሀገር ውስጥ በመተካት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬን የሚያድን ብሎም ለኬሚካል ኢንዱስትሪዎች፣ ለኃይል ማመንጫዎችና ለኬሚካል ማዳበሪያ ምርት እንደ ዋነኛ ጥሬ ዕቃ በማገልገል የኢትዮጵያን የኢነርጂና የኢንዱስትሪ ምሕዳር በከፍተኛ ሁኔታ የሚቀይር አዲስ ምዕራፍ ነው።


ፎቶ:- ከገጸ ድር
የኢትዮጵያን ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከሚያረጋግጡ ግዙፍ የልማት ስራዎች መካከል ጥቂቶቹ

ፕሮፌሰር ደገፋ፣ በግብርናው ዘርፍ የተመዘገበው የስንዴ ምርታማነት ሌላው የሀገሪቱ የማንሰራራት ትልቅ ማሳያ ነው። በመኸርና በበጋ መስኖ ልማት የተመዘገበው የስንዴ ምርት ዕድገት ኢትዮጵያ በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረገው ጥረት ያሳየችው ትልቅ መዋቅራዊ ሽግግር መሆኑን የልማት ጥናት ምሁሩ አልሸሸጉም። ሀገሪቱ ለዘመናት ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የምታስገባውን ስንዴ በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ብቻ ሳይሆን ለውጭ ገበያ ማቅረብ መጀመሯ የሚደነቅ የፖሊሲ ስኬት ነው። በዝናብ ላይ ብቻ የነበረውን የግብርና ጥገኝነት በማስቀረት፣ አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በመተግበር እና የመስኖ መሬቶችን በማስፋፋት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥና የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ማፋጠን ተችሏል።

የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ከአካባቢ ጥበቃ ባለፈ ዘላቂ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ፋይዳ ያለው ሀገራዊ ንቅናቄ ነው። ከ56 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል የሀገሪቱን የደን ሽፋን ማሳደጉ የካርቦን ልቀትን ለመቀነስና አፈር መሸርሸርን ለመከላከል አስችሏል። በተጨማሪም የተተከሉት ችግኞች የተፈጥሮ ሚዛን ከመጠበቅ ባለፈ የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጡ በርካታ የፍራፍሬ ዓይነቶችንና ለእንጨት ኢንዱስትሪ የሚሆኑ ዕፅዋትን ያካተቱ በመሆናቸው ለገበሬው የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ምንጭ እየሆኑ ይገኛሉ።

> **"ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴው ግድብ፣ የተፈጥሮ ጋዝ ፋብሪካ፣ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር እንዲሁም በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙት የአየር መንገድ ግንባታ፣ የከሰል ድንጋይ፣ የጋዝና የአፈር ማዳበሪያ ፋብሪካዎች የኢትዮጵያ የማንሰራራት አቅምና ምልክቶች ናቸው"**

በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙት የአየር መንገድ፣ ሁለተኛው የተፈጥሮ ጋዝ እና የአፈር ማዳበሪያ ፋብሪካዎች የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከመሠረቱ የሚቀይሩ ስልታዊ ፕሮጀክቶች ናቸው። ሀገሪቱ በየዓመቱ ለማዳበሪያ ግዢ የምታወጣውን በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር በሀገር ውስጥ በማስቀረት ለሌሎች የልማት ዘርፎች ለማዋል ያስችላል።

በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች እየተገነቡ ያሉት የከሰል ድንጋይ ማጠቢያና ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ለከባድ ኢንዱስትሪዎች ትልቅ የሀገር ውስጥ አቅም እየፈጠሩ ነው። እነዚህ ፋብሪካዎች እንደ ሲሚንቶና ብረት ያሉ አምራች ዘርፎች ከውጭ የሚያስገቡትን የከሰል ድንጋይ በሀገር ውስጥ ጥራት ባለው የታጠበ ከሰል በመተካት የምርት ወጪያቸውንና የውጭ ምንዛሬ ፍላጎታቸውን ይቀርፋሉ። በተመሳሳይ ጊዜ በማዕድን ፍለጋና ማቀነባበሪያ ዘርፍ ለብዙ ሺህ ዜጎች አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን እየፈጠሩ ይገኛሉ።

በቢሾፍቱ አካባቢ ግንባታው የተጀመረው አዲሱ ሜጋ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት የኢትዮጵያን የአቪዬሽን አቅም በዓለም አቀፍ ደረጃ የበለጠ የሚያጠናክር ነው። አዲሱ አውሮፕላን ማረፊያ በዓመት እስከ 100 ሚሊዮን ተሳፋሪዎችን የማስተናገድ አቅም የሚኖረው ሲሆን፣ አዲስ አበባንና አካባቢዋን የአፍሪካ ዋነኛ የካርጎና የመሸጋገሪያ ማዕከል ያደርጋታል። ይህም የሀገሪቱን የወጪና ገቢ ንግድ ሎጅስቲክስ በማፋጠን ለቱሪዝምና ንግድ ዘርፍ ትልቅ ዕድገት ያመጣል።

የአዲስ አበባ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች እና መሰል ከተማን የማደስ ሥራዎች ሀገሪቱ ለዓለም አቀፍ ውድድርና ለዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ ምቹነት ያላትን ዝግጁነት የሚያሳዩ ናቸው። የእግረኛ መንገድ፣ የብስክሌት መስመሮች፣ አረንጓዴ ቦታዎችና የመዝናኛ ስፍራዎች መስፋፋታቸው ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹና ጤናማ አድርጓታል። ከዚህ በተጨማሪ የመብራት፣ የውሃ፣ የስልክ እና የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች ከመንገድ ግንባታው ጋር ተቀናጅተው በመሰራታቸው የከተማዋን ዘመናት የተሻገሩ መዋቅራዊ ችግሮች ፈትተዋል። ይህም አዲስ አበባ የአፍሪካ ኅብረት እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መቀመጫ እንደ መሆኗ፣ ዓለም አቀፍ ደረጃዋን የጠበቀች መዲና እንድትሆን አስችሏታል።

ፕሮፌሰር ደገፋ፣ የተመረቁና በግንባታ ላይ ያሉ አገራዊ ጥረቶች የውጭ ጫልቃ ገብነትንና ጥገኝነትን በመቀነስ፣ የኢትዮጵያን የምጣኔ ሃብት ነጻነትና የሉዓላዊነት ትርክት በአዲስ መልክ የሚገነቡ የሀገሪቱ የማንሰራራት ሕያው ምልክቶች ናቸው ብለዋል። በጥቅሉ ኢትዮጵያ በማንሰራራት ላይ እንደምትገኝ ጠቁመው፣ አስቀድማ እውን ያደረገቻቸው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴው ግድብ ግንባታ፣ የስንዴ ምርታማነት፣ የመጀመሪያው የተፈጥሮ ጋዝ ፋብሪካ፣ በስኬት ጎዳና ላይ ያለው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር እንዲሁም በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙት የጋዝና የአፈር ማዳበሪያ ፋብሪካዎች፣ የከሰል ድንጋይ ፋብሪካ፣ የአየር መንገድ ግንባታ እና በአዲስ አበባም የተከናወኑ ልዩ ልዩ የልማት ስራዎች የኢትዮጵያ የማንሰራራት አቅምና ምልክቶች እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡

እነዚህ ጥረቶች ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት፣ የሰው ኃይል እና ስልታዊ ብሔራዊ ዕቅድ አጣጥማ በመጠቀም ከመልማትና ራስን ከመቻል ፍላጎት ባሻገር፣ ወደ አዲስ የልማትና የብልፅግና ምዕራፍ እየተሸጋገረች መሆኗን የሚያረጋግጡ ተጨባጭ ማሳያዎች ስለመሆናቸው የልማት ጥናት ምሁሩ አስምሮበታል።

## ጥረት ... ከገጽ 1 የዞረ




ፎቶ- ከፋይል

በሴፍትኔት መርሃ ግብር ከተረጂነት ወደ አምራችነት የተሸጋገሩ ወይዘሮ ጤናዬ ተሰማ እና ወይዘሮ ዙልፋ መሃመድ

ይሁን የቤተሰባቸውን መሠረታዊ ፍላጎት ለማሟላት አልበቃቸውም ነበር።

በዚህ የፈተና ጊዜ ነበር በወረዳቸው የሁለተኛው ዙር የሴፍቲኔት ፕሮግራም ምዝገባ የተጀመረው። ያጋጠማቸውን የከፋ የኑሮ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ ዕድል ተሰጥቷቸው የፕሮግራሙ ተጠቃሚ መሆናቸው ለእሳቸውና ለልጃቸው ትልቅ እፎይታ እንደሰጣቸው ተናግረዋል።

ወይዘሮ ዙልፋ በፕሮግራሙ መሰረት ጧት ጧት የተመደቡበትን የጽዳት ሥራ በማከናወን፣ በትርፍ ጊዜያቸው ደግሞ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን እየሠሩ ኑሯቸውን ደረጃ በደረጃ ማሻሻል ጀመሩ። ይህ አዲስ ተስፋ የተሻለ ነገር የመፍጠር መነሳሳትን ጭሮባቸዋል።

ፕሮግራሙ ሲጠናቀቅ ከተሰጣቸው ድጋፍና ከቆጠቡት ገንዘብ ላይ የለውዝ ቅቤ ማምረቻ ማሽን በመግዛት የራሳቸውን የንግድ ድርጅት መሠረቱ። ዛሬ ላይ ልጃቸውን በተሻለ ሁኔታ ከማስተማርና ከመመገብ ባለፈ፣ ለውዝ በመልቀም፣ በመቁላትና በማሸግ ሥራዎች ላይ ለሁለት ሌሎች እንስቶችም የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል።

በዚሁ ወረዳ የሁለት ልጆች እናት የሆኑት ወይዘሮ ጤናዬ ተሰማም በተመሳሳይ ዕድል የራሳቸውን የተስፋ መንገድ የቀየሱ ሌላዋ ጥንካሬያቸው የሚያስደምም እናት ናቸው። የሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ ከመሆናቸው በፊት ልጆቻቸውን ለመመገብ ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም፤ ልብስ ከማጠብ እስከ እንጀራ መጋገር ያልሠሩት አድካሚ ሥራ ባይኖርም፣ ሕይወታቸው ግን ከድህነት ማቅ መውጣት ተስኖት ነበር።

“ሁለት ልጆችን ያለ አባት ማሳደግ፣ ያውም ቋሚ ሥራና አስተማማኝ ገቢ በሌለበት ሁኔታ ምን ያህል እንደሚከብድ መገመት አይከብድም” የሚሉት ወይዘሮ ጤናዬ፣ በወቅቱ ልጆቻቸውን ለመመገብ፣ ለማስተማርና ዕለታዊ ሕይወታቸውን ለመምራት ያሳለፉትን መራር ፈተና በእንባ በታጀበ ትዝታ ያስታውሱታል።

በሴፍቲኔት ፕሮግራም መታቀፋቸው ግን ያንን ከባድ የገንዘብ ጫና አቅልሎላቸዋል። የቤተሰባቸውን የምግብ ዋስትና አስተማማኝ ከማድረግ ባሻገር፣ በየወሩ የሚያገኙትን ትንሽ ገቢ ሳይቀር እየቆጠቡ የራሳቸውን ሥራ የመፍጠር ትልቅ ሕልም እንዲሰንቁ አደረጋቸው።

ፕሮግራሙ ሲጠናቀቅ በራሳቸው ቁጠባና ከመንግሥት በተደረገላቸው ድጋፍ በእደ-ጥበብ ሥራ ላይ ተሰማሩ። ዛሬ ላይ ሥራቸውን አስፋፍተው 10 እናቶችን በማሠልጠንና አብረዋቸው እንዲሠሩ በማድረግ ለሌሎች የተስፋ ብርሃን መሆን ችለዋል። ለወደፊቱም የብድር አገልግሎት ከተመቻቸላቸው ሥራቸውን ይበልጥ በማስፋፋት በርካታ እናቶችን በሥራ የማቀፍ ትልቅ እቅድ አላቸው።

“ማንኛውም ሰው ሥራን ሳይንቅ በተፈጠሩ የሥራ አማራጮች በመስራት ከኢኮኖሚ ጥገኝነት መላቀቅ ይችላል” የሚሉት ወይዘሮ ጤናዬ፣ “በከተማችን ሥራው ሰው አጣ እንጂ የሚሠራ ሥራ አልጠፋም” ሲሉ ተናግረዋል።

ጳጉሜ 1 የእመርታ ቀን ነው:: ሀገራችን ብሎም ከተማችን ከተረጂነት ወደ አምራችነት እያደረገች ባለችው ታሪካዊ ሽግግር ውስጥ የሴፍቲኔት መርሃ ግብር የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም:: በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አነስተኛ ገቢ ያላቸውንና በከፍተኛ የድህነት ወለል ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን በዘላቂነት ለማቋቋም የሚደረገው የከተማ ሴፍቲኔት ፕሮግራም፣ በርካቶችን ከእጅ ወደ አፍ ሕይወት አውጥቶ ወደ አምራችነትና ወደ ስራ ፈጣሪነት በማሸጋገር ላይ ይገኛል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራና ክህሎት ቢሮ የምግብ ዋስትና እና ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት የህብረተሰብ ተሳትፎ ቡድን መሪ አብርሃም እልፌ እንደሚገልፁት፣ ፕሮግራሙ በ2009 ዓ.ም ጥር ወር ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን በስራ ልምምድ ከተካተቱ ወጣቶች ጋር ተደምሮ 730 ሺህ 57 ዜጎችን በ196 ሺህ 702 የቤተሰብ ተወካዮች አማካኝነት በተለያዩ ምዕራፎች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

ፕሮግራሙ በተለያዩ ምዕራፎችና በገንዘብ ድጋፍ ምንጮች ተከፋፍሎ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ምዕራፍ 94 ሺህ 25 የቤተሰብ ተወካዮች፣ በሁለተኛው ምዕራፍ 31 ሺህ 2፣ በተጨማሪ ፋይናንስ ሁለት 6 ሺህ 640 የቤተሰብ ተወካዮች እንዲሁም የመንግስት አቻ ፈንድ 39 ሺህ 41 የቤተሰብ ተወካዮች ታቅፈዋል።

በአሁኑ ወቅትም በተጨማሪ 25 ሺህ 994 የቤተሰብ ተወካዮች በሂደት ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ ከቅድመ ዝግጅት እስከ ትስስር ባለው ሂደት ደግሞ 65 ሺህ 35 የቤተሰብ ተወካዮች ይገኛሉ። የመጀመሪያው፣ የሁለተኛውና የክፍል አንድ ተጨማሪ ፋይናንስ ተጠቃሚዎች ሙሉ በሙሉ ተመርቀው ወደ መደበኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መሸጋገራቸውን አቶ አብርሃም ተናግረዋል።

በሴፍቲኔት ፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችን በሁለት ዋና ዋና ዘርፎች ከፍለው የሚስተናገዱ መሆናቸውን የገለጹት አቶ አብርሃም፣ የመጀመሪያው ከአጠቃላይ ኮታው 16 በመቶ የሚሆነውና በሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የሚመራው የቀጥታ ድጋፍ ነው። ይህ ዘርፍ ሙሉ በሙሉ መስራት የማይችሉ አረጋውያንን፣ የአካል ጉዳተኞችንና ከእድሜ ክልል ውጪ ያሉ አቅመ ደካሞችን ያቀፈ ሲሆን ያለ ምንም አካላዊ ስራ ቀጥታ የገንዘብ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

በሌላ በኩል 84 በመቶ የሚሸፍነው የልማት ስራዎች ደግሞ ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 60 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙና መስራት የሚችሉ ዜጎችን የሚያሳትፍ ሲሆን፣ በደረቅ ቆሻሻ፣ በውበትና አረንጓዴ ልማት፣ በከተማ ግብርና፣ በአነስተኛ መሰረተ ልማትና በተፋሰስ ልማት ስራዎች ላይ ተሰማርተው በሰሩት ልክ በዓለም ባንክ መስፈርት መሰረት የሚከፈላቸው ነው።

ተጠቃሚዎቹም እውነተኛ ደሃ የሆኑ ዜጎች ብቻ እንዲካተቱ ለማድረግ ግልጽና ጥብቅ አሰራር የሚከተል አራት ደረጃ ያለው የማጣራት ሂደት ይተገበራል። በ11 ክፍለ ከተሞች፣ በ119 ወረዳዎችና በ781 ክላስተሮች ውስጥ የልየታና የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ተደራጅተው የሚሰሩ ሲሆን፣ የተመረጡ አባላት ስም ዝርዝር በግልጽ ቦታ ተለጥፎ ህብረተሰቡ ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት አስተያየትና ቅሬታ እንዲሰጥበት ይደረጋል።

በመቀጠልም በዓለም ባንክና በባለሙያዎች በተዘጋጁ 12 የኑሮ ደረጃ መለኪያ መስፈርቶች (PMT) ቤት ለቤት የመጨረሻ ማጣራት ከተከናወነ በኋላ፣ የባንክ ሂሳብ ደብተር፣ የብሔራዊ መታወቂያ እና የሙያ ስነ-ምግባር ስልጠና ተሰጥቷቸው ተጠቃሚዎቹ ወደ ስራ ይገባሉ።

ተጠቃሚዎች በፕሮግራሙ በሚቆዩበት ጊዜ ቀጣይነት ያለው የሕይወት ክህሎት፣ የቢዝነስ ፕላን ዝግጅት እና የካፒታል ቁጠባ ስልጠና የሚያገኙ ሲሆን፣ ከመደበኛ ክፍያቸው 20 በመቶ እንዲሁም ከተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ስራዎቻቸው 50 በመቶ እንዲቆጥቡ ይደረጋል። ፕሮግራሙን አጠናቀው ሲወጡም በወቅቱ ምንዛሬ ታስቦ የ600 የአሜሪካ ዶላር ግራንት እና የቆጠቡት ገንዘብ ተደምሮ ለስራ ማስጀመሪያ ይሰጣቸዋል።

በተጨማሪም በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ለ3 ወራት የሙያ ስልጠና የሚያገኙ ሲሆን፣ ቢሮው በራሱ በጀት ባስገነባቸው 19 ሼዶች እና 4 የ G+4 ህንፃዎች ውስጥ 292 ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው በመስራት ላይ ይገኛሉ፤ በአሁኑ ወቅትም በአራዳ ክፍለ ከተማ ተጨማሪ G+8 ህንፃ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

በስራ ሂደቱ ላይ እንደ የተረጅነት አስተሳሰብ፣ የመስሪያ ቦታ ጥበት እንዲሁም የብድርና የሕጋዊ ሰነዶች ችግር ያሉ ተግዳሮቶች የሚያጋጥሙ ቢሆንም፣ አስተዳደሩ በራሱ አቅም ህንፃዎችን በመገንባት፣ ልዩ የብድር ማቃለያዎችን በማመቻቸትና ተጠቃሚዎች ከወጡ በኋላም የድጋፍና ክትትል ስራዎችን በመስራት መፍትሔ ለመስጠት እየሰራ ነው። በስራና ክህሎት ቢሮ የተገነቡት ህንፃዎችና ሼዶችም ያለአግባብ ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፉ በየ15 ቀኑና በየሩብ ዓመቱ ጥብቅ ኦዲት ይደረግባቸዋል።

በአጠቃላይ የከተማ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተራ የገንዘብ እርዳታ ከመስጠት ባለፈ የዜጎችን ስነ-ልቦና፣ የሙያ ክህሎት፣ የቁጠባ ባህልና የመስሪያ ቦታ አቅም በማሳደግ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን ዜጎች ከዜሮ ተነስተው ምርቶቻቸውን እስከ ውጭ ሀገር ኤክስፖርት ወደ ማድረግ ደረጃ ያሸጋገረ የልማት ሞዴል ሆኖ ቀጥሏል።

# የመቻል አቅም መስታወቶች

**• ኢትዮጵያውያን በህብረትና በጽናት ፈተናዎችን ወደ ታላላቅ ሀገራዊ ስኬቶች የመቀየር የተግባር ማሳያዎች ያሏቸው ህዝቦች ናቸው**

**በቶለሳ መብራቴ**

የኢትዮጵያ ታሪክ ከተራ ተስፋ ይልቅ በተግባር፣ በጽናት፣ በቁርጠኝነት እና በህብረት የተገነባ መሆኑን ታሪካዊ ክስተቶች በግልጽ ይመሰክራሉ። ኢትዮጵያውያን ተባብረው ሲነሱ የማይበገሩበትን፣ ፈተናዎችን ወደ መልካም አጋጣሚ የሚቀይሩበትን እና ትልልቅ የታሪክ ድሎችን የሚያስመዘግቡ የተግባር ህዝቦች መሆናቸውን በተደጋጋሚ አሳይተዋል። ይህ የተግባር አቅም በዘመናት መካከል በሚከሰቱ ሀገራዊ ጥሪዎችና ፈተናዎች ውስጥ በግልጽ እየጎላ ወጥቷል።

ለጋራ ዓላማ በጋራ መቆምን፣ መስዋዕትነት መክፈልን እና በፈተናዎች ሳይበገሩ አብሮ ተባብረው በፅናት መሰለፍን የተካኑት ኢትዮጵያውያን፣ ይህ ፅናታቸው ታሪክ ተሻጋሪና አንፀባራቂ ድሎችን አጎናፅፈዋቸዋል፡፡ በቁርጠኝነት፣ በውድ መስዋዕትነት፣ በአንድነት፣ በአይበገሬ ፅናት፣ በውስብስብ እና አስቸጋሪ ፈተናዎች ውስጥ አልፈው እውን ካደረጓቸው ድሎች መካከል የዓድዋ ድል፣ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እና ሌሎች በርካታ እሴቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡



ፎቶ፡- ገፀ ድር

ኢትዮጵያውያን በትብብርና በፅናት እውን ያደረጓቸው በርካታ ዘመን ተሻጋሪ የጋራ ታሪክ እና ሀብቶች አሏቸው

ኢትዮጵያ በአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ የተቀዳጀችው የዓድዋ ድል እና በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን እውን ያደረገችው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የዚሁ ህዝባዊ ትብብር ያስገኟቸው ውጤቶች መገለጫ ናቸው። ባለፉት ስምንት ተከታታይ ዓመታት ሲካሄድ የቆየው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ደግሞ የዚሁ ዘመን የመቻልና የተግባር ምልክት ቀጣይ ታሪካዊ ማሳያ ሆኖ ተመዝግቧል።

የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያንን አንድነትና የተግባር ሰውነት ለዓለም ያስመሰከረ የመጀመሪያው ታላቅ የታሪክ ምዕራፍ ነው። በወቅቱ የነበሩት ኢትዮጵያውያን በቋንቋ፣ በባህልና በጂኦግራፊ ሳይወሰኑ ሀገራዊ ጥሪን ተቀብለው በጽናት በመቆም የወረራን አደጋ መክተዋል። የዓድዋ ድል ተራ ወታደራዊ ስኬት አይደለም፤ ህዝቦች ተባብረውና በአንድነት ተነስተው የቴክኖሎጂና የኃይል ብልጫ ያለውን አካል ማሸነፍ እንደሚችሉ ያረጋገጠ የታሪክ ማሳያ ነው።

በተመሳሳይ መልኩ፣ በዘመናችን እውን የሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የዚሁ ታሪካዊ የመቻል መንፈስ አካል ነው። ግድቡ የውጭ የፋይናንስ ምንጭ ሳይጠበቅ፣ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን እውቀት፣ ጉልበትና የገንዘብ አስተዋጽኦ የተገነባ ግዙፍ ፕሮጀክት ነው። ኢትዮጵያውያን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገራት በመሆን የቦንድ ግዥ በመፈጸም፣ ወርሃዊ ደመወዛቸውን በመለገስና ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ ተዓምር ሊባል የሚችል ስራ ሰርተዋል። ይህ ፕሮጀክት ኢትዮጵያውያን "አንችልም" የሚለውን አስተሳሰብ ሰብረው፣ የተጀመረን ስራ እስከ መጨረሻው ማድረስ የሚችሉ የተግባር ሰዎች መሆናቸውን ዳግም ያረጋገጡበት ትልቅ የታሪክ መሰረት ነው።

ከዓድዋ ድል እና ከህዳሴው ግድብ በመቀጠል፣ ባለፉት ስምንት ተከታታይ ዓመታት ሀገሪቱ ስታካሂደው የቆየችው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የኢትዮጵያውያንን የተግባር ማህበረሰብ በህብረት በአዲስ መልክ ለዓለም ያሳየ ክስተት ነው። መርሃ ግብሩ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል፣ የአፈር መሸርሸርን ለመግታትና የደን ሽፋንን ለማሳደግ ታልሞ የተጀመረ ሀገራዊ ንቅናቄ ነው።

ይህ መርሃ ግብር ተራ የዛፍ ተከላ ብቻ ሳይሆን፣ ሚሊዮኖች በአንድ ሀገራዊ ዓላማ ስር የተሰበሰቡበትና የተለያየ የህብረተሰብ ክፍል ያለ ልዩነት አካፋና ዶማ ይዞ ወደ ሜዳ የወጣበት ትልቅ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ነው። ኢትዮጵያውያን ለዓድዋ ዘመቻ እና ለታላቁ የህዳሴው ግድብ ግንባታ እንደጎረፉት ሁሉ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርም ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አዛውንቶች፣ የመንግስትና የግል ተቋማት ሰራተኞች በአንድነት በመሰለፍ ሀገራዊ ጥሪውን በተግባር መልሰዋል።

በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የአደጋ መከላከልና የምጣኔ ሃብት መምህርና ተመራማሪ አሸናፊ ኃይሉ (ዶ/ር)፣ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን ከሌሎች መሰል እንቅስቃሴዎች ልዩ የሚያደርገውና የኢትዮጵያውያንን የመቻል አቅም የሚያጎላው ዋነኛው ምክንያት መርሃ ግብሩ ሳይቋረጥና ሳይዛባ ለስምንት ተከታታይ ዓመታት መዝለቁ እንደሆነ ይገልጻሉ። ብዙ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ፕሮጀክቶች በመጀመሪያው ዓመት ተጀምረው በሂደት ትኩረት በማጣት የሚዳከሙበት ሁኔታ ቢስተዋልም፣ የአረንጓዴ አሻራው ግን ከዓመት ዓመት በተመሳሳይ ድምቀት፣ ጉልበትና የመተባበር መንፈስ ቀጥሏል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በዘንድሮው የአረንጓዴ ዐሻራ ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፣ መርሃ ግብሩ ኢትዮጵያውያን በጋራ በመሆን አረንጓዴና ዘላቂነት ያለው ሀገር መገንባት እንደሚችሉ በተግባር ያሳየ መሆኑን ገልጸዋል። አባቶቻችን በዓድዋ ላይ ወራሪን በማሳፈር ገድል እንደሠሩ ሁሉ፣ የእኛም ትውልድ በአረንጓዴ ዐሻራ ለትውልድ የሚሻገር ሌላ ታላቅ ገድል እየሠራ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተደጋጋሚ ሲያነሱ ይስተዋላል።

ከዚህም በላይ መርሃ ግብሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ አድናቆትን ባተረፉ በአንድ ጀንበር በሚካሄዱ ታላላቅ የችግኝ ተከላ ሁነቶች ታጅቦ መጓዙ የህዝቡን ልዩ ቁርጠኝነት ያሳያል። በ2011 ዓ.ም በአንድ ጀንበር ከ353 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል የተጀመረው ይህ ታሪካዊ ስኬት እያደገ በመምጣት፣ በ2018 ዓ.ም በአንድ ጀንበር ከ805 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል አዲስ በዓለም አቀፍ ደረጃ ህዝባዊ ተሳትፎ ሪኮርድ ማስመዝገብ አስችሏል። በስምንት ዓመታት የዘመቻ ጊዜ ውስጥ ከ56 ቢሊዮን በላይ ችግኞች የተተከሉ ሲሆን፣ ይህም ሀገሪቱ የያዘችውን የ65 ቢሊዮን ችግኞች ግብ ለማሳካት አብዛኛውን መንገድ እንድትጓዝ አድርጓታል።

የዚህ ያልተቋረጠ ሀገራዊ ንቅናቄ ውጤት በቃላት ስብከት ሳይሆን በመሬት ላይ በሚታይ ተጨባጭ ለውጥ የተረጋገጠ ነው። ሀገሪቱ በ1980ዎቹ መጨረሻ ደርሳበት ከነበረው ዝቅተኛ የደን ሽፋን (ከ3 በመቶ በታች) በመነሳት፣ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የደን ሽፋኑን ወደ 23 ነጥብ 6 በመቶ ማሳደግ ችሏል። በተጨማሪም ከተተከሉት ችግኞች መካከል አብዛኞቹ ለምግብነት የሚያገለግሉ የአቮካዶ፣ የማንጎ፣ የዘይቱን፣ የብርቱካን፣ የኮክ፣ የዘይቱን፣ የአፕል እና መሰል ተክሎች በመሆናቸው የአነስተኛ አርሶ አደሮችን ገቢና የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ አስችለዋል። በተከናወኑ የተቀናጁ የውሃና አፈር ጥበቃ ስራዎች ምክንያትም የከርሰ ምድር ውሃ መጠን እንዲያገግም፣ የወንዞች ደለል እንዲቀንስና የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገራት የተረጋጋ የውሃ ፍሰት እንዲያገኙ አድርጓል።

እንደ አሸናፊ (ዶ/ር) ማብራሪያ፣ ባለፉት ስምንት ተከታታይ ዓመታት የተካሄደው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከአካባቢ ጥበቃና ከዛፍ ተከላ ስራ ያለፈ ትልቅ ሀገራዊና ስነ-ልቦናዊ ትርጉም አለው። ኢትዮጵያውያን ታሪካቸውን በቃላት ሳይሆን በተግባር፣ በፉከራ ሳይሆን በስራ የሚጽፉ የጽናት ባለቤቶች መሆናቸውን ያረጋገጡበት አዲስ መድረክ ነው።

አባቶቻችን በዓድዋ ሀገራዊ ነጻነትን የዚህ ትውልድ አባላት በህዳሴው ግድብ የኢኮኖሚና የኃይል ነጻነትን ለማረጋገጥ እንደታገሉት ሁሉ በአረንጓዴ አሻራ የተመዘገበው ስኬትም ሀገሪቱን ከአካባቢ መራቆትና ከአየር ንብረት ስጋት የመታደግ ታላቅ የተግባር ድል ነው። መርሃ ግብሩ ኢትዮጵያውያን ሲተባበሩና በአንድ ሀገራዊ ዓላማ ስር ሲቆሙ የማይበገሩ እና የታለመውን ግብ በጽናት ማሳካት የሚችሉ መሆናቸውን ለዓለም ያስመሰከረ አዲስ የመቻል ትርክት ነው።

ኢትዮጵያ እስከ አሁን ባለው ጊዜ ውስጥ ከ56 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከልና የደን ሽፋኑን በመጨመር የተግባር መሪነቷን አስመስክራለች። ይህ ስኬት ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ በንግግር ሳይሆን በተግባር የለወጠች ሀገር መሆኗን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በማስመስከሩ መድረኩን እንድታገኝ እንዳስቻላት አሸናፊ (ዶ/ር) አስረድተዋል።

መላ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ሆነው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን ማስቀጠላቸው በሀገር ደረጃ የአፈር መሸርሸርን ለመቀነስ፣ የነጠፉ ምንጮችና ወንዞች እንዲያንሰራሩ ለማድረግና አካባቢን ለመጠበቅ አስችሏል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ የበካይ ጋዞችን በመምጠጥ ረገድ የምታበረክተውን ሚና በማሳየት የሀገሪቱን በጎ ገጽታ ከመገንባቱ በላይ የአረንጓዴ ዲፕሎማሲ አቅሟን አጠናክሮላታል። ይህ ተግባር ኢትዮጵያ በካርበን ንግድ እና በፓሪስ ስምምነት ማዕቀፍ ውስጥ ተጠቃሚ እንድትሆን መንገድ የሚከፍት መሆኑን አሸናፊ (ዶ/ር) ተናግረዋል።

ኢትዮጵያውያን በጋራ ሲቆሙና ሲተባበሩ የራሳቸውን ሀገራዊ የተፈጥሮ ጸጋ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን፣ የቀጠናውን የውሃና የአካባቢ ደህንነት በማረጋገጥ ለዓለም አቀፍ የአየር ንብረት መረጋጋት አዎንታዊ አሻራቸውን ያኖራሉ። ይህም የጋራ መተባበርና ቁርጠኝነት ከሀገር ውስጥ ህብረት ተሻግሮ በዓለም አቀፍ መድረክ ታሪካዊ መሪነትንና ተጽዕኖ ፈጣሪነትን በተግባር የሚያረጋግጥበት ታላቅ ማሳያ ነው።

# እውቅና የተቸረው የትውልድ ግንባታ

- **የነገን ትውልድ ታሳቢ ያደረገውን የአዲስ አበባ “የቀዳማይ ልጅነት እንክብካቤ ፕሮጀክት” የተለያዩ ሀገራት በተሞክሮነት እየወሰዱት መሆኑም ተጠቁሟል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

ዛሬ የአደጉ ሀገራት የእድገትና የብልፅግና ማማ ላይ መድረስ ቁልፉ ምስጢር ለሰው ሀብት ልማት ከሰጡት ከፍተኛ ትኩረት ጋር ይያያዛል። እንደነ ፊንላንድ፣ ቻይና፣ ጃፓን እና እስራኤል ያሉ ሀገራት ከታች ጀምሮ በህጻናት ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን በማፍሰስ ትላልቅ ፈጠራዎችን የሚፈበርኩ፣ በስነ ምግባርና በዲሲፕሊን የታነፁ እንዲሁም ሀገራቸውን የሚወዱ ዜጎችን ማፍራት ችለዋል።

ጤናማ፣ አምራችና ብቁ የሰው ሀይል ለመፍጠር መሰረት የሚጣለው በለጋ የልጅነት ዕድሜ ላይ ነው፡፡ የዓለም ጤና ድርጅት መረጃ እንደሚያመላክተው፣ የሰው ልጅ ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው የአእምሮ ዕድገቱ የሚሰራው በመጀመሪያዎቹ ስድስት ዓመታት ውስጥ ነው፡፡ ይህ የቀዳማይ ልጅነት ልማትና እንክብካቤ የሚከናወንበት የእድሜ ክልል ከዚህ ቀደም በሀገር አቀፍም ሆነ በአዲስ አበባ ደረጃ ትኩረት ተነፍጎት ቆይቷል። በዚህ ምክንያት የነገው ሀገር ተረካቢ ትውልድ ሁለንተናዊ እድገት ላይ ስብራት አጋጥሞ መቆየቱን መረጃዎች ያመለክታሉ። በከተማ አስተዳደሩ “የነገ ተስፋ ሕፃናት ለአዲስ አበባ፤ የቀዳማይ ልጅነት እንክብካቤ ፕሮጀክት” በሚል ርዕስ በ2014 ዓ.ም የተዘጋጀው ሰነድ እንደሚያሳየው፣ በሀገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በአዲስ አበባ እናቶች የቅድመ ወሊድ ክትትል ከማድረግ ጀምሮ የድህረ ወሊድ ክትትልን፣ ለህጻናት ጡት ማጥባትን፣ እንደ ዕድሜያቸው የሚያስፈልጋቸውን ትምህርትና የተመጣጠነ ምግብ የማግኘት ሁኔታን በተመለከተ ሰፊ ክፍተቶች ይስተዋላሉ። በተለይም የተመጣጠነና አልሚ ምግብ በአግባቡ ባለማግኘታቸው በሀገር አቀፍ ደረጃ 38 በመቶ ያህሉ ሕፃናት የመቀንጨር ችግር ያጋጠማቸው ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ደግሞ የመቀንጨር ምጣኔው 15 በመቶ ያህል እንደነበር ሰነዱ ያመለክታል፡፡

አዲስ አበባ ይህንን ስብራት ለመጠገንና ‘ቀዳማይ ልጅነትን’ በማረጋገጥ የነገዋን ኢትዮጵያ በፅኑ መሰረት ላይ ለመገንባት በቁርጠኝነት እየሰራች ትገኛለች። ይህ የከተማዋን የነገን ትውልድ ታሳቢ ያደረገውን ተነሳሽነት የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በተሞክሮነት እየወሰዱት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃም እውቅና እየተሰጠውና አድናቆት እየተቸረው ይገኛል፡፡

ከሰሞኑ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዓለም አቀፉ “አክት ፎር ኤርሊ ይርስ” (Act For Early Years) ኢኒሼቲቭ “የቅድመ ልጅነት እድገት ሻምፒዮን” ተብለው እውቅና ተሰጥቷቸዋል።




ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዓለም አቀፉ Act For Early Years ኢኒሼቲቭ “የቅድመ ልጅነት እድገት ሻምፒዮን” ተብለው እውቅና ተሰጥቷቸዋል

እውቅናው የከንቲባ አዳነች አቤቤ አመራርና የከተማ አስተዳደሩ ለሕፃናት እድገት እያደረገ ያለውን ኢንቨስትመንት በተለይም በ“የአዲስ አበባ የወደፊት ተስፋ የቅድመ ልጅነት እድገት ተነሳሽነት” የተሰጠ ነው። ኢኒሼቲቩ ቀዳማይ ልጅነትን በመንግሥታት ፖሊሲዎች እና በዓለም አቀፍ ኢንቨስትመንት አጀንዳ ማዕከል ላይ ለማስቀመጥ በትኩረት ይሰራል።

የአዲስ አበባ ከንቲባ ጽህፈት ቤት መረጃ እንደሚያመላክተው፤ እውቅናው የተሰጠው ከቀድሞው የታላቋ ብሪታኒያ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዓለም አቀፍ ትምህርት ልዩ መልዕክተኛ ጎርደን ብራውን በኩል የኢኒሼቲቭ አጋሮችን በመወከል ሲሆን፣ የተባበሩት መንግስታት የህጻናት መርጃ ፈንድ (UNICEF) እና የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና ባህል ተቋም (UNESCO)ን ጨምሮ ከተለያዩ አጋር ተቋማት ጋር በመተባበር የተሰጠ ነው። እውቅናው አዲስ አበባን በአፍሪካ የቀዳማይ ልጅነት እድገት የከተማ አመራር ተምሳሌት ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያጠናክረው ይታመናል።

**የአዲስ አበባ ጥረት፣ ያስገኘው ውጤትና እውቅና**

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሳይኮሎጂ ትምህርት ክፍል የቀዳማይ ልጅነት መምህርና ተመራማሪ ፍስሃ ተክሉ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን ሁለንተናዊ እድገት የሚሰራበት ዘመን ነው፡፡ “ልጆች ጤናማ ሆነው አድገው ለሀገራቸውና ለማህበረሰባቸው የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ከተፈለገ፣ በእድገት የእድሜ ክልላቸው ላይ ተገቢውን እንክብካቤና ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በህፃናት ላይ መስራት እድገታቸው ጤናማና የወደፊት ህይወታቸው ብሩህ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ፣ በፈጣራ የተካኑ፣ አምራችና ለሀገራቸው የሚጠቅሙ ዜጎች ሆነው እንዲወጡ ያስችላል፡፡ ዛሬ በልጆች ላይ መስራት፣ ነገ ትልቅ ፍሬ የሚያስገኝ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ነው፡፡”

> **“በህፃናት ላይ መስራት እድገታቸው ጤናማና የወደፊት ህይወታቸው ብሩህ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ፣ በፈጣራ የተካኑ፣ አምራችና ለሀገራቸው የሚጠቅሙ ዜጎች ሆነው እንዲወጡ ያስችላል”**

በቀዳማይ ልጅነት ላይ ጥናት ያደረጉት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ጀምስ ሂክማን እንደሚሉት፣ ከፅንስ ጀምሮ በህጻናት እድገት ላይ ፈሰስ የሚደረግ አንድ ዶላር ከ8 እስከ 10 ዶላር ትርፍ ያስገኛል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአካልና በአዕምሮ የበለፀገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ለመገንባት ሁሉን አቀፍ፣ የተለያዩ ሴክተሮችን የሚያሳትፍ የቀዳማይ ልጅነት እንክብካቤ ፕሮጀክት፣ “የነገ ተስፋ ህጻናት ለአዲስ አበባ!” በሚል መሪ ሀሳብ ፕሮጀክት በመንደፍ ወደ ስራ ከገባ ሰነባብቷል፡፡

የህፃናት የቀን ማቆያ ማዕከላትን የማስፋፋት ስራ ተሰርቷል፡፡ ሁለተኛው ስራ ህፃናት በጨዋታ የሚማሩባቸውንና የሚዝናኑባቸውን ስፍራዎች ማመቻቸት ሲሆን፣ ይህ የእሁድ የሰንበት ዝግ መንገድና የመጫወቻ ቦታዎች ማልማትን ይጨምራል። ሶስተኛው ደግሞ ባለሙያዎችን በመጠቀም ቤት ለቤት በሚደረግ ጉብኝትና በሸማች ማህበራት በኩል ለነፍሰ ጡሮች፣ ለሚያጠቡ እና እስከ 3 ዓመት ለሆኑ ህፃናት የሚደረግ የቀጥታ አልሚ ምግብ ድጋፍ ነው፡፡

ከተማ አስተዳደሩ አዲስ አበባን ልጆችን ለማሳደግ ምርጥ አፍሪካዊት ከተማ ለማድረግ ባቀደው የቀዳማይ ልጅነት የልማት ፕሮግራም፣ በቀጥታ አልሚ ምግብ ድጋፍ ብቻ በርካታ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል። የከተማዋ ጤና ቢሮም በሁሉም ጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች የዕድገት ክትትል ከማድረግ ባሻገር፣ ተቋማቱን ለህፃናት ምቹና ሳቢ የማድረግ እንዲሁም በሰለጠኑ ሰራተኞች አማካኝነት የወላጆች የምክርና የአቅም ግንባታ አገልግሎትን ቤት ለቤት በመስጠት የትውልድ ግንባታ ስራውን በቅንጅት እየመራው ይገኛል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቀዳማይ ልጅነት ዙሪያ የሚሰራውን ስራ በቅርበት እንደሚከታተሉና በአንዳንድ ስራዎች ላይም ተሳትፎ እንደሚያደርጉ የሚናገሩት መምህር ፍስሃ፣ በቀዳማይ ልጅነት እንክብካቤና እድገት ዙሪያ የሚሰራው ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ስራ፣ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ደረጃም አርአያ የሆነ ትልቅ ተነሳሽነት ነው፡፡

በተጨባጭም በልጆች ትምህርት፣ አያያዝ፣ በከተማዋ በተለያዩ ቦታዎች ልጆችን ያማከሉ የመጫወቻ ቦታዎችና ልጆች የሚንቀሳቀሱባቸው የጋራ መጠቀሚያ ስፍራዎች እንዲኖሩ የተሰራው ስራ አበረታችና ለወደፊቱ ጤናማና አምራች ዜጋ ለማፍራት መሰረት የሚጥል እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራሙ በአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሚመራ ሲሆን ይህም ለፕሮጀክቱ ስኬት ቁልፍ ሚና ተጫውቷል።

# መዲናዋን አዲስ መልክ ያላበሱ የልማት ስራዎች



ፎቶ ከገፀ ድር

የአዲስ አበባን ገፅታ ከቀየሩ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት በከፊል

**በስንታየሁ ምትኩ**

ከጥቂት ዓመታት በፊት የአዲስ አበባ ገጽታ የኢትዮጵያና የአፍሪካ መዲናነቷን፣ እንዲሁም የዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲ ማዕከልነቷን በፍጹም የሚመጥን አልነበረም። መንገዶቿ እግረኛን ያላማከሉ፣ ህንጻዎቿ የወየቡና የተዥጎረጎሩ፣ የመንገድ መብራቶቿም ዘመኑን የማይመጥኑ፣ የአረንጓዴ ስፍራዎቿ ሽፋን አነስተኛ፣ ወንዞቿም ተፈጥሯዊ ውበታቸውን አጥተው ወደ ቆሻሻ መጣያና መፀዳጃነት የተቀየሩ ነበሩ። እርጅና የተጫናቸውና ለመኖር ምቹ ያልሆኑ ሰፈሮችም በስፋት ይገኙ ነበር፡፡

ትውልድና እድገታቸው አራት ኪሎ የሆነው አቶ ዮሐንስ ሙሉጌታ፣ ድሮ በአካባቢው ቤቶች ያረጁ ከመሆናቸውም በላይ ግድግዳቸውና ጣሪያቸው የወየበ፣ የተዥጎረጎሩ ለዕይታ የማይስቡ ነበሩ። የአካባቢው የመንገድ መሰረተ ልማት በቂ ባለመሆኑ የትራፊክ መጨናነቅም ይታይበት ነበር፡፡

ዛሬ ግን ያ ሁሉ ታሪክ ሆኗል። በግራና በቀኝ ሶስት ሶስት መኪናዎችን በሰፊው የሚያስተናግዱ ሰፋፊ መንገዶች ተሰርተዋል። የእግረኛ መንገዶች ሰፍተው፣ ውብና ምቹ ሆነው በመሰራታቸው ነዋሪዎች ዘና ብለው በነጻነት ይንቀሳቀሳሉ። በመንገድ ዳር የተተከሉ አረንጓዴ ሳሮችና አየር የሚወሰድባቸው መናፈሻዎች የአካባቢውን ውበት በእጥፍ ጨምረውታል በማለት የአካባቢውን የበፊትና የአሁን ገፅታ እያነጻጸሩ ይናገራሉ፡፡

አቶ ዮሐንስ የኮሪደር ልማቱ የመሠረተ ልማት ግንባታ ብቻ ሳይሆን የከተማዋን የፅዳት ባህል ጭምር የለወጠ እንደሆነ ያነሳሉ፡፡ "ድሮ በየቦታው ቆሻሻ ይጣል ነበር፤ ለምሳሌ፡- በፒያሳና በተለያዩ አካባቢዎች በየመንገዱ መፀዳዳት የተለመደ ነበር፡፡ አሁን ግን በየአካባቢው ዘመናዊና ደረጃቸውን የጠበቁ መፀዳጃ ቤቶች በመገንባታቸው አካባቢው ምን ያህል ፅዱና ውብ እንደሆነ ማንኛውም ሰው በአይኑ አይቶ መመስከር ይችላል። ሰዎች ዘና ብለው ንፁህ አየር የሚያገኙበትና የሚዝናኑበት ቦታ ሆኗል።"

በአምስት ኪሎ ከብሔራዊ ሙዚየም ፊት ለፊት በሚገኘው አረንጓዴ መናፈሻ ውስጥ ህጻን ልጃቸውን ይዘው ሲዝናኑ ያገኘናቸው ወይዘሮ ጅማወርቅ ዘነበም የኮሪደር ልማቱ አዲስ አበባ ፅዱ፣ ውብና ምቹ ከተማ እንድትሆን ማስቻሉን ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ቀደም ከስራ ውጪ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበትና ልጆቻቸውን ይዘው የሚዝናኑበት በቂ ቦታ እንዳልነበረ የሚያስታውሱት ወይዘሮ ጅማወርቅ፣ አሁን ግን በኮሪደር ልማቱ አማካኝነት በሳር፣ በዕፅዋትና በተለያዩ አበቦች የተዋቡ፣ ሰው ሰራሽ ፏፏቴዎችና የልጆች መጫወቻዎች፣ የማረፊያ ወንበሮችና የሻይ ቡናና ምግብ አገልግሎት የሚሰጥባቸው መናፈሻዎች ተሰርተዋል። "ከስራ ውጪ ስንሆን ወጣ ብለን አየር ወስደን በጥሩ መንፈስ ወደ ቤታችን እንመለሳለን። ከሁሉም በላይ ደግሞ ስፍራው ደሃና ሀብታም ሳይባል ሁሉም ህብረተሰብ እኩል የሚጠቀምበት መሆኑ ልዩ ያደርገዋል" ሲሉ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ።

የከተማዋን ወንዞችን የተመለከትን እንደሆነ የቆሻሻ መጣያ ሆነው በከፍተኛ ደረጃ በመበከላቸው ፀጋ ከመሆን ይልቅ የበሽታ ምንጭና እዳ ሆነው ቆይተዋል። በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ዲዛይንና ፕላን ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል ሊሬቦ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ ከዚህ ቀደም የመዲናዋ ወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች የመጥፎ ጠረን ምንጭ በመሆናቸው ሰዎች አፍንጫቸውን ይዘው የሚያልፉባቸው ነበሩ፡፡ ምንም ጥቅም የማይሰጡ መፀዳጃና የቆሻሻ መጣያ ስፍራም ነበሩ፡፡

አሁን ግን የሚያማልሉ፣ በግራና በቀኝ ልጆች የሚጫወቱባቸው፣ የነገው ሀገር ተረካቢ ትውልድ የሚናፈስባቸውና የሚዝናናባቸው ስፍራዎች ሆነዋል። የወንዝ ዳርቻዎች ለዓይን ምግብ፣ ለአፍንጫ መልካም መዓዛ፣ ወንዞቹ ሲወርዱ የሚሰማው የፏፏቴ ድምፅና የአዕዋት ዜማ ለጆሮ የሚጣፍጥ፣ የአዕምሮ እረፍትና ሀሴት የሚደረግባቸው የውበት ማዕከል ሆነዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸምን ለከተማው ምክር ቤት ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ የኮሪደር፣ የወንዝ ዳርቻ ልማት እና የከተማ ማደስ ስራዎች ዋና ዓላማ የነዋሪዎችን አስከፊ ህይወት ማሻሻል እንዲሁም ጤናማ፣ ምቹና ንጹህ አካባቢን መፍጠር ነው፡፡ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች ያረጁና የተበላሹ በመሆናቸው፣ በአንዳንድ ሰፈሮች ደግሞ በባሰ ሁኔታ ምንም ዓይነት የፍሳሽ መስመር ባለመኖሩ ነዋሪዎች ለአስከፊ የኑሮ ሁኔታ ተዳርገው ቆይተዋል፡፡

ለነዋሪዎች ቤቶችን ገንብቶ በማስረከብ፣ ምትክ መሬት በማቅረብ፣ ካሳ በመክፈል፣ መስሪያ ሱቅ በማቅረብ አካባቢዎችን ወደ ንፁህና ውብ ስፍራነት መለወጥ መቻሉን ከንቲባዋ አክለዋል፡፡

የከተማ ዲዛይንና ፕላን ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፣ በኮሪደርና የወንዝ ዳር ልማት፣ ያረጁ አካባቢዎችን መልሶ በማደስ፣ በአረንጓዴ አሻራ የተሰሩ ስራዎች አዲስ አበባን የቱሪዝም፣ የንግድና ኢንቨስትመንት፣ መዝናኛ፣ የኮንፈረንስ ቱሪዝም መዳረሻ እያደረጓት ይገኛል፡፡ በፅዳትና በውበቷ በዓለም አቀፍ መድረኮች ተወዳዳሪ መሆን ችላለች፡፡

ቱሪዝምን ብናነሳ መዲናዋ በ2017 በጀት ዓመት ከ180 በላይ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ኮንፈረንሶችን ማስተናገድ ችላ ነበር፡፡ በተጠናቀቀው የ2018 በጀት ዓመት ደግሞ ከ221 በላይ ዓለም አቀፋዊ ኮንፈረንሶችን አስተናግዳለች፡፡

ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል (ዶ/ር) እንደሚሉት፣ አዲስ አበባ ቀደም ሲል በብዙ መልኩ ዘመናዊ ከተማ ሊያሟላቸው በሚገቡ መስፈርቶች ስትመዘን ከደረጃ በታች ነበረች። በየጽሑፎቻቸው መግቢያ ዓለም አቀፍ ደረጃን የማታሟላ ከተማ እያሉ ነበር የሚገልጿት፡፡ ባለፉት ዓመታት በኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ አረንጓዴ አሻራ በተሰሩ ስራዎች የቀድሞ ስሟ ተረት ሆኗል፡፡ ከ2010 ዓ.ም በፊት 2 ነጥብ 8 በመቶ የነበረው የከተማዋ የአረንጓዴ ሽፋን፣ በአሁኑ ወቅት ከ24 በመቶ በላይ ደርሷል፡፡ ባላት መሰረተ ልማት፣ በንጽህና እና ውበቷ የአፍሪካና የአውሮፓ መሪዎች የሚቀኑባት ከተማ ሆናለች፡፡

ከዚህ ባሻገር ከተማዋ እያስመዘገበች ያለው ለውጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እና ሽልማት እያስገኘላት እንደሆነ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል (ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡ የመዲናዋ ለውጥ በከፍተኛ የአመራሩ ብቃት እና ርብርብ መገኘቱን ታሳቢ በማድረግ ዓለም አቀፍ ተቋማት የተለያዩ ሽልማቶችን አበርክተዋል። ከሁለት ዓመት በፊትም የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የከተማዋን ነዋሪዎች ሕይወት ለማሻሻል ባሳዩት በሳል እና ቁርጠኛ አመራር በደቡብ ኮሪያ በተካሄደው የ'ሴኡል ስማርት ሲቲ 2024'

ወደ ገጽ 21 ዞሯል

> የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎች ወደ መዲናዋ የሚመጡ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች፣ የከተሞች ከንቲባዎች፣ ባለሙያዎችና የተለያዩ ዜጎች የሚጎበኟቸው፣ ልምድና ተሞክሮ የሚወስዱባቸው ሆነዋል

# ክፍት የሥራ ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ከዚህ በታች በተገለፀው ክፍት የሥራ መደብ ብቁ አመልካቾች ተቀብሎ በማወዳደር በውጤታቸው መሠረት ብልጫ ያገኙትን እጩዎች በቋሚነት ለመቅጠር ይፈልጋል።

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ደመወዝ | የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ብዛት | ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ | መደቡ የሚገኝበት የሥራ ክፍል | ለመደቡ የተፈቀደ ጥቅማ ጥቅም | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኤክስኪዩቲቭ ሴክሬታሪ I | IX | 12,566.00 | 4 | በሴክሬተሪያል ሳይንስና ኦፊስ ማኔጅመንት፣ ሴክሬታሪ ሳይንስ፣ ሴክሬተሪ አድሚኒስትሬሽን፣ ሴክሬታሪያል ማኔጅመንት፣ አድሚኒስትሬቲቭ ሴክሬታሪ፣ አድሚኒስትሬቲቭ ኦፊስ ሴክሬታሪ ቴክኖሎጂ፣ ኮምፒውተራይዝድ ሴክሬታሪ ሳይንስ ኤንድ ኦፊስ ማኔጅመንት፣ ኦፊስ ማኔጅመንት፣ ከስተመር ኮንታክት ኤንድ ሲክሬታሪያል ኦፕሬሽን፣ የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም ቴክኒክና ሙያ (10+3) ወይም ሌቭል 2፣ 3፣ 4፣ 5 ደረጃ 4 ዓመት የሥራ ልምድ ያላት/ያለው | በተቋሙ ውስጥ ባሉ ክፍት መደቦች | 800.00 የማትጊያ አበል እና የቤት አበል ድጎማ 1250.00 | |
| 2 | የመረጃ ዴስክ ሠራተኛ | VI | 8,029.00 | 2 | ዲፕሎማ፣ ኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ሲስተምና አቻ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና አቻ፣ ቢዝነስ ማኔጅመንትና አቻ፣ ስታትስቲክስ እና አቻ፣ ሴክሬተሪያል ሳይንስና አቻ ኮምፒውተር ሳይንስና አቻ 2 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው/ት | በተቋሙ | የቤት አበል ድጎማ 1250.00 | |
| 3 | ሴክሬታሪ II | VIII | 11,500.00 | 1 | በሴክሬተሪያል ሳይንስና ኦፊስ ማኔጅመንት፣ ሴክሬታሪ ሳይንስ፣ ሴክሬተሪ አድሚኒስትሬሽን፣ ሴክሬታሪያል ማኔጅመንት፣ አድሚኒስትሬቲቭ ሴክሬታሪ፣ አድሚኒስትሬቲቭ ኦፊስ ሴክሬታሪ ቴክኖሎጂ፣ ኮምፒውተራይዝድ ሴክሬታሪ ሳይንስ ኤንድ ኦፊስ ማኔጅመንት፣ ኦፊስ ማኔጅመንት፣ ከስተመር ኮንታክት ኤንድ ሲክሬታሪያል ኦፕሬሽን፣ የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም ቴክኒክና ሙያ (10+3) ወይም ሌቭል 2፣ 3፣ 4፣ 5 ደረጃ 2 ዓመት የሥራ ልምድ ያላት/ያለው | በሰው ሃብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት | 800.00 የማትጊያ አበል እና የቤት አበል ድጎማ 1250.00 | |
| 4 | ረዳት ገንዘብ ያዥ | VI | 8,029.00 | 2 | በአካውንቲግ/በሂሳብና መዝገብ አያያዝ/፣ ማኔጅመንት፣ አካውንቲንግና በጀት ስፖርት፣ አካውንቲንግና በጀት ሰርቪስ፣ አካውንቲንግና ፋይናንስ፣ አካውንቲንግ ኤንድ ኦዲቲንግ፣ በፐብሊክ ሴክተር አካውንቲግ ኤንድ ፋይናንስ የኮሌጅ ዲፕሎማ፣ ቴክኒክና ሙያ (10+3)፣ ሌቭል 3 እና 4 ሆኖ 0 ዓመት የሥራ ልምድ ያላት/ያለው | በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት | የቤት አበል ድጎማ 1250.00 | |

**ማሳሰቢያ፡-**

አመልካቾች ለምዝገባ ስትመጡ ዋናውን የትምህርት ማስረጃና የሥራ ልምድ ማስረጃ ከማይመለስ ፎቶ ኮፒ ጋር በማያያዝ ማቅረብ ይጠበቅባችኋል፡፡ አመልካቾች የብቃት ማረጋገጫ ወይም COC ይዛችሁ መምጣት ይጠበቅባችኋል፡፡

**የምዝገባ ቦታ፡-** ለም ሆቴል ኖክ ነዳጅ ማደያ ፊት ለፊት ያለው MA ህንፃ 5ኛ ፎቅ በሚገኘው የባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት የሰው ኃይል አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**የምዝገባው ጊዜ፡-** ማስታወቂያው ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 10 የስራ ቀናት ይሆናል።

**የመመዝገቢያ ሰዓት፡-** ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 2:30 እስከ ቀኑ 11:00 ድረስ ይሆናል፡፡

**የፈተና ጊዜ፡-** በውስጥ ማስታወቂያ የሚገለጽ ይሆናል፡፡

**ሴት አመልካቾች ይበረታታሉ!!**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን**

## ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር ል/ክ/ከ/ወ/10/780/ፋ/ጽ/ቤት
## የግዥው መለያ ቁጥር 01/2019 ዓ.ም

በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 አስተዳደር ጽ/ቤት በስሩ ለሚገኙ ጽ/ቤቶች ለ2019 ዓ.ም በጀትዓመት ጥቅል ግዥ ከዚህበታች በሎት የተጠቀሱት እቃዎችን በግልጽ ጨረታ ህጋዊ አቅራቢዎችን አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ አቅራቢዎች መሳተፍ ይችላሉ፡፡

**የሎት ምድብ** — **የጨረታማስከበሪያ CPO**

ሎት.1. የጽ/መሳሪያ ግዥ ______________________________ 20000.00
ሎት.2. የጽዳት እቃዎች ግዥ____________________________ 20000.00
ሎት.3. የደንብ ልብስ ግዥ ____________________________ 20000.00
ሎት.4. ደንብ ልብስ ስፌት ______________________________ 10000.00
ሎት.5. ኤሌክትሮኒክስ ጥገና ____________________________ 5000.00
ሎት.6. ፈርኒቸር ጥገና _________________________________ 5000.00
ሎት.7. ህትመት ስራ ግዥ ______________________________ 8000.00
ሎት.8. መስተግዶ የታሸገ፤ ውሀ ለስላሳ መጠጦች፤ ቡና ሴሬሞኒ፤ ሻይ አቅራቢ ____ 5000.00
ሎት.9. ሞታርቦና ዲጀ ኪራይ ___________________________ 10000.00
ሎት.10. የዲኮር እቃ ኪራይ ____________________________ 10000.00
ሎት.11. የቄብ ዶሮ እንቁላል ጣይና የአትክልት ዘር ግዥ _____10000.00
ሎት.12. ኤሌክትሮኒክስ እቃ ግዥ______________________15000.00
ሎት.13. መለስተኛ የህዝብ ማመላለ 26 ሰው የሚጪን መኪና ኪራይ (እለታዊ) _______10000.00

**በዚሁም መሰረት፡-**

1. በጨረታው ለመወዳደርፍ ላጎት ያላቸው ተጫራቾች 2019 ዓ.ም የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላችህ የዘመኑን ግብር የከፈሉ በመንግስት ግ/ን/እ/ኤጀንሲ ድህረ ገጽ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ ህጋዊ የቲንነበር እና የቫት፤ ከሪላስ ያላችሁ ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. ጥቃቅንና አንስተኛ ተጫራቾች ካደራጃቸው ባለስልጣን ደብዳቤ የሚያመጡት የጨረታ ሰነድ በነጻ መውሰድና 3% ቅናሽ የሚደረግላቸው እራሳቸው ላመረቱት እቃና ቫሊው አድ ላደረጉት እቃ ብቻ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ/CPO ብቻ ቢል ቦንድ እና ቼክ አንቀበልም ከጨረታ ሰነዶች ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት እለት አንስቶ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት ውስጥ የማይመለስ ብር 400.00/አራት መቶ ብር ብቻ/ በመክፈል በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ፋ/ጽ/ቤት ቢሮ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 104 በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
5. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በታሸገ ኢንቨሎፕ ማስታወቂያ ከወጣበት እለት አንስቶ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት በወረዳ 10 ፋ/ጽ/ቤት የመንግስት ግዥ ቡድን ቢሮ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
6. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት 10ኛው ቀን 11፡30 ጨረታው ያልቃል፡፡ አልቆ የሚታሸግ ሲሆን በ11ኛው ቀን 2፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡ በወረዳ 10 ፋ/ጽ/ቤት የመንግስት ግዥ ቡድን ቢሮ ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ታሽጎ ይከፈታል፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩበት ሎት የተሟላ የፍላጎት መግለጫ እና ሳንፕል ማዘጋጀትና ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
8. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ለእያንዳንዱ ዋጋ ከቫት ጋር ጠቅላላ ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
9. የዘገ የጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
10. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቻውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈጻሚው መስሪያ ቤት ደረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
11. ለጨረታ ከቀረቡት እቃዎች ዝርዝር ውስጥ ጽ/ቤት እስከ 20% ጨምሮ ወይም ቀንሶ የመግዛት መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡
12. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ ማብራሪያና ጥያቄ ካለዎት፡- ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ፋ/ጽ/ቤት በስልክ ቁጥር 0115574351 በመደወል ወይምቅ/ልደታ ቤ/ክጀርባ አዲስ አበባ ፎምና ፕላስቲክ ፋብሪካ አጠገብ ቢሮአችን በአካል በመቅረብ መጠየቅ ይችላሉ።**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልደታ ክ/ከተማ የወረዳ10 ፋይናንስ ጽ/ቤት**

---

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/03 ብሎክ 12 ፓርሴል 12 የህንጻ ቁጥር 2 የቤት ቁጥር B3/87 በካርታ ቁጥር CKS 10162/መ/ፍ/87 በሴሪ ቁጥር 008108 በአሰገደች ሰይድ አየለ ስም የሚገኘው የጋራ ህንጻ የቤት ባለሀብትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይገፔዋለሁ የሚል ካለ በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ይዞ እንዲቀርብ እየጠየቅን ይገፔዋለሁ የሚል ከሌለ በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቂርቆስ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የኪነ ጥበብ መሰናዶዎች

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የመጽሐፍ ምርቃት፣ የእደ ጥበብ እና የስዕል አውደ ርዕይ፣ የሃሳብ ውይይት እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡



ፎቶ ፡- ከገፀ ድር
ከመዲናዋ የጥበብ መሰናዶዎች በከፊል

## የዕደ ጥበባት አውደ ርዕይ

የአዲስ አበባ ባህል እና ኪነ ጥበብ ቢሮ ያዘጋጀው የዕደ ጥበባት አውደ ርዕይ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በትናንትናው ዕለት የተከፈተው ይህ አውደ ርዕይ በመገናኛ የካ ክፍለ ከተማ፣ በሜክሲኮ ታክሲ ተራ፣ በአዲሱ ገበያ ጃንቦ ህንፃ እና በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ግቢ ውስጥ በርካታ የስራ ኃላፊዎችና የዘርፉ ባለሙያዎች በተገኙበት በድምቀት እየተካሄደ ይገኛል፡፡ አውደ ርዕይው እስከ ጳጉሜን 5 ቀን 2018 ዓ.ም ይቆያል።

## መጽሐፍት

"የእናቴ 'ሮሚዮ' እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች" የተሰኘው መጽሐፍ ዛሬ ይመረቃል፡፡ በደራሲና ጋዜጠኛ ስመኝ ግዛው የተጻፈው ይህ መጽሐፍ ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም አዳራሽ ይመረቃል፡፡ በምርቃቱ ላይ ወጣትና አንጋፋ ደራሲያን የሚገኙ ሲሆን የቴአትር ባለሙያዎች ከመጽሐፉ የተመረጡ ታሪኮችን በትወና መልክ ለታዳሚያን እንደሚያርቀቡ ተገልጿል፡፡

በሌላ መረጃ "The Awakening Bell for Africans" የተሰኘ አዲስ መፅሐፍ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ተመርቆ ለንባብ በቃ፡፡ በአቶ በቀለ ፉፋ የተፃፈው ይህ መፅሐፍ የአውሮፓ እና የአፍሪካን የእድገት ልዩነት በመተንተን በውጪ የሚገኙ የአፍሪካ መሪዎች፣ ዳያስፖራዎች እና ምሁራን ወደ ሀገራቸው በመመለስ ለአፍሪካ እድገት በአንድነት መስራት እንዳለባቸው የሚያሳስብ ይዘት ያለው ነው፡፡ ይህ የመጽሐፍ ምርቃት የፓን አፍሪካኒዝም መሰረት በሆነው የዓድዋ ድል መታሰቢያ መካሄዱ፤ መታሰቢያው ከቆመለት ታሪካዊ ዓላማ ጋር የሚጣጣም እና ፋይዳው የጎላ መሆኑን ለማመላከት መሆኑን ደራሲው በምርቃቱ ወቅት ተናግረዋል፡፡

## የስነ ጥበብ አውደ ርዕይ

"ፍቅር እስከ መቃብር" በስዕል የተሰኘ አውደ ርዕይ በእይታ ላይ ይገኛል። የሰዓሊ ነጋልኝ ሉሌ የስዕል ስራዎች የቀረቡበት ይህ አውደ ርዕይ እስከ መስከረም 11 ቀን 2019 ዓ.ም እንደሚቆይ ተገልጿል፡፡ አውደ ርዕይው እየታየ የሚገኘው ሃያት ሪጅንሲ ሆል በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል ሲሆን መግቢያው በቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን በኩል በሚገኘው በር ነው፡፡

በሌላ መረጃ በሐመረ ብርሃን የብራና መጻሕፍት ሥራ ድርጅት የተዘጋጀው እና ሐሙስ ዕለት የተጀመረው "የምድር ጌጥ ኢትዮጵያ" የተሠኘ ዐውደ ርዕይ እስከ መስከረም 3 ቀን 2019 ዓ.ም ድረስ በሆላንድ ፓርክ ይካሄዳል።

## የሐሳብ ውይይት

ሳይንሳዊ የውይይትና የሐሳብ መድረክ በዛሬው ዕለት ይደረጋል። የውይይቱ ርዕስ "ማይንድ ማፒንግ" (Mind Mapping) ሲሆን ለጥናት ሐሳብን ማደራጀት እንዴት ይቻላል? በሚል ርዕስ ላይ ያተኮረ የውይይትና የእውቀት ልውውጥ ፕሮግራም ነው፡፡ በዕለቱም ስለ ማይንድ ማፒንግ፣ ለጥናት ያለው ጥቅም፣ ሐሳብን በተደራጀ መልኩ ለማስቀመጥና ለማስታወስ የሚረዳበትን መንገድ በጥላሁን ተስፋዬ (ዶ/ር) መነሻ ጹሑፍ ቀርቦ ከታዳሚያን ጋር ውይይት ይደረግበታል ተብሏል፡፡ መርሃ ግብሩ ዛሬ ከቀኑ 8:30 ሰዓት ጀምሮ ዋልያ መጻሕፍት፣ አራት ኪሎ፣ ቱሪስት ሆቴል ዝቅ ብሎ ይካሄዳል፡፡

## የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሑድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ በብሔራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 7፡30 ሰዓት "12ቱ እንግዶች" እንዲሁም በ11:30 ሰዓት "በር የሌለው ቤት" ይታያሉ። በዚሁ ቴአትር ቤት እሁድ በ7፡30 ሰዓት "ንጉስ አርማሕ" እንዲሁም በ11፡30 ሰዓት "እምዬ ብረቷ" ይታያሉ፡፡ ተመልካቾችም ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ"ሁሉ በጄ" መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ ደግሞ "እሳት ወይ አበባ" ዘወትር ቅዳሜ በ11፡00 ሰዓት እንዲሁም "ባልቻ አባነፍሶ" እሁድ በ8:00 ሰዓት የሚታዩ ሲሆን ትኬቱን በኦንላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

ቦሌ ፍላሚንጎ በህፃናትና ወጣቶች የቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስ እሁድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት "የንባብ ከተማ" የተሰኘው አዲስ የልጆች ቴአትር ለእይታ ይበቃል፡፡ እሑድ በ8፡00 ሰዓት "ወህኒ አምባ" እንዲሁም 11፡30 ሰዓት "አትጥሪኝ" የተሰኙ ቴአትሮች ለተመልካች ይደርሳሉ፡፡

እንዲሁም በሀገር ፍቅር ቴአትር ረቡዕ በ11፡00 ሰዓት "አሉ" የተሰኘው አዲስ ቴአትር፣ ሐሙስ 11፡30 ሰዓት "ነገሩ አይቆምም፣ እሑድ በ8፡00 ሰዓት "ሰዴታ" (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12፡00 ሰዓት "የመጨረሻው ፍርድ" ለጥበብ አፍቃሪያን ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው ወደ ታች 4 + 5 + 7 + 4 + 5 = 25 ነው፡፡ ሁለተኛው ከላይ ወደ ጎን 4 + 8 + 3 + 2 + 8 = 25 ነው፡፡ በዚህ አመክንዮ መሰረት የመጨረሻው ወደ ታች 8 + 2 + 3 + 3 + 9 = 25 ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ የሚገባው ትክክለኛ ቁጥር 9 ነው፡፡




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ከጥበብ ጓዳ የሚቀዳ በጎነት

**በጊዜው አማረ**

በጎነት የሰው ልጅ ከፍ ያለ ሞራላዊና መንፈሳዊ እሴት ሲሆን፣ ያለምንም የራስ ወዳድነት ቅድመ ሁኔታ ለሌሎች መልካም ማሰብና ማድረግ ነው። የሰውን ልብ የሚያነጻ፣ ማህበረሰብን የሚያስተሳስር እና ሰላምን የሚያሰፍን ታላቅ ሃይል ነው። በቃል የሚገለጽ ብቻ ሳይሆን፣ በተግባር የሚታይ የርህራሄ፣ የይቅርታ፣ የእርዳታ እና የአብሮነት መገለጫም ነው።

በእለት ተእለት ማህበራዊ ሕይወታችን ውስጥ በጎነት የጋራ መተሳሰብ ማዕዘን ነው። በችግር ጊዜ ለወገን መድረስ፣ አቅመ ደካሞችን መርዳት የጤናማ ማህበረሰብ መሰረት ነው። በጎነት ሲኖር በሰዎች መካከል መተማመን ይሰፍናል፤ ጥላቻና መከፋፈል ይወገዳል። መከባበርና መተሳሰብ ከፍ ይላል፡፡ አንድ ማህበረሰብ በበጎ አድራጊ ልቦች ሲታነጽ፣ የችግሮች ክብደት ይቀንሳል፤ የደስታና የሰላም አድማስም ይሰፋል።

ይህን መነሻ በማድረግ ዓለም አቀፍ የበጎነት ቀን በየዓመቱ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ነሃሴ 30 (በፈረንጆች መስከረም 5) ይከበራል፡፡ ይህ ቀን የተመረጠበት ዋና ምክንያት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰላም መልእክተኛ የሆኑት እና በህንድ ለድሆችና ለተቸገሩት ብዙ ያደረጉት ማዘር ትሬዛ ያረፉበት ቀን በመሆኑ ነው። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ. በ2012 ባስተላለፈው ውሳኔ መሰረት ቀኑ በዓለም ዙሪያ ያሉ ህዝቦች የበጎ አድራጎት ስራዎችን እንዲያከናውኑ እና ለሰብአዊነት ያላቸውን ቁርጠኝነት እንዲያሳዩ ትልቅ እድል ፈጥሯል።

የዚህ ቀን ዋና አላማ ድህነትን ለመቀነስ፣ ማህበራዊ ፍትህን ለማስፈን እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰብአዊ ድጋፍን ባህል ማዳበር ነው። “በጎነት በጦርነት፣ በረሃብ፣ በበሽታ እና በተፈጥሮ አደጋዎች ለተጎዱ ሚሊዮኖች የተስፋ ብርሃን ነው” የሚለው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ቀኑ ርህራሄን፣ መረዳዳትን እና ህብረትን የምናስታውስበት እና በተግባር የምናሳይበት ልዩ ቀን ነው በማለት ያክላል። በየዓመቱ በሚከበርበት ወቅት የተለያዩ የበጎ አድራጎት ስራዎች፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮች እና የገቢ ማሰባሰቢያዎች ይካሄዳሉ። ይህ ቀን እያንዳንዱ ግለሰብ በትንሽም ቢሆን ለሌሎች ህይወት መሻሻል የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት እንደሚችል በማስታወስ፣ የመረዳዳት እና የፍቅር እሴቶች በምድር ላይ እንዲስፋፉ ጉልህ ድርሻ ይጫወታል ተብሎ ይታመናል።

በጎነት በምድር ላይ እንዲስፋፋ፣ እሴትና ባህል እንዲሆን ትልቅ አበርክቶ ከሚያደርጉ ነገሮች ውስጥ ደግሞ ኪነ ጥበብ አንዱ ነው፡፡ “ኪነ ጥበብ



ፎቶ ፦ ኤ አይ ቻት ጂፒቲ
በበጎ አድራጎት ስራዎች ላይ ኪነ ጥበብ የበኩሉን አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛል

በሰው ልጆች ህይወት ውስጥ በጎነትን ለማስተማር እና ለማስፋፋት፣ ገቢ ለማሰባሰብ አይተኬ ድርሻ ተጫውቷል፤ እየተጫወተም ይገኛል” ይላል የሀበሻ ኳየር መስራች እና ሙዚቀኛ ቢተው ዳዊት፡፡

በተለይ ደግሞ ሙዚቃ የሰውን ልጅ ልብ በቀጥታ የሚነካ እንደሆነ የሚናገረው ባለሙያው፣ ሃሳብን በስዕል፣ በግጥም፣ በሙዚቃና በድራማ መልክ የማስተላለፍ እምቅ አቅም ያለው ዘርፍ ነው በማለት ያክላል፡፡

በጎነትን በማህበረሰቡ ውስጥ ለማስረጽና ለማስፋፋት በሚደረጉ ጥረቶች ኪነ-ጥበብ የሚጫወተው ሚና የላቀ ነው። ሰዓሊያን፣ ቀራጺያን፣ ገጣሚዎች እና ሙዚቀኞች ባላቸው ልዩ ተሰጥኦ የመረዳዳትና የበጎነትን አስፈላጊነት በስራዎቻቸው ሲገልጹ፣ የህብረተሰቡን ህሊና በማነሳሳት ለበጎ አድራጎት ስራዎች ትልቅ መነሳሳትን ይፈጥራሉ። እሱባለው ይታየው፣ ሳሚ ዳን፣ ቤቲ ጂ እና ዳዊት ጽጌ በጋራ ለበጎ አድራጎትና በጎ አድራጎትን ለማበረታታት በሰሩት ሙዚቃ፡-

ዳሩ ምንድ ነው የህይወት ውሉ
መኖር ካልቻለ አንዱ ለሁሉ
ጥንትም ከድሮ የመጣ እውነት
መተባበር ነው የኛ ማንነት… በማለት

የገለጹትም የዚህ ማሳያ መሆኑን ባለሙያው ይገልጻል፡፡

በአገር አቀፍም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በጎነትን ለማስፋፋት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የገቢ ማሰባሰቢያ መርሃ ግብሮች ዋነኛ አካል ናቸው። የሙዚቃ ኮንሰርቶች፣ የቴአትር ትርኢቶች እና የስዕል ኤግዚቢሽኖች ለሰብአዊ ዓላማዎች ሀብት ለማሰባሰብ እንደ ትልቅ ድልድይ ያገለግላሉ። ህዝቡ ኪነ-ጥበብን እየተመለከተና እየተዝናና፣ በተመሳሳይ ጊዜ ለተቸገሩ ወገኖች ድጋፍ የሚያደርግበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። በዚህም አማካኝነት ጥበብ ለበጎ አድራጎት ሥራዎች የፋይናንስ ምንጭ በመሆን ዘላቂ ለውጥ ያመጣል በማለት ቢተው ዳዊት ያብራራል።

ለአብነትም፡- ከሁለት ዓመት በፊት ከሸማ የስዕል ኤግዚቢሽን ጋር በመተባበር የስዕል ዓውደ-ርዕይ ለዕይታ ክፍት ሆኖ ነበር፡፡ በዓውደ-ርዕዩ መክፈቻ ላይ ጳጉሜ ተውኔት አያልነህ ሙላቱን ጨምሮ አንጋፋ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችና በአዲስ አበባ ያሉ የውጭ ሀገራት አምባሳደሮች ተገኝተውበታል፡፡ ከዚሁ ጋር ገቢው ሙሉ በሙሉ ለመቄዶኒያ የአረጋዊያንና የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል የሚሆን የመጽሐፍ ምርቃት ፕሮግራም ተከናውኗል፡፡ መጽሐፉ በወቅቱ የቺሊ አምባሳደር ሮድሪጎ ጉዝማን ባሮስ የተጻፈ ነው፡፡ ይህ ሁነት ጥበብ ለበጎነት ያለውን ፋይዳ እንዲሁም በጎነት ድንበርና ሀገር እንደሌለው ያስተማረ ክስተትም ነበር፡፡

በእርግጥ በሀገራችን ኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ለበጎ አላማ፣ ለእርዳታ፣ ለድጋፍ፣ ለማስተማርና እያዝናኑ ገቢ ለማስገኘት በተለያየ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የኢትዮጵያ ኪነ-ጥበብ ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ከማህበራዊ ሕይወት ጋር የተጣመረ፣ ለችግር ጊዜ ደራሽ እና የሕዝብ ድምፅ ሆኖ ኖሯል። አርቲስቶች፣ ገጣሚዎች፣ ተዋናዮች እና ሙዚቀኞች በኪነ-ጥበብ ስራዎቻቸው አማካኝነት ለተቸገሩ ወገኖች ድጋፍ ለማሰባሰብ፣ ህብረተሰቡን ለማንቃት እና ትምህርት ለመስጠት ግንባር ቀደም ሚና ተጫውተዋል። በተለይም በልማት፣ በድርቅ፣ ሰው ሲታመም፣ እንደ መቄዶኒያ ያሉ ተቋማትን ለማገዝ የጥበብ ሰዎች የሚያዘጋጇቸው መርሃ ግብሮች ብዙዎች ሕይወት ዘንድ ትልቅ ፋይዳ ነበራቸው። አሁንም ይህ ተግባር ቀጥሏል፡፡

ለአብነት፡- ባሳለፍነው ዓመት አርቲስት ቅድስት ይልማ “ጀስቲሲያ” የተሰኘውን ፊልሟን በአሜሪካ የተለያዩ ግዛቶች ተዘዋውራ በማሳየት የተገኘውን ገቢ ለበጎ አድራጎት ለግሳለች፡፡ በሀገራችን ታሪክ ውስጥ በርካታ የበጎ አድራጎት የሙዚቃ ኮንሰርቶች፣ የቴአትር ትርኢቶች እና የስዕል ኤግዚቢሽኖች ተካሂደዋል። በእነዚህ መርሃ ግብሮች የተገኘው ገቢ ሙሉ በሙሉ ለችግረኞች፣ ለአቅመ ደካማ አረጋውያን፣ ወላጅ ለሌላቸው ህጻናት እና ለተፈጥሮ አደጋ ተጎጂዎች ማከፋፈያ ውሏል። ሕዝቡም ኪነ-ጥበብን እየተመለከተ እና እየተዝናና የድርሻውን የሰብአዊነት ኃላፊነት እንዲወጣ ታላቅ ድልድይ ሆኖ አገልግሏል። ይህ አሠራር የኢትዮጵያውያንን የመከባበር እና የመረዳዳት ባህል በኪነ-ጥበብ ሃይል ይበልጥ እንዲጎለብት አድርጓል።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ ኪነ-ጥበብ ማህበራዊ ችግሮችን በመከላከል እና ትምህርት በመስጠት ረገድ የማይተካ ሚና አለው። የድሮም ሆነ የዘመኑ የቴአትር እና የሙዚቃ ስራዎች የሰውን ልብ በመንካት ስለ ሰላም፣ ስለ ፍቅር፣ ስለ አንድነት እና ስለ በጎነት ይሰብካሉ። በስነ-ጽሑፍ እና በፊልም መስክ የሚታዩት አበረታች ስራዎች ሰዎች ስለ ማህበራዊ ኃላፊነት እንዲያስቡ እና የበጎ አድራጎት ሥራዎችን በባለቤትነት እንዲሰሩ ከፍተኛ ግንዛቤ ፈጥረዋል።

የዘርፉ ባለሙያ ቢተው ዳዊት እንደገለጸው፣ ኪነ ጥበብ ሌሎችን የማስተማር፣ የማነቃቃትና የማስተባበር አቅም ጥልቅና በልኩ ያልተነገረለት እንዲሁም ገና ያልተሰራበት ትልቅ ሃይል ነው፡፡ ይህን ሃይል ደግሞ ለበጎ አድራጎት ስራዎች፣ ለልማት፣ ለመተጋገዝና በጎ ለሆኑ ጉዳዮች መጠቀም ይቻላል፡፡

መተዛዘን ቢኖር መረዳዳት ቢኖር
መተሳሰብ ቢኖር ሁሉም ቢተባበር
ሰው ለሰው ቢፋቀር ሁሉም ቢተባበር
የት ይደረስ ነበር… የሚለው የንዋይ

ደበበ፣ አረጋሃኝ ወራሽ እና ፀጋዬ እሸቱ የጥበብ አበርክቶ ሌላኛው የሀገራችን የበጎ አድራጎትና የኪነ ጥበብ ቁርኝትን የሚያሳይ ስራ ነው፡፡

ዓለም አቀፍ ልምዶችና ተሞክሮዎች የሚያሳዩትም የኪነ ጥበብና በጎ አድራጎት ትስስር ጥብቅ መሆኑን ነ። ሉዊ ሚካኤል ሼክትማን እ.ኤ.አ. በ2023 ያሳተሙት “Philanthropy in art: locality, donor retention, and prestige” የተሰኘ

ወደ ገጽ 21 ዞሯል

ኢኮኖሚ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# በከተማ ግብርና ውጤታማነት የተቋማት ሚና እስከምን?

• በአዲስ አበባ ከተማ 2 ሺህ 776 የመንግስትና የግል ተቋማት የተቀናጀ እና ዘመናዊ የከተማ ግብርና ስራ በመስራት ላይ እንደሚገኙ ተመላክቷል

**በይግለጡ ጓዴ**

በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በሀገራችን በከተሞች የሚስተዋለው ፈጣን የህዝብ ቁጥር መጨመር እና የምግብ ፍላጎት እድገት፣ አዳዲስ እና ዘላቂ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን መከተልን ግድ ብሏል። ከእነዚህ መፍትሔዎች መካከል በዋናነት እየተጠቀሰ የሚገኘውና በከተሞች ውስጥ አዲስ ተስፋና እንቅስቃሴ የፈጠረው ተቋማዊ የከተማ ግብርና ነው። ይህ በየተቋማቱ ግቢዎች፣ ክፍት ቦታዎች እና ህንጻዎች ላይ የሚከናወን የከተማ ግብርና ስራ፣ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባለፈ ለከተሞች ውበት፣ ለአየር ንብረት መስተካከል እንዲሁም ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዘላቂነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል።

ተቋማዊ የከተማ ግብርና ሲባል የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የግል ድርጅቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ ፋብሪካዎች እና ሌሎች ማህበራዊ ተቋማት የሚገኙባቸውን ክፍት ቦታዎች፣ የጣሪያ ላይ መሬቶች እና በረንዳዎችን በመጠቀም የሚከናወን የተቀናጀ የግብርና ስራ ነው። እንቅስቃሴው የጓሮ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ የእንስሳት ማድለብ፣ የዶሮ፣ የወተት እና የንብ እርባታን ያካተተ ነው።

ይህ አሰራር ተቋማቱ ለሰራተኞቻቸውና ለአገልግሎት ጠያቂዎቻቸው ጤናማ፣ ትኩስ እና ተፈጥሯዊ (ኦርጋኒክ) ምርቶችን በካፌዎቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያስችላቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም የከተማዋን የስራ አጥነት ቁጥር ለመቀነስ፣ የምግብ ወጪን ለመቆጠብ፣ አነስተኛ ደመወዝ ላላቸው ሰራተኞች ተጨማሪ ገቢ ለመፍጠር እና የከተሞችን የአካባቢ ጥበቃ ለማሻሻል ትልቅ እገዛ እያደረገ ይገኛል።

በአዲስ አበባ ከተማ ተቋማትን የከተማ ግብርና ምርት ማዕከል አድርጎ ከማስቀጠል አንፃር በርካታ ውጤታማ ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሆነ ከከተማዋ አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ። በተለይም የጤና ጣቢያዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች እና የፌዴራል ተቋማት ግንባር ቀደም የምርት ማዕከል እየሆኑ መጥተዋል።

በከተማዋ የተለያዩ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ ተቋማት ለዚህ እንቅስቃሴ አርአያ የሚሆኑ ተግባራትን እያከናወኑ



ፎቶ፦ ከገጸ ድር

በአዲስ አበባ ከተማ በተቋማት ውስጥ እየተከናወኑ ከሚገኙ የከተማ ግብርና ስራዎች ከፊሎቹ

ይገኛሉ፡፡ ተቋማት ያላቸውን ሰፊ ቦታ፣ የህንፃዎች ጣራ ወይም ክፍት መሬትን በመጠቀም የተለያዩ የግብርና ሥራዎችን ማከናወን እንደሚችሉ በተግባር እየታየ ነው። ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ስር የሚገኘው የመጋላ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፣ ተቋሙ እያከናወነ ከሚገኘው የመማር ማስተማር ስራ ጎን ለጎን በትምህርት ቤቱ የከተማ ግብርና ስራን በከፍተኛ ሁኔታ አጠናክሮ በመቀጠል ላይ ይገኛል።

የመጋላ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር መምህር ኃይለማሪያም ክንዴ እንደገለጹት፣ ትምህርት ቤቱ ከተቋቋመበት ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ የከተማ ግብርና ስራ በሙከራ ደረጃ ላይ የነበረ ቢሆንም፣ በተደራጀ አቅም በመምህራን፣ በተማሪዎችና በአስተዳደር ሰራተኞች በስፋት መተግበር የተጀመረው ግን ካለፈው ዓመት ወዲህ ነው፡፡

ትምህርት ቤቱ በቅጥር ግቢው ውስጥ በሚገኝ 2 ሺህ ካሬ ሜትር ባዶ ቦታ ላይ ቀይ ስር፣ ጎመን፣ ድንችና ጤፍ በማምረት የትምህርት ቤቱን ገቢ እያሳደገ ይገኛል። በዚህ ዓመት የጤፍ ምርት ከተሰበሰበ በኋላ፣ ወዲያውኑ ጥቅል ጎመን በመትከል ምርቱን ለገበያ ማሰራጨት ችለዋል። እንደ ርዕሰ መምህሩ ገለጻ፣ “መሬት ጾም ማደር የለበትም” የሚል ፅኑ አቋም በመያዝ በዓመት ሁለት ጊዜ የተለያዩ የጓሮ አትክልት እና የሰብል ምርቶችን እያመረቱ ነው።

በትምህርት ቤቱ ለጓሮ አትክልት ልማት የገጸ-ምድርና የከርሰ-ምድር ውሃን ጥቅም ላይ እያዋሉ መሆናቸውን የጠቀሱት ርዕሰ መምህሩ፣ የክፍለ ከተማውና የወረዳው የከተማ ግብርና ጽህፈት ቤቶች የሙያ፣ የግብዓት እና የምርጥ ዘር ድጋፎችን እንደሚያደርጉላቸው ተናግረዋል። በዚህ ዓመት ስድስት መኪና ሙሉ ጥቅል ጎመን እና 10 ኩንታል ጤፍ አምርተው ለገበያ አቅርበዋል። አንድ መኪና ጥቅል ጎመን በ120 ሺህ ብር ሂሳብ በመሸጥ ከስድስት መኪና ጥቅል ጎመን ሽያጭ ብቻ 720 ሺህ ብር ገቢ አግኝተዋል። ይህ ጥቅል ጎመን ለአካባቢው ማህበረሰብ፣ ለትምህርት ቤቱ መምህራንና ለአስተዳደር ሰራተኞች ተደራሽ ሆኗል። ትምህርት ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ ሲያመርት ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ የሚያገኝ ሲሆን፣ ገቢው ለችግረኛ ተማሪዎች ምገባና ለትምህርት ቤት ግብዓት ማሟያ ይውላል።

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጌታቸው ሀብተማርያም እንደገለጹት፣ በወረዳው በሚገኙ የመንግስት የጤና እና የትምህርት ተቋማት የከተማ ግብርና በትኩረት እየተሰራ ነው። ለምሳሌ ኮልፌ ጤና ጣቢያ በእፅዋትና በዶሮ እርባታ፣ ሎሚ ሜዳ ጤና ጣቢያ በእፅዋት ልማት እና በዶሮ እርባታ ተደራጅተው እየሰሩ ሲሆን፣ ሚሊኒየም ትምህርት ቤት ደግሞ በእፅዋት እና በእንስሳት ዘርፍ በተቀናጀ መንገድ ምርት በማመርት ላይ ይገኛሉ።

በየካ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት የእጽዋት ሀብት ቡድን መሪ አቶ ተሾመ ካቡ እንደተናገሩት፣ በክፍለ ከተማው 214 ተቋማት በከተማ ግብርና ስራ ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ። እነዚህም የትምህርት፣ የጤና፣ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የፌዴራልና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም እድሮች ናቸው። በተለይም የደጃዝማች ወንድራድ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከትምህርት ጎን ለጎን በጓሮ አትክልት ልማት፣ በዶሮ እርባታ፣ በከብት ማድለብ፣ በወተት እና በንብ እርባታ ዘርፍ የተቀናጀ የከተማ ግብርናን በጥራት በመተግበር ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

በተመሳሳይ የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የእንስሳት ዘርፍ ቡድን መሪ አቶ ሃብታሙ ቃበታ እንዳረጋገጡት፣ 60 ተቋማት በእንስሳት እና በእጽዋት ልማት ተሳትፎ የሚያደርጉ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 27ቱ አዲስ የተቀላቀሉ ናቸው። ከእነዚህም መካከል ወረዳ 1 አቡነ ባሴሊዎስ፣ ወረዳ 4 አየር ጤና ትምህርት ቤት፣ ወረዳ 6 የማነብርሃን ትምህርት ቤት፣ ወረዳ 11 ረጲ ጃፓን ትምህርት ቤት እንዲሁም ኪያ፣ አዲስ አለም፣ አጃንባ እና እመብዙሃን ትምህርት ቤቶች ይገኙበታል።

በተጨማሪም ተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከል፣ ዩኒየን ሸማቾች እና ጅማበር መናሐሪያ አዲስ ከተቀላቀሉት መካከል ናቸው። በወረዳ 1 የሚገኘው የአለርት ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልም በውስጡ የከብት፣ የዶሮ፣ የንብ እርባታ እና የእፅዋት ልማት ስራዎችን በስፋት እያከናወነ ይገኛል።

በአዲስ አበባ ከተማ አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንደወሰን አካሌ እንደገለጹት፣ የከተማ ግብርናን በማስፋፋት፣ በማጠናከር እና በማዘመን በከተማዋ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተከናወኑ ስራዎች ከፍተኛ ውጤት አምጥተዋል።

በአሁኑ ወቅት 2 ሺህ 776 የመንግስትና የግል ተቋማት የተቀናጀ እና ዘመናዊ የከተማ ግብርና ስራ በመስራት ላይ ይገኛሉ፤ ይህም ተቋማቱ የምርት ማዕከል እንዲሆኑ፣ ለሰራተኞቻቸው ምርት እንዲያቀርቡ፣ ማዕድ እንዲያጋሩ እና አነስተኛ ገቢ ያላቸው ሰራተኞቻቸውን እንዲደግፉ አድርጓቸዋል።

ከለውጡ ማግስት ጀምሮ የከተማ ግብርና ስራ በከተማዋ ነዋሪዎች ዘንድ አዎንታዊ የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ አስችሏል። በቤተሰብ እና በተቋማት ደረጃ በተከናወኑ የከተማ ግብርና ስራዎች በ2012 በጀት ዓመት 157 ሺህ 502 የነበረው ተጠቃሚ ቁጥር በአሁኑ ሰዓት ወደ 1 ሚሊዮን 283 ሺህ 537 አድጓል። በእንስሳትና በሰብል ልማት ዘርፍ በ2012 በጀት ዓመት 64 ሺህ 600 ቶን የነበረው ዓመታዊ ጠቅላላ የምርት መጠን፣ በአሁኑ ወቅት በዓመት ወደ 615 ሺህ 108 ነጥብ 3 ቶን ከፍ ብሏል።

ለዚህ ስኬት መረጋገጥ በሌማት ትሩፋት ንቅናቄ አማካኝነት የተሰበሰበው ሀብት እና በመንግስት የተመደበው በጀት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። በዚሁ በጀት ዓመት ብቻ 22 ክላስተሮች፣ 6 ግሪንሃውሶች፣ 8 የመኖ ማቀነባበሪያዎች እና 107 የግብርና መሸጫ ሱቆች ተገንብተው ለአገልግሎት መብቃታቸውን ዳይሬክተሩ አብራርተዋል፡፡

ተቋማዊ የከተማ ግብርና ያስመዘገበው ውጤት የሚያበረታታ ቢሆንም፣ እንቅስቃሴው ይበልጥ ውጤታማ እና ዘላቂ እንዲሆን የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫዎች ሊኖሩት ይገባል። በመጀመሪያ ደረጃ፣ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን (እንደ ሃይድሮፖኒክስ እና የከተማ ዘመናዊ መስኖ) ማሳደግ አስፈላጊ ነው። በሁለተኛ ደረጃ፣ የተቋማትን አመራሮች እና ሰራተኞች ቁርጠኝነት የበለጠ ማጠናከርና ቀጣይነት ያለው የባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ ማቅረብ ይገባል።

የጠዋት ፀሐይ

# የመዲናዋ የመዝናኛ አማራጮች በልጆች አንደበት

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች እንደምን አላችሁ? በከተማችን በኮሪደር ልማት የተሰሩ አዳዲስና ውብ የመጫወቻ እንዲሁም የመዝናኛ ቦታዎችን አይታችኋል? ተዝናንታችሁስ ታውቃላችሁ? በዛሬው ቆይታችን፤ ጓደኞቻችሁ በእነዚህ አዳዲስ ቦታዎች እየሄዱ እንዴት እንደሚዝናኑ፣ ምን ያህል ደስ የሚል ጊዜ እንዳሳለፉና የመጫወቻ አማራጮቻቸው እንዴት እንደሰፉላቸው ያካፈሉንን ሀሳብ ወደ እናንተ እናደርሳለን! መልካም ንባብ ይሁንላችሁ፡፡

ሃሴት ሰለሞን እባላለሁ፡፡ መዝናናት በጣም ያስደስተኛል፡፡ ነገር ግን ለእኛ ለልጆች በነፃነት ለመጫወትና ለመዝናናት የተዘጋጀ ምቹ ቦታ አልነበረም፡፡ ሰፈር ውስጥ ከጓደኞቼ ጋር እጫወት፣ አልፎ አልፎም አምባሳደር ሞል ከእናትና አባቴ ጋር እየሄድኩ እዝናና ነበር፡፡

በአሁኑ ወቅት በኮሪደር ልማቱ በተዘጋጁልን መጫወቻዎች በዥዋዥዌው ላይ እየተወዛወዝኩ፣ መንሸራተቻዎች ላይ እየተንሸራተትኩ፣ አሸዋ ወይም ሰው ሰራሽ ጭቃ ላይ የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆን እየሰራሁ ጊዜዬን በደስታ በማሳለፍ ላይ እገኛለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፏፏቴዎችን የመመልከትና ከቤተሰብ ጋር ፎቶ የመነሳት እድልንም ፈጥሮልኛል፡፡



ፎቶ፡- በገነት ወንድሙ
ልጆች በለሙት አዳዲስ የመዝናኛ ስፍራዎች ሲጫወቱ



መሃመድ ሽምሱ እባላለሁ፡፡ ትርፍ ጊዜዬን በመዝናናት ነው የማሳልፈው። በኮሪደር ልማቱ በተሰሩልን መጫወቻ ቦታዎች ቀበና ወንዝ፣ አንድነት፣ አምባሳደር እና ወዳጅነት ፓርኮች ተዝናንቻለሁ። በቅርብ የማናገኛቸውን እንስሳት ለማየት አስችሎኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሳይክል ለመንዳት ምቹ የሆኑ መንገዶችም ተሰርተዋል፡፡

አደጋ ይደርስብኛል ሳልል ደህንነቴ ተጠብቆ እንድጫወትና እንድዝናና አድርጎኛል፡፡ ከቤት መውጣት አዳዲስ ጓደኞችን እንድተዋወቅና አብሬያቸው እንድጫወት አግዞኛል፡፡ የኮሪደር ልማቱ አዳዲስ ነገሮችን እንዳይ፣ በተለያየ ቦታ የመዝናናት አማራጮችን እንዳሰፋ አድርጎኛል፡፡

ፍርዶስ ሙራድ እባላለሁ፡፡ የኮሪደር ልማቱ ከመሰራቱ በፊት አንበሳ ግቢ እዝናና ነበር። ከትምህርት ቤት ስመለስ ስልክ ወይም ቴሌቪዥን ላይ ጊዜዬን አሳልፋለሁ። ከሰፈር ከጓደኞቼ ጋርም አባሮሽ እጫወት ነበር። አማራጭ የሆነ መጫወቻ ቦታ ባለመኖሩ በምፈልገው ልክ አልጫወትም ነበር፡፡ አሁን ግን ለመጫወት ምቹ የሆኑ መዝናኛ ቦታዎች ተሰርተዋል፡፡ አራዳ ፓርክ፣ ቀበና እንዲሁም ካሳንችስ የልጆች መጫወቻ ተዝናንቻለሁ፡፡

የተሰሩት መዝናኛ ቦታዎች በሚመቸኝ ሰዓት፣ በፈለግኩት ቦታ እንዲሁም የምፈልገውን ጨዋታ ለመጫወት እንድችል አማራጮችን አስፍቶልኛል፡፡

ናታን ኤሊያስ እባላለሁ፡፡ ከዚህ በፊት የምጫወተው በመንገድ ዳር፣ በኮብልስቶን ወይም ለመጫወቻ ባልተመቹ ስፍራዎች ነበር። በምጫወትበት ጊዜም የመኪና አደጋ እንዳያጋጥመኝ እፈራ ነበር፡፡

በአሁኑ ሰዓት የተሰሩት የመዝናኛ ስፍራዎች፣ የእግር ኳስ ሜዳ ከጓደኞቼ ጋር እንድጫወት፣ ዛፎች፣ አበቦችና አረንጓዴ ቦታዎች ያሉባቸው ስፍራዎች ከቤተሰቦቼ ጋር በመውጣት በተፈጥሮ መደሰት እንድችል አድርጎኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ንጹህ፣ ውብ፣ ሰፊ በሆኑ የእግረኛ መንገዶች በነፃነት እንድንቀሳቀስ፣ እንድንሮጥና ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን እንድናደርግ እድል ፈጥረውልናል፡፡ ይህም አካላችን እንዲጠነክር፤ የአዕምሮ ሰላም እንድናገኝ ጠቅሞናል፡፡

ልጆች የኮሪደር ልማቱ ከመሰራቱ በፊት እንደልባችሁ የምትጫወቱበትና የምትዝናኑበት ምቹ ቦታ አልነበረም። በዚህም በመንገድ ዳር ወይም በማይመቹ ቦታዎች ለመጫወት ትገደዱ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን ለዓይን የሚማርኩ አረንጓዴ ቦታዎች፣ በእግራችሁ በነጻነት እንድትንቀሳቀሱ የሚያግዟችሁ ምቹ የእግረኛ መንገዶች፣ የተለያዩ መጫወቻዎችና የስፖርት ሜዳ አማራጮች ስለተሰሩላችሁ በምትፈልጉት ቦታ በመሄድ መዝናናትን ምርጫችሁ አድርጉ እንላለን፡፡

## ብርቅዬዋ ወር ጳጉሜን




ጳጉሜን በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር (ካላንደር) ውስጥ የዓመቱ የመጨረሻ እና በጣም አጭር ወር ናት። ጳጉሜን የጎደሎ ወርም ትባላለች፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ጳጉሜን እንደሌሎቹ ወራት 30 ቀን የላትም። ጳጉሜን ወር ያላት ቀን በየዓመቱ 5 ቀናት ብቻ ሲሆን፣ በየ4 ዓመቱ (በዘመነ ሉቃስ) ደግሞ 6 ቀናት ትሆናለች።

"ጳጉሜን" የስሟን ስያሜ ያገኘችው ወይም "ጳጉሜን" የሚለው ቃል የመጣው "ኤፓጎሜኔ" ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም "ትርፍ" ወይም "ተጨማሪ ቀን" ማለት ነው።

ኢትዮጵያ በጳጉሜን ወር አማካኝነት ብቸኛ የ13 ወራት ባለቤት እና ባለፀጋ ናት። በዚህም በዓለም የተለየች ያደርጋታል፡፡

በጳጉሜን ወር ምን ይደረጋል አዲስ ዓመትን መቀበያ ወርም ናት፡፡ ክረምት አልፎ፣ መስከረም 1 (አዲስ ዓመት) ሳይጠባ በሁለቱ መካከል ያለች የሽግግር ወቅትም ናት። በመሆኑም በዚህች ወር ሰዎች ያለፈውን ዓመት አጠቃለው አዲሱን ዓመት ለመቀበል ይዘጋጃሉ።

ጳጉሜን ወር የሚጥለው ዝናብ የዕጥበት ወቅት ይባላል፡፡ በዚህም በባህላችን የጳጉሜን ዝናብ ልዩ ተደርጎ ይታያል። ልጆችና አዋቂዎች በጳጉሜን ዝናብ መታጠብ (መነከር) "ጤና ይሰጣል" ብለው ያምናሉ።

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ግንዱ ወደ ላይ ጫፉ ወደ ታች?**

**መልስ፡-** ሐ. የከብት ጅራት

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ላይጠቅማት ሸክሙ ባሳት?**

ሀ. የፍየል ጅራት

ለ. የበግ ላት

ሐ. የላም ቀንድ

**ልጆች፤ መልሱን ከጓደኞቻችሁ እና ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ተወያዩበት።**

## የቅጥር ማስታወቂያ

ማህበራችን አድዋ ፓርክ ሳይት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ከዚህ በታች ያለዉን ክፍት የሥራ ቦታ አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል፡፡

**የሥራ መደብ፡-** ሥራ አስኪያጅ

**ብዛት፡-** 1 (አንድ)

**የሥራ ቦታ፡-** ገርጂ ኢምፔሪያል የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግቢ ውስጥ

**ደመወዝ፡-** በስምምነት

**የትምህርት ደረጃ፡-** ባችለር ዲግሪ (Bachelor's Degree) በማኔጅመንት ወይም በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን (Business Administration)

**የሥራ ልምድ፡-** 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ

**ተመራጭ ሁኔታ፡-** በጋራ መኖሪያ ቤቶች አስተዳደር ላይ የሠራ/ች ቢሆን ይመረጣል

**የማመልከቻ ጊዜ፡-** ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7 (ሰባት) የሥራ ቀናት ውስጥ ማመልከት ይችላሉ።

**ማሳሰቢያ፡** - ለተጨማሪ መረጃ ስልክ ቁጥር 011-639-44-63 በመደወል ማግኘት ትችላላችሁ፡፡

**አድዋ ፓርክ ሳይት የኮንዶሚኒየም ባለቤቶች ኃ/የተ/ኅ/ሥራ ማህበር**

## ጨረታ ማስታወቂያ

በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 እውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ2019 በጀት አመት ለመስሪያ ቤቱ ስራ አገልግሎት የሚውሉ፡-

| የሎቱ አይነት | ሎቱ የሚወክለው ዘርፍ | ለየሎቱ የሚያዘው የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ መጠን |
|---|---|---|
| ሎት-1 | የፅፈት መሳሪያ | 15000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-2 | የደንብ ልብስ | 15000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-3 | የፅዳት እቃ | 5000 /አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-4 | ኮምፒውተርና ፕሪንተር ተዛማጅ | 15000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-5 | ፈርኒቸር ሌሎች ቋሚ እቃዎች | 10000 /አስር ሺህ ብር/ |
| ሎት-6 | መፅሃፍት | 5000 /አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-7 | የህክምና እቃዎች | 1000 /አንድ ሺህ ብር/ |
| ሎት-8 | የተለያየ የማሽን ጥገና ስራ | 1000 /አንድ ሺህ ብር/ |
| ሎት-9 | የጀነሬተር ጥገና | የለውም |
| ሎት-10 | የተለየዩ ኬሚካሎችን ማስገድ | የለውም |
| ሎት-11 | የጥገና ስራ | 5000 /አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-12 | መኪና ኪራይ | የለውም |

በጨረታ ቁጥር 01/019 አወዳድሮ እቃዎቹን እና አገልግሎቶቹን ለመግዛት ይፈልጋል። በመሆኑም በዚህ መሠረት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መስፈቶች የሚያሟሉ ድርጅቶችና ግለሰቦችን በጨረታው እንዲሳተፍ ይፈልጋል፡፡

1. ከላይ በዝርዝር ለተጠቀሱት ዕቃዎች አግባብነት ያለው ሕጋዊ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸው
2. የዘመኑን ግብር የከፈሉ እንዲሁም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ወይም አዲስ አበባ መስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር ለመመዝገባቸው የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉና ቫት ተመዝጋቢ የሆኑ እንዲሁም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርና የግብር ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት በልደታ ክ/ከተማ በዕውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በመገኘት ለሙሉ ሰነድ 200 (ሁለት መቶ ብር ብቻ) በመክፈል የጨረታውን ሰነድ መውሰድ ይችላሉ፡፡ ጨረታው የሚዘጋው ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ በወጣ በ11ኛው ተከታታይ የስራ ቀናት ከጠዋቱ 4፡30 ሰአት ተዘግቶ 5፡00 ይከፈታል፡፡
4. ተጫራቾች እያንዳንዱ ዕቃ እና አገልግሎት የሚሸጡበትን ዋጋ ከነቫቱ መግለጽ አለባቸው፡፡
5. በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተጠቀሱትን ሰነዶች እና ከተቋሙ የሚገዙትን ሰነድ ጭምር ኦርጅናሉን ኮፒ በማድረግ በ2 በተለያዩ ፖስታዎች አስገብቶ አርጅናልና ኮፒ ብሎ በመፃፍና በማሸግ ሙሉ አድራሻቸውን በመጥቀስ ሰነዱ ላይ በመፈረም ማህተም በመምታት በዕውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በግዢ ቢሮ ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡
6. በጨረታ ሰነዱ ላይ ዋጋ በሚሞሉበት ጊዜ ስተት ከተፈጠረ በአንድ መስመር ሰርዞ ካናቱ ፊርማ በማድረግ ማስተካከል ይፈቀዳል ነገር ግን በፍሉድ ማጥፋት እና ስርዝ ድልዝ ማድረግ አይፈቀድም፡፡
7. ተጫራቹ ዋጋ መሙላት ያለበት በተቋሙ ሰነድ ላይ ብቻ ሲሆን ከዚህ ውጪ ሌላ ሰነድ መጠቀም አይፈቀድም፡፡
8. ከተቋሙ ፍላጎት ወይም ስፔሲፊኬሽን ውጪ በራስ ፍላጎት ማርክ ጠቅሶ ዋጋ መስጠት አይቻልም
9. በሰነዱ ላይ ዋጋ በሚሞሉበት ወቅት የማይወዳደሩበትን እቃ ዋጋ መሙያ ቦታውን ባዶ መተው አይፈቀድም፡፡
10. ተጫራቾች የተጠቀሱትን ዕቃዎች በሙሉ ወይም በከፊል መጫረት ይችላሉ በተጨማሪም መደበኛ የጨረታ ሰነዱን በተጫራች የሚሞሉትን እና መፈረም ያለባቸውን ቦታዎች በአግባቡ ሞልቶ ፈርሞ መሃተም አድርጎ መመለስ አለባቸው
11. በጨረታ ለቀረቡት እቃዎች ሳምፕል የሚገቡ እቃዎች የማወዳደሪያ ሰነዱ ላይ ተጠቅሰዋል ናሙና መቅረብ ያልቻሉ እቃዎችን ከውጤት በኋላ በአካል ይዞ በመምጣት ማሳየት እና ትዛዝ ሲሰጠው ማስገባት ይኖርበታል፡፡
12. ከላይ በተጠቀሰው መሰረት CPO በልደታ ክፍለ ከተማ እውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ስም በማሰራት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
13. አሸናፊ ለሚሆኑ ተጫራቾች የውሉን 10 በመቶ ሲፒኦ ማስያዝ አለባቸው፡፡
14. የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ የሚወዳደሩትን የሎት መጠን ያክል ደምሮ በአንድ ሲፒኦ ማሰራት ይቻላል። መ/ቤቱ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
15. ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አምራች ካልሆኑ በስተቀር በደብዳቤ የማናስተናግድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**ድራሻ፡- የቀድሞ 3 ቁጥር ማዞሪያ ቶታል ስልክ 011-8346370**

**ልደታ ክ/ከተማ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት እውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት**

# የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

## የግዢ ጨረታ ማስታወቂያ መለያ ቁጥር 001/2019

በቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር የቦሌ ቡልቡላ ወረዳ 12 ጤና ጣቢያ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት፡-

ሎት 1. የደንብ ልብስ፣ ሎት 2. አላቂ የፅህፈት እቃዎች፣ ሎት 3. አላቂ የፅዳት እቃዎች፣ ሎት 4. ቋሚ እቃዎች፣ ሎት 5. ልዩ ልዩ መሳሪያዎች /አላቂ የቢሮ እቃዎች/፣ ሎት 6. ህትመት፣ ሎት 7. መድሃኒት እና ሪኤጀንት፣ ሎት 8. የአልሙኒየም ፓርቲሽን ስራ (አቅርቦትን ጨምሮ) ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

በዚህ መሰረት ጨረታውን ለመሳተፍ የሚፈልጉ ህጋዊ ተጫራቾች የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን አለባቸው ፡፡

1. ተጨራቾች በዘርፉ የተሰማሩበትን ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር ለመክፈላቸው ማስረጃማ ቅረብ የሚችል፣
2. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በአቅራቢነት የተመዘገበና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
3. የታደሰ የንግድ ፍቃድያለው፣
4. ተጫራቾች ናሙና ለተጠየቁባቸው እቃዎች ናሙናውን ቀድመው ጨረታ ሰነዱ ሣጥን ውስጥ ከማስገባታቸው በፊት ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. የቋሚ እቃ ተጫራቾች በአድራሻችሁ በመምጣት የእቃዎችን እስፔክ እና ጥራት የምናይ ይሆናል፡፡
6. ተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል፣
7. ተጫራቾች ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ C.P.O ብቻ ማቅረብ አለባቸው፡፡

| ሎት ቁጥር | የሎት ዝርዝር | የተጠየቀው የጨረታ ማስከበሪያ |
|---|---|---|
| ሎት 1. | የደንብ ልብስ | የኢትዮ.ብር 15,000 |
| ሎት 2. | አላቂ የፅህፈት እቃዎች | የኢትዮ.ብር 15,000 |
| ሎት 3. | የፅዳት እቃዎች | የኢትዮ.ብር 10,000 |
| ሎት 4. | ቋሚ እቃዎች | የኢትዮ.ብር 30,000 |
| ሎት 5. | ልዩ ልዩ መሳሪያዎች/አላቂ የቢሮ እቃዎች | የኢትዮ.ብር 8,000 |
| ሎት 6. | ህትመት | የኢትዮ.ብር 15,000 |
| ሎት 7. | መድሃኒት እና ሪኤጀንት | የኢትዮ.ብር 30,000 |
| ሎት 8. | የአልሙኒየም ፓርቲሽን ስራ (አቅርቦትን ጨምሮ) | የኢትዮ.ብር 30,000 |

8. የጨረታ ሰነዱን ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በየሎቱ የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል የተዘጋጀውን ሰነድ ከተቋሙ ቢሮ ቁጥር 404 /4ኛ ፎቅ እየቀረቡ መግዛት ይቻላል፡፡
9. ተጫራቾች ጨረታ ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉት 10 /አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 409 ድረስ በመምጣት ዋጋው የተሞላበትን የጨረታ ሰነዱን ዋናውንና ፎቶ ኮፒ ለየብቻው በማሸግ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
10. ጨረታው በ10ኛው ቀን 11፡00 ሠዓት ታሽጎ በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ የጨረታ መዝጊያና መክፈቻ የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተጠቀሰው ተመሳሳይ ሠዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
11. ተጫራቾች ያሸነፉበትን የገንዘብ መጠን የውል ማስከበሪያ 10% በባንክ የተረጋገጠ cpo ማስያዝ አለባቸው፡፡
12. ተጫራቾች ጨረታ ለሚወዳደሩባቸው ቋሚ ዕቃዎች መስሪያ ቤቱ ባቀረበው ስፔስፊኬሽን መሰረት ማቅረብ አለባቸው፡፡ ስፔስፊኬሽን ላይ የድርጅታቸውን ማህተም ፊርማ መኖር አለበት፡፡
13. የጨረታ አሸናፊ ድርጅት ያሸነፉበትን ዕቃ በራሱ ትራንስፖርት ንብረት ክፍል ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
14. መ/ቤቱ ለጨረታ ከቀረበ ውዕቃ እስከ 20% የመቀነስም ሆነ የመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
15. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
16. ተጫራቾች በሰነዳቸው ስማቸውን እና ሙሉ አድራሻቸውን በትክክል መሙላትና በማህተም መረጋገጥ አለበት፡፡

**አድራሻ፡- ስልክ 09-86-38-96-18 /0118 88 01 28**

**በቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የቦሌ ቡልቡላ ወረዳ 12 ጤና ጣቢያ ከማርያም ማዞሪያ 100 ሜ ገባ ብሎ**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር የቦሌ ቡልቡላ ወረዳ 12 ጤና ጣቢያ**

ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የተቋማትን አገልግሎቶች የማዘመን ጉዞ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?

• በበጀት ዓመቱ በመዲናዋ የሚገኙ የመንግሥት ተቋማትን ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል አሠራር ለማስገባት መታቀዱ ተጠቁሟል

**በደረጀ ታደሰ**

የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ሲነሱ ከነበሩ መሰረታዊ ችግሮች መካከል፡- የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት፣ ፍጥነት፣ የፍትሃዊነት መጓደል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ተቋማቱ ይከተሉት የነበረው ተለምዷዊ አሠራር ከወረቀት እና ከሰው ንክኪ ያልተላቀቀ፣ ዘመኑ የፈጠራቸውን ቴክኖሎጂዎችንና አሠራሮችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ያላዋለ፣ ከተናጥል የሥራ እንቅስቃሴ ወጥቶ የጋራ እና የተቀናጀ የተግባራት ትስስርን ያልፈጠረ ... ሆኖ ለዘመናት መቆየቱ ተፅዕኖው ከፍተኛ መሆኑ ተደጋግሞ ይገለጻል፡፡

"ችግርን ለይቶ ማወቅ የመፍትሔውን ግማሽ መንገድ እንደመጓዝ ይቆጠራል" እንደሚባለው፤ በመንግሥት ተቋማት ሰፍነው የቆዩ፣ የተገልጋይን እርካታ ያጎደሉ፣ ለምሬት እና ለመልካም አስተዳዳር ጥያቄ መነሻ የሆኑ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመፍታት፣ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት መስጠት ወሳኝ መሆኑ ታምኖበት ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ በተለይ የለውጡ መንግሥት መምጣትን ተከትሎ፣ ለጉዳዩ ትልቅ ትኩረት በመስጠት፣ ስትራቴጂካዊ የሆኑ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ በዚህም፤ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አሠራራቸውን በማዘመንና በቴክኖሎጂ በመታገዝ፣ የሚያበረታታ ውጤት አስመዝግበዋል፤ በማስመዝገብ ላይም ናቸው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በዚህ ረገድ እየተጓዙበት ያለው መንገድ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ እየተመዘገበ ላለው የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን የአሠራር መዘመንና በቴክኖሎጂ የማገዝ ስኬት ቁልፍ ሚና የተጫወቱ ተቋማት አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል። ምክንያቱም ይህ ተቋም፤ "የመንግስትና የህዝብ አገልግሎቶች በዘመናዊ የዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዙ፣ የተቀላጠፉ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነባቸው እንዲሆኑ ማድረግ" የሚለውን ተልዕኮ የማሳካት ኃላፊነት የተሰጠው፣ ኃላፊነቱንም በውጤታማነት ለመወጣት የሚሠራ በመሆኑ ነው፡፡

በዚህ ፅሑፍ ባለፉት ዓመታት፣ በተለይም ከለውጡ ማግሥት ጀምሮ፣ እንደከተማ አስተዳደር የመንግስትና የህዝብ አገልግሎቶች በዘመናዊ የዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዙ፣ የተቀላጠፉ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነባቸው እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ምን ተሠራ፤ ምንስ ውጤት መጣ? የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ በማንሳት ጉዳዩን ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ አዋሌ መሐመድ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡



ፎቶ ፡- ከፋይል
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ አዋሌ መሐመድ

"ቢሮው የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን አሰራር ለማዘመን እና የተገልጋዩን ህብረተሰብ እንግልት ለመቀነስ በርካታ መሰረታዊ ሥራዎችን አከናውኗል" ያሉት አቶ አዋሌ፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከተከናወኑ በርካታ ተግባራት መካከል ጥቂቶቹን ዘርዝረዋል። እንደሳቸው ገለጻ፤ በተቋማት የአሠራር ሂደት ማሻሻያ (Business Process Re-engineering - BPR) ተሠርቷል። የተቋማት አገልግሎቶች ዲጂታላይዝ ከመደረጋቸው በፊት የአገልግሎት ሂደት አላስፈላጊ ቢሮክራሲ እንዲቀነስላቸው ተደርጓል። የማዕከላዊ መረጃ ቋት (Central Repository) ተዘርግቷል፡፡ የህዝብ ቆጠራ፣ የቦታ፣ የንግድ ፈቃድና የሲቪል ምዝገባ መረጃዎች እንዲቀናጁ ተደርጓል። የክፍያ ስርዓትን በዲጂታል ቴክኖሎጂ አማካኝነት የሚከናወንበት ሂደት ተመቻችቷል፡፡ ከፋይናንስ ተቋማትና ከኢ-ቲ-ስዊች ጋር በመቀናጀት የአገልግሎት ክፍያዎች በቴሌብር፣ በባንክ እና በፖስ (POS) ማሽኖች እንዲፈፀም ተደርጓል፡፡

በከተማ አስተዳደር ደረጃ ያሉ የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን አሠራር የማዘመን ዋና ዓላማን አስመልክቶ ኃላፊው እንዳስረዱት፤ "የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት አሠራርን የማዘመን ዋና ግብ ዜጋን ማዕከል ያደረገ ቀልጣፋ፣ ፍትሐዊ፣ ግልፅ እና ተደራሽ አገልግሎት መዘርጋት ነው። ይህም የመንግስት አሰራርን ዘመናዊ በማድረግ የህዝብን እርካታ ማሳደግ፣ ብክነትን ማስወገድና የመዲናዋን ኢኮኖሚያዊ ውድድር አቅም ማሳደግ ነው፡፡"

ከላይ የተጠቀሰውን ዓላማ ወይም ግብ ለማሳካት በተሠራው ሥራ የተመዘገበው ውጤት በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? የሚለውን ጥያቄ ያነሳንላቸው፣ ቢሮ ኃላፊው በሰጡት ምላሽ፤ "ከተቀመጠው ዓላማ አንጻር የስራው አፈጻጸም አጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ በጣም አበረታችና ከፍተኛ ስኬት ያስመዘገበ ነው ማለት ይቻላል። በተለይም በገቢዎች ቢሮ፣ በንግድ ቢሮ፣ በሲቪል ምዝገባና በነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ የመሳሰሉ ተቋማት የወረቀት አልባ አሰሠራርን በመተግበር የተመዘገቡት ውጤቶች የሚጠበቀውን ግብ ያሳኩ ናቸው። እነዚህን ተቋማት ጨምሮ ከ120 በላይ የመንግስት አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በዲጂታል ሲስተም እንዲሰጡ ተደርጓል።" በማለት አስረድተዋል፡፡

ኃላፊው አክለው እንዳስረዱት፤ የመንግሥት ተቋማትን አገልግሎት አሠራር የማዘመንና በቴክኖሎጂ የማስደገፍ ተግባር በተገልጋዮች ዘንድ ተጨባጭ ውጤት አምጥቷል፡፡ ተገልጋዮች ለአንድ አገልግሎት የሚወስድባቸው ጊዜ ከቀናት ወደ ደቂቃዎች ዝቅ ብሏል። በየተቋማቱ ይታይ የነበረው መልካም አስተዳደር እጦትና ጉቦኝነት በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። የከተማ አስተዳደሩ የገቢ አሰባሰብ ብቃት በዲጂታል ታክስና ክፍያ ስርዓት ምክንያት በከፍተኛ መጠን አድጓል፡፡ በአዲስ መሶብ የአንድ መስኮት አገልግሎት አማካኝነት ከ80 በላይ የሚሆኑ የመንግስት አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከልና በዲጂታል ፕላትፎርም አቀናጅቶ ማቅረብ ተጀምሯል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በተሠሩ ሥራዎች አብዛኞቹ የከተማ አስተዳደሩ ዋና ዋና ተቋማት ወደ ዲጂታል የአሠራር ስርዓት የገቡ ቢሆንም፣ አሁንም በሙሉ አቅማቸው ያልገቡ ወይም በከፊል ባህላዊ አሰራርን የሚከተሉ ተቋማት መኖራቸውን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ፡- የመረጃ አደረጃጀትና ጥራት ችግር መኖር (በተለይ በአንዳንድ ተቋማት የቆዩ የወረቀት መረጃዎችን ወደ ዲጂታል የመለወጥ ሥራ ረጅም ጊዜ የሚወስድና ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ መሆኑ)፣ የህግና ደንብ ማዕቀፎች አለመሟላት (ለአንዳንድ አገልግሎቶች የዲጂታል ፊርማና የዲጂታል ሰነድ ህጋዊነት ደንቦች ሙሉ በሙሉ አለመጽደቃቸው) እንዲሁም የልዩ ፍላጎትና ውስብስብ አሰራሮች (ለአብነት፡- የፍትሕና የመሬት ዘርፍ አገልግሎቶች ከፍተኛ ህጋዊ ፍተሻና የመስክ ማረጋገጫ የሚጠይቁ መሆናቸው) አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል ለማሸጋገር ጊዜ መውሰዱን በምክንያትነት አብራርተዋል፡፡

በመዲናዋ ያሉ የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አሠራራቸውን የማዘመንና በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ የማድረጉ ተግባር፣ በሂደቱ ውስጥ የታዩ ችግሮችን ቀርፎ፣ በ2019 በጀት ዓመት ሁሉንም ተቋማት ወደ ዲጂታል አሠራር ለማስገባት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ አቅዶ ወደ ተግባር ገብቷል፡፡ በዚሁ መሰረት፡- በያዝነው የ2019 በጀት ዓመት የመጀመሪያው 6 ወራት (እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2019 ዓ.ም) ድረስ 80 ከመቶ የሚሆኑትን እንዲሁም እስከ በጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ (ሰኔ 30 ቀን 2019 ዓ.ም) ድረስ የመንግስት ተቋማትን ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል አሠራር በማስገባት አፈጻጸሙን 100 ከመቶ ለማሳካት ስትራቴጂካዊ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

የመንግሥት አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዙ እና ዘመናዊ አሠራርን የተከተሉ ለማድረግ የተቀመጠው ግብ እንዲሳካ ከቢሮው በተጨማሪ ሌሎች አካላትም ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አቶ አዋሌ መሐመድ ባስተላለፉት መልዕክት፤ "የመንግሥት ተቋማት አሰራራቸውን ሙሉ ለሙሉ ለዲጂታላይዜሽን ክፍት ማድረግ፣ ሰራተኞቻቸውን ማብቃትና መረጃዎችን ማቀናጀት፣ የግል ዘርፍና ቴክኖሎጂ ኩባንያዎች በቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት ግንባታና በፈጠራ ስራዎች ላይ በመንግስትና የግል ዘርፍ አጋርነት (Public-Private Partnership) መሳተፍ፣ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች የዲጂታል ትምህርትን ስርአተ-ትምህርት አጠናክሮ መተግበርና የምርምር ስራዎችን ማከናወን፣ ህብረተሰቡና ተገልጋዩ የዲጂታል አማራጮችን በቅንነትና በብቃት መጠቀም፣ ባህላዊ አሠራርን የመተው ፍላጎት ማሳየትና በተግባር መግለጥ ይገባል" ብለዋል፡፡

## ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

በልደታ ክፍል ከተማ ወረዳ 07 አስተዳደር ጽ/ቤት ለ2019 በጀት ዓመት 1ኛ ዙር የግብዓት ግዥ በግልጽ ጨረታ ሕጋዊ ተጫራቾች አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ የተሰማሩ ሕጋዊ ንግድ ፍቃድ ያላቸዉን ተጫራቾች አወዳድሮ መግዛት ስለሚፈልግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ አቅራቢዎች መሳተፍ ይችላሉ፡፡

| የሎት ምድብ | የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ |
|---|---|
| 1. የደንብ ልብስ | 20000 |
| 2. የጽህፈት መሳርያ | 15000 |
| 3. የጽዳት መጠበቅያ | 15000 |
| 4. የጽዳት እቃዎች | 2000 |
| 5. የመኪና ጎማ | 15000 |
| 6. የኤሌክትሮኒክስ | 10000 |
| 7. የፈርኒቸር ግዥ | 10000 |
| 8. የቢሮ መስተንግዶ | 3000 |
| 9. የሰራተኛ ካፍቴርያ | 5000 |
| 10. የጥገና አገልግሎት ግዥ | 2000 |
| 11. የትራንስፖርት ግዥ | 2000 |

1. ተጫራቾች ሕጋዊ የ2019 ዓ.ም የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያላቸው፡፡
2. ተጫራቾች የዘመኑን የ2019 ዓ.ም ግብር የከፈሉበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. ተጫራቾች TIN number ተመዝጋቢ የሆኑና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
4. ተጫራቾች ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ እና የVAT ተመዝጋቢ መሆን አለባቸው፡
5. የጨረታ ሰነድ መሸጫ ዋጋ 200/ ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ከቢሮ ቁጥር 09 መዉሰድ ይችላሉ፡፡
6. ከሎት 1-7 ላሉት ግዥዎች ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበርያ ላሸነፉት የእቃዉን ዋጋ 2% በባንክ በተረጋገጠ CPO ከዉል ጋር ማቅረብ አለባቸዉ፡፡
7. የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፡፡
8. የጨረታው ሳጥን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት በ10ኛው የሥራ ቀን በ11፡30 ሰዓት ተዘግቶ በቀጣዩ ቀን በ4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም (ሕጋዊ) ወኪሎቻቸው በተገኙበት ቢሮ ቁጥር 09 ይከፈታል፡፡
9. በጨረታው የተሳተፉት ሁሉም አቅራቢዎች ሰነዳቸውን ሞልተው ካስገቡ በኋላ ተጫራቾች ወኪሎቻቸዉ እንዲገኙ በማድረግ ይከፈታል፡፡
10. ዕለቱ በበዓላት ቀን ከሆነ ጨረታው በሚቀጥለው የሥራ ቀናት ይከፈታል፡፡
11. ወረዳው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ ሙብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
12. ተጫራች ድርጅቶች ለእቃ ማጓጓዣ የትራንስፖርት አገልግሎት በራሳቸዉ ወጪ መሸፈን ይጠበቅባቸዋል፡፡
13. ተጫራቾች ከሎት 1 እስከ 4 ድረስ ላሉት ሰነድ በሚያስገቡበት ወቅት ሳምፕል ማቅረብ አለባቸዉ
14. ተጫራቾች ከአንድ እስከ አስር /1—10/ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በኦሪጅናልና በኮፒ ማቅረብ የሚችሉ

**አድራሻ፦ ጎላ ፓርክ ፊት ለፊት**
**በስልክ ቁጥር 011-554-1638**

**የልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 7 ፋይናንስ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ለመኖሪያ አገልግሎት በአበበ አለሙ ሺበሺ በካርታ ቁጥር 01/583/009297/802744/01 በሴሪ ቁጥር 0245941 ተሰጥቷቸው የነበረው ማህደር ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ሌላ ማህደር እንደሚከፈትላቸው እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090707286 ሴሪ 0263686 የሆነው በቀሲስ ታደሰ ሲሳይ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት(ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 26/12/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**ጉዳዩ፦ የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 09 ማርሸት ግዛቸው ተሰማ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ የቤት ቁጥር 9999/1 ባለቤትነት የይዞታ የመለያ ቁጥር AA000050900901 ሴሪ L 013704 የተሰጠበት ቀን 29/10/2009 ዓ.ም የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቀን 26/12/2018 ዓ.ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ 30 ቀን ውስጥ በይዞታው ሙብት አለኝ የሚል እና ይህ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ያገኘ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ የይዞታ ካርታው መጥፋቱን በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣላቸው ሲሆን ካርታ መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ለአመልካቹ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

### በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 አስተዳደር ጽህፈት ቤት ስር ላሉት ጽህፈት ቤቶች በ2019 ዓ.ም በጀት ዓመት 1ኛ ዙር ግልፅ ጨረታ የሚያስፈልጋቸውን

ሎት 1 የእስቴሽነሪ ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ CPO -------------------- 20,000.00 ብር

ሎት 2 የፅዳት ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ CPO -------------------------10,000.00 ብር

ሎት 3 የደንብ ልብስ እቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ CPO ------------------20,000.00 ብር

ሎት 4 የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሆን የጨረታ ማስከበሪያ CPO ------5,000.00 ብር

ሎት 5 የተለያዩ የግብርና ዘር ምርቶች የጨረታ ማስከበሪያ CPO ----------5,000.00 ብር

ሎት 6 የአዳራሽ ዲኮር የጨረታ ማስከበሪያ CPO --------------------------5,000.00 ብር

ሎት 7 የደንብ ልብስ ስፌት የጨረታ ማስከበሪያ CPO ---------------------5,000.00 ብር

ሎት 8 ለመስተንግዶ አገልግሎች የጨረታ ማስከበሪያ CPO --------------- 5,000.00 ብር

ሎት 9 የህትመት ስራዎች የጨረታ ማስከበሪያ CPO ---------------------- 5,000.00 ብር

ሎት 10 የኮምፒውተር ጥገና የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን ----------- 5,000.00 ብር

ሎት 11 እንቁላል ጣይ ቄብ ዶሮ በእንሰሳ ዘርፍ ግብዓቶች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን ---- 25000 ብር

ብቃት ያላቸውንና በመስኩ የተሰማሩ ተጫራቾችን አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል በዚህም መሰረት፡-

1. በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ በመንግስት ግ/ን/አስ/ኤጀንሲ ድህረ ገፅ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ፣ የቲን እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ በየሎቱ ለይተው ማሲያዝ እንጂ ቼክ እና ቢድ ቦንድ የማናስተናግድ መሁኑን እያሳወቅን፡፡ በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ፋይናንስ ጽ/ቤት ስም ከጨረታው ሰነዶች አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ከሆነ የአምራችነት ሰርተፍኬት (ደብዳቤ) ማቅረብ ይኖርባቸዋል ፡፡
4. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት እለት አንስቶ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 402 በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይቻላሉ፡፡
5. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ ማስታወቂያው ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ለተከታታይ 10 የስራ ቀናት በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ፋይናንስ ጽ/ቤት 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 403 ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
6. ከሎት 1-10 ላሉት የግዥ እቃዎች ለውል ማስከበሪያ ላሸነፉባቸው እቃዎች የእቃውን ዋጋ 10% በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ማሲያዝ አለባችሁ
7. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በአስረኛው ቀን በ10፡30 ሰዓት ታሽጎ በ11 ቀን 3፡00 ሰዓት በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ፋይናንስ ጽ/ቤት 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 403 ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም የበአል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ታሽጎ ይከፈታል፡፡
8. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ለሎት 1፣ ለሎት 2፣ ለሎት 3፣ ለሎት 5 በከፊል፣ ለሎት 9 ናሙና ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን በተራ ቁጥር በቀረበው የፍላጎት መግለጫ መሰረት የተሟላ የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀትና ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
9. ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን እቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጨምሮ እቃዎች በዝርዝር ማስገባት ይኖርበታል ቫትን ያላካተተ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች እና ስርዝ ድልዝ ያለው ዋጋ ያቀረበ ተጫራች ከጨረታ ውድድር ይሰረዛል ፡፡

10 የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይነት የለውም

11. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
12. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ አድራሻ፡- ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 አስተዳደር ጽ/ቤት ተክለሀይማኖት ፔፕሲ ፋብሪካ አጠገብ**

**ስልክ ቁጥር 0112-75-91-71/0112-75-91-70**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልደታ ክፍለ ከተማ የወረዳ 5 ፈይናንስ ጽ/ቤት**

### የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለመጠየቅ

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት በ መልካምነሽ መንክር ገብረማርያም ስም የተመዘገበ ኮንዶሚንየም መለያ ቁጥሩ AA00005120733230806062 የሆነና የተሰጠበት ቀን 04/01/2014 የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የጠፋባቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ በቁጥር የካፓ/መ/ቁ/15/1913/18 በ18/12/2018 ዓ.ም የተጻፈ ማስረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ የሚል በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ምትክ ሰርተፍኬት የምንሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 01 ክልል ውስጥ በወ/ሮ መድህን አርአያ አረጋዊ ስም ካርታ ቁጠር 05397 ሴሪ ቁጥር 048581 በሆነ የተመዘገበው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን 21/12/2018 ዓ.ም ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 06 በአዲሱ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር አዲስ በካርታ ቁጥር ደ2/09/09/002829/004413/01 በአቶ/ወ/ሮ/እነ ማንደፍሮ ሀይሉ ወልደአብ ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመቅረብ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ጥላሁን በየነ ኪዳኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000060300833 ሴሪ ቁጥር R 017310 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 04 የካርታ ቁጥር ወ4/ውዝ01/1460/22813/00 ሴሪ 081098 የሆነው በአቶ ጀማል መሀመድ አብዱልአዚዝ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 13/12/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በብሩኬ አለማየሁ ጥበበ ስም የተመዘገበ ይዞታ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000090706280 ሴሪ ቁጥር L 098102 የሆነ ይዞታ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን በ25/12/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ለመኖሪያ አገልግሎት በካርታ ቁጥር 01/447/13277/00 በሴሪ ቁጥር 097522 በቶፊቅ ከሊል ሁሴን ተሰጥቷቸው የነበረው ማህደር ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ሌላ ማህደር እንደሚከፈትላቸው እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ አበበ ሱራፌል ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ቦሌ16/150/8148/00 ሴሪ ቁጥር 130422 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤት ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼአለሁ የሚል ሰው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት መስከረም ገብረህይወት ስም የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000080106623 የሴሪ ቁጥሩ 022054 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ተለዋጭ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ተሾመ ደምሴ ወልደስምኦን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 14 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061404964 የሚገኘው መኖሪያ ቤት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ካርታ ሴሪ ቁ R 0205426 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ /የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት /ካርታ ስለጠፋባቸው በማኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጠቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 368 የይዞታ ጣይቱ ኢብራሂም ሙሄ እና ደጉ ደነቀ ኢብሳ ስም የተመዘገበው የካዳስተር ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር AA000020500136 ሴሪ ቁጥር R 007462 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 22/12/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑ የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ 30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ አንደተሞከረው በየሡፍ ሀጂ አሊ ስም በቀድሞ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ቀበሌ 05 በአዲሱ ክ/ከተማ በልደታ ወረዳ፣ 08 በካርታ ቁጥር 05/127/13402/00፣ ሴሪ ቁጥር 097085 የተመዘገበ ይዞታ ካርታ ጠፋብኝ ብለው በቀን 07/12/2018 ዓ.ም በማመልከቻ ጠይቀውናል፡፡ ስለዚህ የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያሙች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳይ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጂናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዠዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ ሙብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ መዝገቡ ለገሰ ሀብቴ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA0000610073053400223 ሴሪ ቁጥር C 195764 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

እነ ወ/ሮ መሰለች ጸጋዬ ደጀኔ (2 ሰዎች) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 07 የይዞታ (የቤቱ) ልዩ መለያ ኮድ ቁጥር AA000100705788 የተሰጠበት ቀን 18/01/2018 ዓ.ም ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰርተፍኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግንቸዋለሁ/ይዠዋለው/ የሚል ሰው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰርተፍኬት/የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፍስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ 19 ቀበሌ 56 በአዲሱ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር---------በካርታ ቁጥር ዴ1/14026/21044/57775/77213/03 በአቶ/ወ/ሮ/እነ ባዩሽ ጉልላት እና 6ቱ ወራሾች ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመቅረብ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የይዞታ መለያ ቁጥር፡- ሴሪ ቁጥር፡- C228854 ይዞታ መለያ ቁጥር፡- AA000061400420050003 ፍቅር አሰፋ ታረቀ ስም በተቋማችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት ይዠዋለሁ ወይም አግኝቸዋለው የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ፣ ከወጣበት ቀን እስከ 30 ቀን ድረስ በጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ /ሰርተፍኬት/ እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

# ጳጉሜን እና የቱሪዝም ዕድሎች

በለይላ መሀመድ




ግራፊክስ በእዮብ ተፈራ

የ13 ወር ፀጋ ባለቤት መሆን የሚፈጥረውን መልካም አጋጣሚ የቱሪስት መስህቦችን ለማስተዋወቅ መጠቀም ይገባል

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ፣ በታሪክና በባህል ሀብት የታደለች ሀገር ናት፡፡ በዓለም በጥንታዊ ስልጣኔ ባለቤትነቷ፣ በሰው ዘር መገኛነቷም ትታወቃለች፡፡ የቱሪዝም መምህርና ተመራማሪ አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን እንደተናገሩት፣ በዓለም የቱሪዝም ገበያ ውስጥ አንድ ሀገር ከሌላው የሚለይበት ልዩ ታሪክ የቱሪዝም እሴት ነው። አንዳንድ ሀገራት በጥንታዊ ቅርሳቸው የሚታወቁ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በተፈጥሮ ውበታቸው፣ በባህላቸው ወይም በልዩ የህይወት መርሃቸው የቱሪስቶችን ቀልብ ይስባሉ።

ኢትዮጵያ ከእነዚህ ሁሉ በተጨማሪ ለዓለም ልዩ የሆነ መለያ የ13 ወር ፀሐይ ጸጋ አላት። '13 ወራት ፀሐይ ጸጋ' የሚለው መሪ ሃሳብ በቀላሉ የሚነገር ቢሆንም በውስጡ የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር፣ ባህል፣ ተፈጥሮና ልዩ ማንነት የሚያገናኝ ሰፊ የቱሪዝም ሀብት እንደሆነ የሚናገሩት የቱሪዝም ምሁሩ አያሌው (ዶ/ር)፣ ይህንን ልዩ የቱሪዝም ሀብት በማስተዋወቅ በተገቢው መጠቀም እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። ጳጉሜን የኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር ልዩነትን ብቻ የምትወክል ወር ሳትሆን ሀገሪቱ ለዓለም ልዩ ገጽታዋን የምታስተዋውቅበት የቱሪዝም መግቢያ በር መሆኗንም አክለዋል።

የጳጉሜን ልዩ የጊዜ መቁጠሪያነት የቱሪስቱን ጉጉት ይቀሰቅሳል፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክና ተፈጥሮ ደግሞ ያንን ጉጉት ወደ ጉብኝት ሊቀይሩት ይችላሉ። ስለዚህ ቀጣዩ ትልቅ ስራ ይህንን የቆየ የሀገር መለያ በአዲስ የዲጂታል ቋንቋ በማደስ "ምድረ ቀደምት" ከሚለው መጠሪያዋ ጋር በተገቢው ማጣመርና የሚሸጥ የቱሪዝም ምርት ማድረግ ይገባል።

አያሌው (ዶ/ር) እንደሚገልፁት፤ ኢትዮጵያ ከብዙ ሀገራት የምትለይበት አንዱ መገለጫዋ የራሷ የዘመን አቆጣጠር መኖሩ ነው። 12ቱ ወራት እያንዳንዳቸው 30 ቀናት ሲኖራቸው በዓመቱ መጨረሻ የምትመጣው ጳጉሜን አምስት ቀናት እና በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ስድስት ቀናት የምትሆን ልዩ ወር ናት። ይህ በውስጡ ሰፊ የታሪክና የባህል ትርክት ይዟል። ጳጉሜን የዓመቱ መጨረሻ ሆና ለመጪው አዲስ ዓመት የምታስረክብ ድልድይ ናት። የአሮጌውን ዘመን በመዝጋት የአዲሱን ዓመት በር ትከፍታለች። በዚህ የዘመን መለወጫ ወቅት ደግሞ ኢትዮጵያ ሌላ የተፈጥሮ ገጽታዋን ትገልጣለች። የክረምቱ ጨለማ እየቀነሰ የፀሐይ ብርሃን ይበረታል። የወንዞች ውሃ ኩልል ወይም ጥርት ይላል። አበቦች ይፈካሉ፡፡ ሜዳና ተራራው አረንጓዴ ልብስ ይለብሳሉ።

> **"ዓለም በመረጃ ብዛት በተጨናነቀበት በዚህ ዘመን፣ የምንነግረው የቱሪዝም ጥሪና የምናቀርበው ታሪክ ማራኪ፣ ሳቢ እና ፈጽሞ የማያሰለች መሆን አለበት"**

መስከረም ሲገባ የሚታየው ይህ የተፈጥሮ ለውጥ ለቱሪዝሙ የራሱ የሆነ አበርክቶ አለው።

ኢትዮጵያ በታሪኳ፣ በባህሏና በተፈጥሮ ሀብቷ ብትታወቅም በሌላ በኩል ደግሞ በረሃብ፣ በድርቅና ግጭት ትታወቃለች፡፡ ይህ 13 ወራት ፀሐይ ፀጋዋ ይህንን ገጽታ ለመቀየር አቅም አለው። ወደ ተጨባጭ የቱሪዝም ምርት መቀየር ያስፈልጋል። የጳጉሜን ወቅትን ከአዲስ ዓመት ጉብኝት፣ ከባህላዊ በዓላት፣ ከተፈጥሮ ጉብኝት፣ ከባህልና ቱሪዝም ጋር ማያያዝ ከተቻለ ቱሪስቶች እንደ አንድ የጉዞ ምክንያት እንዲመለከቷት ያደርጋል። ኢትዮጵያ በየአቅጣጫው የተለያዩ የአየር ንብረቶች፣ የተፈጥሮ ገጽታዎች፣ ተራራዎች፣ ሸለቆዎች፣ ወንዞች፣ ሐይቆችና የዱር እንስሳት ያሏት ሀገር መሆኗን ለዓለም ማሳየት ይቻላል። ወሯን በፊታውራሪነት በመጠቀም ከተለያዩ የሀገሪቱ መስህቦች ጋር ማገናኘት ይቻላል። የታሪክ ሐውልቶች፣ የተፈጥሮ መስህቦች፣ የባህል በዓላት፣ የምግብ ባህል የመሳሰሉትን ሁሉ መጠቀም ይቻላል።

የቱሪዝም ሚኒስቴር የፕሮሞሽን መሪ ሥራ አስፈጻሚ ተሾመ ተክሉ በበኩላቸው፤ "የጳጉሜን ልዩ ወር ምክንያት በማድረግ ኢትዮጵያ የቱሪዝም ሀብቷን '13 ወራት ፀሐይ ጸጋ' በሚል መሪ ሃሳብ ለረጅም ዓመታት ለዓለም ለማስተዋወቅ ስትጠቀምበት ቆይታለች። ይህም የሚያሳየው በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ላይ ያለች አንዷት ወር ብቻ ሳትሆን፣ ኢትዮጵያ ለዓለም የምትናገረው ልዩ ታሪክ ያላት ሀገር መሆኗን ነው። የ13 ወራት ፀሐይ ጸጋ የሚለው መሪ ሀሳብ ጳጉሜን ብቻ የሚያመለክት ሳይሆን ኢትዮጵያ ያላትን ሰፊ የቱሪዝም ሀብት ለዓለም ለማስተዋወቅ እንደ መግቢያ ሊያገለግል ይችላል።" ሲሉ ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ተሾመ ገለጻ፣ ቱሪዝም በአንድ ተቋም ብቻ የሚሳካ ዘርፍ አይደለም። በዚህ ረገድ የቱሪዝም ሚኒስቴር ብቻ ሳይሆን አስጎብኚዎች፣ የጉዞ ድርጅቶች፣ ኤምባሲዎች፣ አየር መንገድ፣ በውጭ ሀገራት የሚገኙ የኢትዮጵያ ማህበረሰቦችና የቱሪዝም አዘጋጆች (ኦርጋናይዘሮች) በጋራ መሥራት ይገባቸዋል። በተለይም በትራንስፖርት፣ በሆቴል፣ በአስጎብኚ ድርጅት፣ በሚዲያ፣ በዲጂታል መድረኮችና በዲፕሎማሲ ተቋማት መካከል ቅንጅት ይፈልጋል።

አያሌው (ዶ/ር) የቱሪዝም ሚኒስቴር የፕሮሞሽን መሪ ሥራ አስፈጻሚውን ሀሳብ ይጋራሉ፡፡ የቱሪዝም ዘርፍ በብቸኝነት የሚሰራ ሳይሆን የሁሉም አካላት እጅ ለእጅ ተያይዞ መስራትን ይጠይቃል። ሚኒስቴሩ ዘርፉን በበላይነት የሚመራ ከመሆኑ አንጻር መመሪያዎችን ለአስጎብኚ ድርጅቶችና የጉዞ ወኪሎች ማስተላለፍ አለበት። በውጭ ሀገራት የሚገኙ ኤምባሲዎችም የሀገር መልዕክተኞች በመሆናቸው በጽሑፍ፣ በቪዲዮ፣ በዲጂታል አማራጮች መረጃዎችን በማሰራጨትና በቱሪዝም ኤግዚቢሽኖች የኢትዮጵያን ልዩ የጊዜ አቆጣጠርና የተፈጥሮ ጸጋ ማስተዋወቅ አለባቸው።

በውጭ ሀገር የሚገኙ የጉዞ አደራጆች (Tour Organizers) ስለ ኢትዮጵያ አስደናቂ እውነታዎች ለዓለም ማህበረሰብ በማስረዳት ቱሪስቶችን በማሰባሰብ የመላክ ሚናቸውን መወጣት አለባቸው። በየሀገሩ የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሀገራቸው አምባሳደር በመሆን የቱሪዝም ኤግዚቢሽኖችንና መድረኮችን በመጠቀም ገጽታ የመገንባት ስራ መስራት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ሌላኛው አስተያየት ሰጪ የቱሪስት አስጎብኚው ፋሲል አበባ ኢትዮጵያ የ13 ወር ፀሐይ ጸጋ ያሏት ሀገር መሆኗን ለእንግዶች ሲያስረዳ የሚፈጠረው ጉጉት በራሱ የቱሪዝም መስህብ እንደሆነ ይገልጻል። የ13 ወራት ፀሐይ ጸጋ የሚለው መልዕክት ቱሪስቱን ያስገርመዋል። ይህ መገረም ወደ ጥያቄ ይለወጣል፡፡ ጥያቄው ደግሞ ወደ ታሪክ፣ ወደ ባህልና ወደ ጉብኝት ፍላጎት ሊመራ ይችላል።

እንደ አስጎብኚው ፋሲል ገለጻ፤ ከሌሎች ሀገራት በተለየ 12ቱ ወራት እኩል 30 ቀናት መያዛቸውና ጳጉሜን ደግሞ በዓመቱ ላይ ተጨማሪ ወር ሆና መገኘቷ እንግዶችን የሚስብ ልዩ ታሪክ ነው። እንዲሁም ኢትዮጵያ 12 ሰዓት

ወደ ገጽ 21 ዞሯል

## ዕውቅና ... ከገጽ 6 የዞረ

ከዚህ አኳያ ለአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እና ለከተማ አስተዳደሩ አመራር የተሰጠው ዓለም አቀፍ እውቅና የተጀመረው ስራ ትልቅ ትርጉም ያለው ከመሆኑ አኳያ ስራውን አጠናክሮ ለመቀጠል ብርታትና መነሳሻ እንደሚሆን መምህር ፍስሃ ተናግረዋል፡፡ ስራዎቹ የአሁኑን ብቻ ሳይሆን የነገውን ትውልድ ታሳቢ ያደረገ በመሆኑ በቀጣይም ጥራቱን ጠብቆ፣ ባለሙያዎችን፣ የወደፊቱን እድሎችና ፈተናዎች (የቴክኖሎጂና ሰው ስራሽ አስተውሎት ፈተናዎችና እድሎችን) እና የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ባማከለ መልኩ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

የመጀመሪያውን ዓለም አቀፍ የቀዳማይ ልጅነት ጉባኤ ከግንቦት 3 እስከ 5 ቀን 2018 ዓ.ም በአዲስ አበባ በተካሄደበት ወቅት ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፣ በመዲናዋ ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ "አዲስ አበባን ህፃናትን ለማሳደግ ምርጧ የአፍሪካ ከተማ ለማድረግ አልመን ከስድስት ዓመት በታች የሆኑ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሕፃናት ተገቢ የጤና እንክብካቤ፣ ትምህርት እና ሁሉን-አቀፍ አገልግሎት ድጋፍ እንዲያገኙ ባለብዙ ዘርፍ ፕሮግራም ተግባራዊ እያደረግን እንገኛለን።

በዋናነትም በቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም ለ330 ሺህ በኢኮኖሚ ተጋላጭ ቤተሰቦች ላይ ቅድሚያ ሰጥተን እየሰራን ነው" ብለዋል፡፡

በ2015 ዓ.ም 11 ብቻ የነበረው የሕፃናት ማቆያ ማዕከላት በ2018 ከ1 ሺህ 155 በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡ በእነዚህ ማዕከላት ለህጻናት የምግብ፣ የህክምና፣ የስነ ልቦና እና የእንክብካቤ አገልግሎት በነፃ እየሰጠ ይገኛል፡፡ በ2015 ዓ.ም 20 ብቻ የነበረውን የልጆች መጫወቻ በ2018 ወደ 5 ሺህ በማሳደግ ልጆች ቦርቀዉ የሚያድጉበት አካባቢን መፍጠር ተችሏል፡፡

ከንቲባዋ በወቅቱ እንደገለጹት፣ በእድገት ወደ ኋላ የቀሩ ህጻናት መጠን በ2015 ዓ.ም መርሃ ግብሩ ሲጀምር ከነበረበት 13 በመቶ ወደ 10 በመቶ ዝቅ፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጅታቸውም ከነበረበት 49 በመቶ ወደ 90 በመቶ ከፍ ማድረግ ተችሏል።

በጥር ወር 2018 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደው አህጉራዊ የከተሞች የተሞክሮ ልውውጥ እና የድርጊት መርሃ-ግብር ግምገማ አውደ ጥናት ላይ ከተሳተፉ የአፍሪካ ከተሞች ከንቲባዎች መካከል የዛምቢያ ዋና ከተማ ሉሳካ ከንቲባ ወይዘሮ ቺላንዶ ችታንጋላ አንዷ ናቸው፡፡ ከንቲባዋ ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ለአራተኛ ጊዜ ሲሆን በመጡ ቁጥር አዳዲስ ለውጦችንና ልማቶችን እንደሚመለከቱ ተናግረዋል፡፡ "የከንቲባ ጽህፈት ቤት የሚመራው የቀዳማዊ ልጅነት ፕሮግራም አለ፡፡ በከተማዋ የሚከናወነው ልማት አብዛኛው የልጆችን ደህንነት፣ የወላጆችና ቤተሰብ ጫናን የሚያቃልል ነው፡፡ ይህንን ተነሳሽነት ወደ ሉሳካ በመውሰድ የቀዳማዊ ልጅነት ፕሮግራምን እየተገበርን እንገኛለን፡፡ ሉሳካ ለልጆችና ወላጆች መኖሪያነት ምቹ የሆነች ከተማ እንድትሆን እንፈልጋለን" ሲሉ ከኢዜአ ጋር በነበራቸው ቆይታ ማንሳታቸው ይታወሳል፡፡

የዘንድሮው ጳጉሜን 5"የነገ ቀን" ተብሎ የተሰየመ ሲሆን፣ ዛሬ ላይ በቀዳማይ ልጅነት ህጻናት ላይ እየተሰሩ ያሉ ዘርፈ ብዙ ስራዎች፣ የነገዋን ሀገር መጻኢ ጊዜ ብሩህ፣ ተስፋ ሰጪና በጠንካራ መሰረት ላይ እየተገነባ ስለመሆኑ የሚያመላክት ነው፡፡

## መዲናዋን ... ከገጽ 7 የዞረ

የስማርት ሲቲ ባለ ርዕይ መሪ ሽልማትን ማግኘታቸው ይታወሳል፡፡ ሽልማቱ ዘላቂ፣ ለአካባቢ ተስማሚ፣ በቴክኖሎጂ የሚመራና ሁሉን አቀፍ ከተማ ለመፍጠር እንደ ኮሪደር ልማት ያሉ ትኩረት የሚሰጣቸው ፕሮጀክቶችና ለዜጎች አስፈላጊ ማኅበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ መርሐ ግብሮችን በመተግበር ያደረጉትን ጥረት ያገናዘበ ነው፡፡

ሌላው አዲስ አበባ ብክለትን ለመከላከል፣ የአየር ጥራትን ለማሻሻል፣ የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ ያሳየችው ቁርጠኝነት፣ ያወጣቻቸው ስትራቴጂዎችና ህጎች "ብሪዝ ስቲስ" በተሰኘ መርሃ ግብር አባልነት እንድትታቀፍ አድርጓታል፡፡ መርሃ ግብሩ የአየር ጥራትን ለማሻሻል፣ የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ፣ ለነዋሪዎች ጤናማ የኑሮ ሁኔታ ለመፍጠር የተጀመረ ዓለም አቀፍ ትብብር ነው፡፡ የከተማ ዲዛይንና ፕላን ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል (ዶ/ር) እንደሚሉት፣ ይህ ለከተማዋ ትልቅ ስኬት የሚባል ነው፡፡

የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ወደ መዲናዋ የሚመጡ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች፣ የከተሞች ከንቲባዎች፣ ባለሙያዎችና የተለያዩ ዜጎች የሚኀበኟቸው፣ ልምድና ተሞክሮ የሚወስዱባቸው ሆነዋል፡፡ ከአንድ ዓመት በፊት ለአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከተማዋን የጎበኙት የደቡብ አፍሪካው ፕሬዝዳንት ሲሪል ራማፎሳ፣ "አዲስ አበባ አሁን ላይ ንጹህ እና ውብ ሆናለች። የከተማዋ ማራኪ ገፅታ ሠዎች እንዲሠሩ እና በርካቶች ለኢንቨስትመንት የሚመርጧት እንድትሆንም አስችሏታል" ሲሉ መናገራቸው ይታወሳል፡፡ ዳንኤል (ዶ/ር) እንደሚሉት፣ በኢኮኖሚ ያደገችና የአፍሪካ ተምሳሌት ከሆነች ሀገር ፕሬዝዳንት እንደዚህ አይነት አስተያየት መሰማቱ የከተማዋን ለውጥ ደረጃ ያሳያል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም (ዶ/ር) ነሐሴ ወር 2017 ዓ.ም "የመደመር መንግስት" የተሰኘውን መጽሐፋቸውን በተመለከተ ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋር ባደረጉት ቆይታ፣ በአዲስ አበባ የወንዝ ዳርቻ የተሰራው ልማት ለአፍሪካ ተምሳሌት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ "ምንም ጥርጥር የለውም፤ የኢትዮጵያ የወንዝ ዳርቻ ልማት ልክ እንደ አረንጓዴ አሻራ ለመላው አፍሪካ ምልክትና ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ገደልና የቆሻሻ መጠራቀሚያ የነበሩ የወንዝ ዳርቻዎች አሁን የተለየ ውበትና ገፅታ ይዘዋል፡፡ ለበርካታ ወገኖች የንግድና የስራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡ የሀገርን ገፅታና መልክ ቀይሯል፡፡

በአዲስ አበባ የተከናወኑት የልማት ሥራዎች የከተማዋን ያረጁ ሰፈሮች መልክ ቀይረዋል። "እንደ እሪ በከንቱ፣ ዶሮ ማነቂያ፣ ፒያሳ እና ሸሮ ሜዳ ያሉ አካባቢዎች ለምተው የከተማዋ የውበት ማዕከል ሆነዋል። ወንዞችን ብንመለከት ለምሳሌ የቀበና ወንዝ በአሁኑ ወቅት በርካታ ጎብኚዎች የሚጎርፉበት ቦታ ሆኗል። አዲስ አበባ በማንሰራራት ላይ ትገኛለች፤ የአፍሪካም ተምሳሌት ሆናለች" ይላሉ የከተማ ዲዛይንና ፕላን ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል (ዶ/ር)፡፡

ቀጣይ ትውልድ የሚታነፅባት አዲስ አበባ እየተፈጠረች ነው፡፡ እነዚህ ስራዎች ዘላቂ ልማትን ከማረጋገጥ አኳያ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡ ለዚህ ውጤት መገኘትም አመራሩ የተጫወተው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ የኮሪደር፣ የወንዝ ዳርቻ እና የአረንጓዴ ልማት ስራዎች የስራ ዕድል ከመፍጠርና ጤናማ የመኖሪያ አካባቢ ከመገንባት ባሻገር የከተማዋን የኮንፈረንስ ቱሪዝም ማዕከልነት በማሳደግ አዲስ አበባን እንደ ስሟ አዲስ እና ውብ እንዳደረጓት አክለዋል።

## ከጥበብ ... ከገጽ 11 የዞረ

የምርምር ጥናት፤ ኪነ-ጥበብ እና በጎ አድራጎት በምን መልኩ እንደሚተሳሰሩ በሰፊው ይዳስሳል። ተመራማሪው በስራቸው እንደገለጹት፣ ጥበብ ተደራሽ የሚሆነው እና ለበጎ አድራጎት ስራዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክተው ከማህበረሰቡ መዋቅር፣ ከአካባቢያዊ እሴቶች እና ከለጋሾች ተሳትፎ ጋር በጠንካራ መሰረት ሲቀናጅ ነው።

ይህ ጥናት ኪነ-ጥበብ የገንዘብ ማሰባሰቢያ መሳሪያ ብቻ ሳይሆን፣ የለጋሾችን ተሳትፎ ዘላቂ በማድረግ እና የማህበረሰብ ትስስርን በማጠናከር ረገድ ትልቅ ኃይል እንዳለው በሳይንሳዊ መንገድ ያረጋግጣል። ሼክትማን በሥራቸው እንደሚያስገነዝቡት፣ ጥበብ እና በጎነት የሰውን ልጅ የጋራ መተሳሰብ ከፍ የሚያደርግ እና ለተቸገሩት ዘላቂ መፍትሔዎችን ለማምጣት የሚያስችልን ታላቅ መድረክ ይፈጥራል። በአጭሩ ኪነ-ጥበብ ድጋፍ ለሚፈልጉ ወገኖች የብርሃን ችቦዎች በመሆን የነገን ተስፋ የማሳየት አቅም ያለው ነው፡፡

በአጠቃላይ በዓለም ሆነ በኢትዮጵያ በኪነ-ጥበብ እና በጎነት መካከል ያለው ቁርኝት እጅግ ጥብቅ እና አመታትን ተሻግሮ ዛሬ የደረሰ ነው። ጥበብ አዝናኝ ብቻ ሳይሆን፣ የተራቆቱትን የሚያለብስ፣ የተጎዱትን የሚጠግን እና ማህበረሰቡን በሞራል የሚገነባ ሀብት ነው። ዛሬም ቢሆን አርቲስቶች እና የጥበብ ባለሙያዎች ይህንን መልካም ባህል አጠናክረው በመቀጠል፣ ለተሻለች እና የእርስ በእርስ መረዳዳት ዘወትራዊ ባህል የሆነባት ኢትዮጵያን ለመገንባት የበኩላቸውን አስተዋጽ ማድረግ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም በፊልሞች፣ በልቦለዶች እና በግጥሞች ውስጥ የሚንጸባረቁ የበጎነት፣ የይቅርታ እና የመረዳዳት እሴቶች ለሀገር ሁለንተናዊ ለውጥ ጉልህ ድርሻ ያበረክታሉ። ጥበብ የሰውን ልጅ ከተራ የራስ ወዳድነት አጥር አውጥቶ የሌሎችን ችግር እንዲጋራና እንዲያስብ የማድረግ አቅምም አለው።

## ጳጉሜን ... ከገጽ 20 የዞረ

ሙሉ ቀንና 12 ሰዓት ሙሉ ሌሊት የሚሆንበት እኩል የተፈጥሮ ምት ያላት ሀገር ናት። የ13 ወራት የፀሐይ ጸጋ ሲባል በክረምት ወቅት ሐምሌና ነሐሴ እንኳን ጠዋት ዘንቦ ከሰዓት ፀሐይ የመውጣት ተፈጥሮአዊ ባህሪ አለ፤ አዲስ አበባ ዝናብ በሚሆንበት ጊዜ እንኳ ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በፀሐይ የተሞሉ በመሆናቸው ዓመቱን ሙሉ ፀሐያማ ሀገር ያደርጋታል። ይህ የጊዜ አቆጣጠር ብቻ አይደለም፤ ሀገርን ለማስተዋወቅ የሚያገለግል መሳሪያ ነው።

የቱሪዝም ፕሮሞሽን መሪ ስራ አስፈጻሚው በበኩላቸው፤ ተቋሙ ይህንን የ50 ዓመታት የቱሪዝም ብራንድ ከአዲሱ ምድረ ቀደምት ጋር በማጣመር በዲጂታል ሚዲያዎች፣ በድረ ገጽና በፌስቡክ ሰፊ የማስተዋወቅ ስራ እየሰራ ይገኛል። ወደፊት እንደ ሀገር ሊሰራ የሚገባው የፕሮሞሽን ስራዎችን ከፋፍሎና አቅጣጫ አስይዞ መስራት ነው። ዓመቱን ሙሉ ወጥ በሆነ መልኩ ማስተዋወቁ እንደተጠበቀ ሆኖ በክረምቱ ወቅት ጳጉሜን የ13 ወራት ፀሐይ ጸጋ በሚል እንደ ልዩ የቱሪስት መቀስቀሻ መጠቀም እንደሚገባ ይገልጻሉ።

ዓለም በመረጃ ብዛት በተጨናነቀበት በዚህ ዘመን፣ የምንነግረው የቱሪዝም ጥሪና የምናቀርበው ታሪክ ማራኪ፣ ሳቢ እና ፈጽሞ የማያሰለች መሆን እንደሚኖርበትም ሚኒስቴሩ ያምናል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጳጉሜን እያንዳንዱ ቀናት ስያሜ በማውጣት እየተከበረ መገኘቱም አንዱ ማሳያ እንደሆነ አክለዋል፡፡

በ1964 ዓ.ም "የኢትዮጵያ የቱሪዝም አባት" በመባል በሚታወቁት በአቶ ሀብተስላሴ ታፈሰ አማካኝነት የተጠነሰሰውና ለግማሽ ክፍለ ዘመን ወይም ለ50 ዓመታት በጽናት የቆየው ኢትዮጵያ 13 የፀሐይ ወራት ያሏት ሀገር የሚለው የሀገራችን የቱሪዝም ዘርፍ ዋነኛ መለያና የክብር ዓርማ ሆኖ የቱሪዝም ሀብቷን ለዓለም ስታስተዋውቅበት ቆይታለች። ምንም እንኳን በ2009 ዓ.ም ምድረ ቀደምት (Land of Origins) በሚለው አዲስ የቱሪዝም ብራንድ ቢተካም የቀደመው በዓለም አቀፍ ደረጃ በቱሪስቶች አዕምሮ ውስጥ በጥልቀት የተቀረጸ በመሆኑ ሁለቱን አጣምሮ መስራት እንደሚገባ የቱሪዝም መምህርና ተመራማሪ አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) ያክላሉ።

## አዲስ አበባ አመራር አካዳሚ
## ADDISABABALEADERSHIP ACADEMY
## የተባባሪ አካላት ጥሪ ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ በከተማ አስተዳደሩ ለሚገኙ ለመንግስትና ለግል ተቋማት ስልጠና በመስጠት፣ ጥናትና ምርምር በማካሄድ፣ የማማከርና ማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት የአመራሩን፣ የባለሙያውን እና የተቋማትን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ለማጎልበት አስፈጻሚ አካላትን መልሶ ማደረጀት አዋጅ ቁጥር 84/2016 የተቋቋመ መንግስታዊ ተቋም ነው፡፡ አካዳሚው የተሠጠውን ተልዕኮ እውን ለማድረግ ካሉት የውስጥ አሰልጣኞች፣ ተመራማሪዎች እና አማካሪዎች በተጨማሪ ከሌሎች ተቋማት ልምድና ብቃት ያላቸውን አሰልጣኞችን፣ ተመራማሪዎችን አማካሪዎችን አወዳድሮ የተባባሪ አሰልጣኞች፣ ተመራማሪዎችና አማካሪዎች ፑል ፈጥሮ በትብብር መስራት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በመስራት፣ የማማከር አገልግሎቶችን በመስጠት እንዲሁም ስልጠና በማሰልጠን ልምዱና ብቃቱ ያላችሁ እና ከዚህ በታች የተገለጸውን መስፈርት የምታሟሉ ተባባሪ አካላት ከዚህ በታች በተጠቀሱት የትብብር መስኮች እንድታመለክቱ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** ከዚህ በፊት በአካዳሚው ተባባሪ የነበራችሁ በወጣው ማስታወቂያ መሰረት ማመልከት ይኖርባቸዋል፡፡

የተጠየቁትን ማስረጃዎች አሟልቶ ያላቀረበ አመልካች ከውድድር ውጪ የሚደረግ ይሆናል፡፡

**ለበለጠ መረጃ: +251-11-667-22-98/ +251-11-667-34-73/ ይደውሉ**

**CV ብቻ መላክ ተቀባይነት አይኖረውም**

| የትብብር መስክ | ተፈላጊ ችሎታ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የትምህርት አይነትና ደረጃ | የስራ ልምድ በዓመት | ከስራ አመራርነት ጋር አግባብነት/ተዛማጅነት ያላቸው ስልጠናዎች: የወሰዷቸው ስልጠናዎች ብዛት | ከስራ አመራርነት ጋር አግባብነት/ተዛማጅነት ያላቸው ስልጠናዎች: የሰጧቸው ስልጠናዎች ብዛት | ዕውቅና ካለው ተቋም የተሰጠ የሙያ ብቃት ማስረጃ |
| ዋና አሰልጣኝ | በሊደርሺፕ፣ በማኔጅመንት፣ በአካዉንትንግ (Peachtree Accounting, PEARLS, IFRS certificate ያለዉ/ላት) በሰው ኃብት ስራ አመራር፣ ኢኮኖሚክስ፣ አካዉንትንግ፣ አመራርና መልካም አስተዳደር፣ የትምህርት ዕቅድና አመራር፣ ዴቨሎፐመንት ስተዲስ፣ በህዝብ አስተዳደር፣ ፐብሊክ ፖሊሲ ስተዲስ፣ ፐብሊክ ማኔጅመንት፣ በቢዝነስ አድምንስትሬሽን፣ በዲቨሎፐመንት ኢኮኖሚክስ፣ የከተማ ስራ አመራር፣ ፖለቲካል ሳይንስና አለምአቀፍ ግንኙነት፣ ፌደራሊዝምና ህገ መንግስት፣ ሳይኮሎጂ፣ ፕሮጀክት ፕላኒንግ እና ማኔጅመንት፣ ጀንደር ስተዲስ፣ በተቋማዊ ሊደርሺፕ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ስትራቴጂክ ስተዲስ፣ ኮምፓራቲቭ ፖለቲክስ፣ ፖለቲካል ኢኮኖሚ፣ ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ በኮሚኒኬሽንና፣ ሰላምና ደህንነት፣ ኢንቫይሮንመንት ኤንድ ዴቨለፐመንት ስተዲስ፣ በከተማ ልማትና አስተዳደር፣ ህግ፣ በሶሲዮሎጂ፣ ከተማ ፕላኒንግና ልማት፣ ግሎባል ስተዲስ፣ ዲፕሎማሲ፣ ስርአተ-ትምህርት ተመሳሳይ፣ በኮሚፒዉተር ሳይንስ 3ኛ ዲግሪ ያለው/ላት | 10 ዓመት በላይ በአሰልጣኝነት ወይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በአማካሪነት/በአመራርነት/በመምህርነት/ በተመራማሪነት የሰራ/ች ሆኖ ከተጠየቀው የስራ ልምድ ዓመት በላይ የሚቀረብ ተጨማሪ ዓመት ተጨማሪ ነጥብ የሚያሰጥ ይሆናል | የአሰልጣኞች ስልጠና (TOT) ያለው/ላትና 3 እና በላይ ከስራ አመራርነት ጋር አግባብነት/ ተዛማጅነት ያላቸው ስልጠናዎችን የወሰዱ ሆኖ ከተጠየቀው በላይ ለወሰዷቸው ተጨማሪ ስልጠናዎች ተጨማሪ ነጥብ የሚያሰጥ ይሆናል | 3 እና በላይ ከስራ አመራር ጋር አግባብነት/ ተዛማጅነት ያላቸው ስልጠናዎች የሰጡ ሆኖ ከተጠየቀው በላይ ለሰጧቸው ተጨማሪ ስልጠናዎች ተጨማሪ ነጥብ የሚያሰጥ ይሆናል | ዕውቅና ካለው ተቋም የተገኘ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ሰርተፊኬት ያለው |

**ማሳሰቢያ፡-**

1. **የስራ ልምድ፡-** አመልካቾች የሚያቀርቡት የስራ ልምድ ማስረጃ የሰሩባቸውን የስራ መደቦች መጠሪያ ስም፣ ከመቼ እስከ መቼ እንዳገለገሉ የሚገልጽ፣ ወቅታዊ የሆነ በአንድ የተጠቃለለ የስራ ልምድ ማስረጃ እና CV ሊያቀርቡ ይገባል፣
2. **የተሰጡ ስልጠናዎች፡-** አመልካቾች በተለያዩ ጊዜያት የሰጧቸውን ስልጠናዎች ዝርዝር የሚያሳይ በሚመለከተው አካል የተፈረመ ህጋዊ የሆኑ ማስረጃዎች ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ (እባክዎን የሰጧቸውን ስልጠናዎች ዝርዝር ሁሉንም ያቀርቡ)
3. **የወሰዷቸው ስልጠናዎች፡-** አመልካቾች በተለያዩ ጊዜያት ለወሰዷቸው ስልጠናዎች የተሰጡ ምስክር ወረቀቶች ወይም በሚመለከተው አካል የተረጋገጡ ሌሎች ህጋዊ ማስረጃዎች ሊቀርቡ ይገባል፡፡ (እባክዎን የወሰዷቸውን ስልጠናዎች ርዕስ ዝርዝር/የምስክር ወረቀቶች/ ሁሉንም ያቀርቡ)
4. **የአሰልጣኞች ስልጠና፡-** አመልካቾች የአሰልጣኞች ስልጠና ስለመውሰዳቸው ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
5. አመልካቾች የተጠየቁ ሁሉንም ማስረጃዎች በአንድ ፒዲኤፍ ተጠቃሎ መቅርብ ይኖርበታል፡፡
6. ከላይ ከተገለጸው አግባብ ውጪ የሚቀርብ፣ የማይነበብና ያልተሟሉ ማስረጃዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም ፡፡

| የትብብር መስክ | ተፈላጊ ችሎታ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የትምህርት አይነትና ደረጃ | የስራ ልምድ በዓመት | ከስራ አመራርነት ጋር አግባብነት/ተዛማጅነት ያላቸው የጥናትና ምርምር ጆርናል እና ሌሎች የጥናት ህትመቶች ብዛት | የጥናትና ምርምር የተሳትፎ ማረጋገጫ |
| መሪ ተመራማሪ እና ዋና አማካሪ | በሊደርሺፕ፣ በስራ አመራር፣ በኢኮኖሚክስ፣ በትምህርት ጥናትና ምርምር፣ ፐብሊክ ፖሊሲ ጥናት፣ ቢዝነስ አድሚንስትሬሽን፣ ህዝብ አስተዳደር/ማኔጅመንት፣ አመራርና መልካም አስተዳደር፣ የትምህርት እቅድና ስራ አመራር፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ በዲቨሎፐመንት ስተዲስ/ስራ አመራር፣ ጀንደር ስተዲስ፣ በስታቲሲቲክስ፣ በሶሲዮሎጂ፣ ሰላምና ደህንነት፣ በተቋማዊ ሊደርሺፕ፣ የልማት አስተዳደር፣ ፌደራሊዝምና ህገ መንግስት ጥናት፣ ግሎባል ስተዲስ፣ ስርዓተ-ትምህርት፣ አስተዳደርና ልማት፣ ዲፕሎማሲ፣ በዴቨሎፐመንት ኢኮኖሚክስ፣ ፕሮጀክት ማኔጅመንት፣ ዲቨሎፐመንት ማኔጅመንት፣ ኧርባን ማኔጅመንት፣ ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ ኢንቫይሮንመንት ኤንድ ዴቨለፐመንት ስተዲስ፣ አርባን አግሪካልቸር እና በተመሳሳይ የትምህርት መስክ 3ኛ ዲግሪ ያለው/ላት | 10 ዓመት በላይ በጥናትና ምርምር፣ የማማከር፣ እና የማህበረሰብ አገልግሎቶች ሆኖ ከተጠየቀው የስራ ልምድ ዓመት በላይ የሚቀረብ ተጨማሪ ዓመት ተጨማሪ ነጥብ የሚያሰጥ ይሆናል | 1 እና በላይ ከስራ አመራርነት ጋር አግባብነት/ ተዛማጅነት ያላቸው የጥናትና ምርምር ጆርናል/ወይም ሌሎች የጥናት ህትመት፣ የማማከር ፕሮጀክቶች/ ስራዎች / ያለው/ያላት/ ሆኖ ከተጠየቀው በላይ ለሚቀርቡ ተጨማሪ የጥናት ህትመቶች/ ጆርናሎች ተጨማሪ ነጥብ የሚያሰጥ ይሆናል | ለሚቀርቡ የጥናትና ምርምር እና የማማከር ስራዎች ጥናቱን/ የማማከር አገልግሎቱ ስለመስራታቸው/ በጥናቱ፣ በማማከሩ ስለመሳታፋቸው ማስረጃ ያላቸውና ማቅረብ የሚችሉ፣ ለማማከር ዕውቅና ካለው ተቋም የተገኘ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ሰርተፊኬት ያለው |

**ማሳሰቢያ. ፡-**

1. **የስራ ልምድ፡-** አመልካቾች የሚያቀርቡት የስራ ልምድ ማስረጃ የሰሩባቸውን የስራ መደቦች መጠሪያ ስም፣ ከመቼ እስከ መቼ እንዳገለገሉ የሚገልጽ፣ ወቅታዊ የሆኑ በአንድ የተጠቃለለ የስራ ልምድ ማስረጃ እና CV ሊያቀርቡ ይገባል፣
2. **ከስራ አመራር ጋር አግባብነት ወይም ተዛማጅነት ያላቸው የጥናትና ምርምር ጆርናል፡-** አመልካቾች በተለያዩ ጊዜያት በጆርናል ላይ ላሳተሟቸው የጥናት ውጤቶች የጥናት ርዕስ፣ ጆርናል ስምና ሊንክ በሲቪያቸው ላይ በግልጽ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፣
3. **ከስራ አመራር ጋር አግባብነት ወይም ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች የጥናት ህትመቶች፡-** አመልካቾች በተለያዩ ጊዜያት ለሰሯቸው/ ለተሳተፉባቸው የጥናት ስራዎች ከሚመለከተው አካል የሰሩትን ወይም የተሳተፉበትን የጥናት ርዕስ ዝርዝር የሚገልጽ ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ (ለእያንዳንዱ የጥናትና ምርምር ስራዎች ከአሰሪው አካል ወይም ከሚመለከተው ማስረጃ ይቀርብበታል)
4. **የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፡-** አመልካቾች ህጋዊ ከሆነ ተቋም የተሰጠ የሙያ ብቃት ሰርተፊኬት ካላቸው ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
5. መስፈርቱን የምታሟሉ አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣ በኋላ ከ25/12/2018 ዓ.ም ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት በአካዳሚው E- Mail: leadership@aala.edu.et ማመልከት አለባችሁ ፡፡ Please, use “Associate Researcher “, “Associate Trainer “, Associate Consultant, or “Associate Researcher, Trainer, and Consultant” as the subject line of your e-mail.
6. አመልካቾችን በአካል የማንቀበል መሆኑን እናሳስባለን፡፡
7. አመልካቾች የተጠየቁ ሁሉንም ማስረጃዎችን በአንድ ፒዲኤፍ ተጠቃሎ መቅርብ ይኖርበታል፡፡

7\. ከላይ ከተገለጸው አግባብ ውጪ የሚቀርብ፣ የማይነበብና ያልተሟሉ ማስረጃዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡

**የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ**

## ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

የልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ግልፅ ጨረታ አውጥቶ ከዚህ በታች ያሉትን እቃዎችን መግዛት ይፈልጋል፡፡

ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዢያ በባንክ የተረጋገጠ cpo በየሎቱ

1 ሎት1 አላቂ የቢሮ እቃዎች ............................................ 9000 (ዘጠኝ ሺ ብር)
2 ሎት2 የጽዳት፣ የደንብ ልብስና የስፖርት ትጥቅ ዕቃዎች........... 8000 (ስምንት ሺህ ብር)
3 ሎት3 ቋሚ ዕቃዎች ................................................... 8000 (ስምንት ሺ ብር)
4 ሎት4 የኤሌትሮኒክስ ዕቃዎች ........................................ 8000 (ስምንት ሺህ ብር)
5 ሎት5 የጥገና ሥራዎች ................................................ 3000 (ሶስት ሺህ ብር)
6 ሎት6 የመኪና እና የሞተር ጎማዎች ................................. 5000 (አምስት ሺህ ብር)
7 ሎት7 መስተንግዶ ግዥ ................................................ 3000 (ሶስት ሺህ ብር)
8 ሎት8 አዳራሽ ዲኮር የወንበር ዲኮር ................................ 3000 (ሶስት ሺህ ብር)
9 ሎት9 የህትመት ስራዎች ............................................. 3000 (ሶስት ሺ ብር)
10 ሎት10 የትራንስፖርት /መጓጓዣ/ ................................... 500 (አምስት መቶ ብር)
11. ሎት 11 ዘር /አዝዕርት/ .................................................. 1000 (አንድ ሺህ ብር)

ብቃት ያላቸዉንና በመስኩ የተሰማሩ ተጫራቾችን አወዳደሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል በዚህ መሰረት

1.በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላችሁ የዘመኑን ግብር የከፈሉ በመንግስት ግ/ን/አስ/ኤጀንሲ ድህረ ገፅ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር ላይ የተመዘገቡ፤ ቲን እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ከጨረታ ሰነዶች ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው
3. ተጫራቾች ጨረታው በአድስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት እለት አንስቶ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 200 /ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል በቀድሞው ን/ስ/ላ/ክ/ ከተማ ወረዳ 04 አስተዳደር በአሁኑ በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ፋይናንስ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 501 በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በታሸገ ኢንቨሎፕ ማስታወቂያ ከወጣበት እለት ጀምሮ ለተከታታይ 10 የስራ ቀናት በፋይናንስ ቢሮ ቁጥር 501 ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በአስራ አንደኛ ቀን በ 4:00 ሰዓት ታሽጎ በእለቱ ከቀኑ 4:30 ሰዓት በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ፋይናንስ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 501 ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀን ቅዳሜና እሁድ ወይም የበአል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ታሽጎ ይከፈታል፡፡
6.ተጫራቾች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ሎት 1፣ ሎት 2 እና ሎት 7 ናሙና ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን ለሎት 3፣ ለሎት 4 እና ለሎት 5 በቀረበው እስፔስፐኬሽን መሰረት የተሟላ እስፔስፐኬሽን ማዘጋጀት እና ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን እቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
8. የዘገየ ጨረታ እና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፡፡
9. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
10. የጨረታ አሸናፊ እንደሆኑ ከተለየ ቦሃላ አሸናፊዎች ያሸነፉበትን ጠቅላላ ዋጋ 10 ፐረሰንት ውል ማስከበሪያ በባንክ የተመሰከረ cpo ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

***<u>ለተጨማሪ ማብራሪያ ጥያቄ</u>***

**አድራሻ አዲስ አበባ በቀድሞው ን/ስ/ላ/ክ/ ከተማ ወረዳ 04 አስተዳደር በአሁኑ በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 አስተዳደር ከሳር ቤት ወረድ ብሎ ሀረር ክሊኒክ ፊት ለፊት 300 ሜትር ገባ ብሎ የመስሪያ ቤቱ ስልክ ቁጥር 0113834260**

**የልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት**

## <u>የጨረታ ማስታወቂያ</u>

በልደታ ክ/ከተማ ት/ት/ጽ/ቤት ካራማራ የመጀ/ደረጃ፣ ሌ/ኮ አብዲሳ አጋ እና ቀበሌ 37 ቅ/አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለ2019 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውል ከዚህ በታች በሎት በዝርዝር የተገለፁትን ዕቃዎች፣ ሎት1 የፅህፈት መሳሪያዎች፣ ሎት2 የፅዳት ዕቃዎች፣ ሎት3 የደንብ ልብስ፣ ሎት4 አላቂና ቋሚ የት/ት መርጃ ዕቃዎች፣ ሎት5 የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣ ሎት6 የተለያዩ የቢሮ ፈርኒቸር መገልገያ ዕቃዎች፣ ሎት7 የተለያዩ የህትመት ስራዎች ሎት8 የመስተንግዶ ውሃ እና ቆሎ በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

1. የንግድ ምዝገባ ሰርተፍኬት
2. በዘርፉ የተሰማሩበት የታደሰ የንግድ ፍቃድ
3. በአቅራቢነት ዝርዝር የተመዘገቡበት ሰርተፍኬት
4. የቫት ተመዝጋቢ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሰርተፍኬት እና የዘመኑ ግብር የከፈላችሁበት ሰነድ ማቅረብ የምትችሉ ማንኛውም ተጫራቾች በጨረታው መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እያሳወቅን እንዲሁም በዋጋ መሙያው ላይ ሳፐል እንዲቀርብባቸው የተገለፁትን ዕቃዎች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ናሙና ማቅረብ ያለባችሁ ሲሆን በሎት6 የተገለፀውን ዕቃ በማምረቻ ወይም በመሸጫ ቦታችው ማሳየት ያለባችው መሆኑን እያሳውቅን ለዚሁ ጨረታው ማስከበርያ የሚሆን ለሎት1.12000.00 /አስራ ሁለት ሺ ብር/፣ ሎት2.10000.00 /አስር ሺ ብር/፣ ሎት3.10000.00 /አስር ሺ ብር/፣ ሎት4.10000.00 /አስር ሺ ብር/፣ ሎት5.15000.00 /አስራ አምስት ሺ ብር/፣ ሎት6.10000.00 /አስር ሺ ብር/ ሎት7. 3000.00/ ሶስት ሺ ብር/ ሎት8. 2000.00 /ሁለት ሺ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ በማስያዝ ከላይ የተዘረዘሩትን ሰነዶች ዋናውን እና ፎቶ ኮፒውን በሁለት ፖስታ በሰም በማሸግ ማቅረብ የምትችሉ ተጫራቾች ት/ቤቱ ያዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ በማይመለስ 300.00 /ሶስት መቶ ብር/ በመግዛት ት/ቤቱ ለዚህ ጨረታ ባዘጋጀው የዋጋ መሙያ ሰነድ ላይ ዋጋችሁን በመሙላት ለጨረታ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ሰነዳችሁን በማስገባት መወዳዳር የምትችሉ መሆኑን እየገለፅን ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ እና የጨረታ ሰነድ በደብዳቤ የምናስተናገድው አምርታችሁ ለገበያ በምታቀርቡት ምርት ላይ ብቻ ነው፡፡ ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ አስር የስራ ቀናት አየር ላይ የሚቆይ ሲሆን በ10ኛው ቀን 11፡00 ሰዓት /አስራ አንድ ሰዓት/ ተዘግቶ በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ በተጠቀሰው ሰዓት ጨረታው ሲከፈት የማይገኙ ተጫራቾች ጨረታው በሌሉበት እንደሚከፈት እያሳወቅን የመክፈቻው ቀን ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም የበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተጠቀሰው ሰዓት ይከፈታል፡፡

**ማሳሰቢያ፡- ት/ቤቱ ለጨረታው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡**

**- የምታቀርቡት ናሙና (ሳምፐል ) ላይ የድርጅታችሁን አርማ ማሃተም ማድረግ አይቻልም!!**

**አድራሻ፡- በልደታ ክ/ከ/ወ/03 ካራማራ የመጀ/ደ/ት/ቤት አብነት አደባባይ ጆስሀንስን አጠገብ ስልክ ቁጥር 0112-73-23-45**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 03 ካራ ማራ የመጀ/ደረጃ፣ ሌ/ኮ አብዲሳ አጋ ቅድመ አንደኛ እና ቀበሌ 37 ቅ/አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**

# በስፖርት ማዕከላት የደመቀች መዲና

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የአንዲት ዘመናዊ ከተማ ህይወት የሚዘራው በሰፋፊ መንገዶቿና በረጃጅም ህንጻዎቿ ብቻ ሳይሆን፣ በስፖርት ዘርፉም ጭምር ነው። ይህንን በተገቢው የተረዳችው አዲስ አበባም የስፖርቱ ዘርፍ እንደ አንድ የመዝናኛ ዘርፍ ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ከተማ ግንባታና የወጣቶች ስብዕና መቅረጫ ቁልፍ መሣሪያ ተደርጎ ተወስዷል። በአዲስ አበባ የታዩት የመጫወቻ ሜዳና የማዘውተሪያ ስፍራዎች ግንባታ ለዚህ ትልቅ ማሳያ ናቸው። ከታላላቅ ስታዲየሞች ባለፈ፣ በየአካባቢው የተገነቡትና ዘመናዊ ሰው ሰራሽ ሳር የተነጠፈባቸው ሜዳዎች፣ ስፖርቱ በሰፈር ደረጃ እንዲያንሰራራና ተተኪ ስፖርተኞችን ለማፍራት ምቹ ሁኔታን ፈጥረዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ለስፖርቱ ዘርፍ የሰጠው ልዩ ትኩረትና የተከናወኑ ሁለተናዊ ልማቶች መዲናዋን ለትልልቅ ስፖርታዊ ውድድሮች ምቹ መዳረሻ አድርጓታል። የወጣቶችና አዳጊዎችን ሁለንተናዊ እድገት ታሳቢ ያደረጉ የመዲናዋ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የወጣቶችን ጤንነት ከመጠበቅ ባለፈ ተተኪ ስፖርተኞች ራሳቸውን እንዲያሳዩ እድል እየፈጠሩ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አሰግደው ኃይለጊዮርጊስ እንደሚገልጹት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የኅብረተሰቡን የስፖርት ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተገነቡ ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል እና የስፖርት ዓይነቶች ያካተቱ መሆናቸው ቀደም ሲል ከነበሩት የተለዩ ያደርጋቸዋል ብለዋል።

ቀደም ሲል በመዲናዋ የነበሩት የስፖርት ማዘውተሪያዎች በቁጥር አነስተኛና ደረጃቸውን ያልጠበቁ በመሆናቸው ዘርፉ በተገቢው መንገድ እንዳያድግ ትልቅ ማነቆ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህን ችግር በመገንዘብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶች ሁለንተናዊ እድገትን ታሳቢ በማድረግ ዘመናዊ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን ገንብቷል፡፡ እነዚህ የስፖርት ማዘውተሪያዎች ወጣቶች ከጎጂ ድርጊቶች እንዲርቁ፣ በአካልና በአእምሮ እንዲዳብሩ እንዲሁም ተተኪ ስፖርተኞች ራሳቸውን እንዲያሳዩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ።

በተለያዩ ክፍለ ከተሞች የተገነቡ የስፖርት ማዘውተሪያዎች የጤና ቡድኖችን የእግር ኳስ ውድድር ጨምሮ የተለያዩ የስፖርት ውድድሮችን በማስተናገድ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም የስፖርት ማዘውተሪያዎች የወጣቶችን ጤንነት ከመጠበቅ ባለፈ ማህበራዊ ትስስር እንዲጎለብት ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ነው፡፡ የስፖርት ቱሪዝምን ለማሳደግ እና ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን እንድታስተናግድ ለማድረግ የስፖርት ማዘውተሪያዎቹ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ስለመሆኑም አቶ አሰግደው ኃይለጊዮርጊስ ያስረዳሉ፡፡



ግራፊክስ - በእዮብ ተፈራ

በቅርቡ በአዲስ አበባ ከተማ ተገንብተው ወደ አገልግሎት ከገቡ ስፖርታዊ ማዘውተሪያ ስፍራዎች ጥቂቶቹ

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ከመሳተፍና ድል ከመቀዳጀት ባሻገር፣ ትልልቅ መድረኮችን በራሷ ሀገር ማዘጋጀት ጀምራለች። ለምሳሌም 5ኛው የአፍሪካ ወጣቶች ኦሎምፒክ እና የባህል ስፖርት ፌስቲቫል፣ የአዲስ አበባ ግራንድ ፕሪ፣ የዓለም አትሌቲክስ ኮንቲኔንታል ቱር የወርቅ ደረጃ ውድድር፣ የ2027 የዓለም አቀፍ የስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር (AIPS) ጉባኤ፣ እነዚህንና የመሳሰሉትን መድረኮችን አስተናግዳለች፡፡ እንዲሁም የአፍሪካ ዋንጫ እግር ኳስን ለማዘጋጀት የሚያስችላትን የጨረታ ሰነድ ለአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (CAF) አስገብታለች። እነዚህን ዝግጅቶች በብቃት ለማስተናገድ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ስታዲየሞች እየተገነቡ ይገኛሉ።

እንደነዚህ ያሉ ታላላቅ ውድድሮች በሀገራችን መካሄዳቸው በርካታ እንግዶችን በመሳብ ለሀገሪቱ የሚሰጡት ጠቀሜታ ቀላል አይደለም። የውጭ ሀገር ዜጎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ የቱሪዝም ዘርፉን ያነቃቃል፤ የውጭ ምንዛሬ ገቢንም ያሳድጋል፤ ይህም ለኢኮኖሚውና ኢንቨስትመንት መነቃቃት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል። የተለያዩ ሀገራት ዜጎች የኢትዮጵያን እውነተኛ ገጽታ፣ እንግዳ ተቀባይነትና ባህል በቅርበት እንዲረዱ በማድረግም ለሀገሪቱ ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት ይጨምራል። ለሀገር ውስጥ ወጣቶች የመዝናኛ እድል ከመፍጠሩ ባሻገር፣ በማህበረሰቡ ውስጥ አዲስ መነቃቃትንና አንድነትን ይፈጥራል።

ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹ ለማድረግ በሚሰራቸው ሰፊ የኮሪደር ልማቶችና የከተማ ማደስ ስራዎች ትልልቅ ታሪካዊና ዘመናዊ ፕሮጀክቶችን ሲገነባ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን አብሮ አካቶ መገንባቱ ለወጣቶች ትልቅ ዕድል ፈጥሯል። ይህ ስራ ሀገራዊ ስፖርቱን ከማሳደግ ባለፈ ከዚህ ቀደም ያልተለመዱና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተወዳጅነት ያላቸውን እንደ ድብልቅ ማርሻል አርት (MMA) ያሉ ስፖርቶችና ስፖርተኞች ወደ መዲናዋ አዲስ አበባ እንዲመጡ በማድረግ ረገድ ታላቅ መሠረት ጥሏል። ሰሞኑን በዓድዋ ድል መታሰቢያ አዳራሽ የተካሄደውን “ዓድዋ ፋይት ናይት” (Adwa Fight Night) የድብልቅ ማርሻል አርት (MMA)፣ የቦክስና የሞይታይ ውድድርን እዚህ ጋር መጥቀስ ይቻላል፡፡

እንደ “ዓድዋ ፋይት ናይት” ያሉ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት መድረኮች ስፖርቱ ከሀገር ውስጥ አልፎ ዓለም አቀፍ ከፍታ ላይ እንዲደርስ አቅም ፈጥረዋል። ዓለም አቀፍ ስፖርታዊ ዝግጅቶችን በመዲናዋ ማስተናገድ ወጣቶች በስፖርቱ ያላቸውን ተሳትፎ ከማሳደጉም በላይ የከተማዋን ስፖርታዊ ቱሪዝም የሚያነቃቁና ለወጣቶች አዳዲስ የስራ ዕድሎችን የሚፈጥሩ ናቸው። ከንቲባ አዳነች አቤቤም በመዲናዋ ዘመናዊ የስፖርት መሰረተ-ልማቶች በመገንባታቸው አዳዲስ የስፖርት አይነቶች እንዲካሄዱ አስችሏል ያሉትም ለዚህ ነው፡፡ ወጣቶች ልዩ ተሰጥኦና ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት፣ ለስፖርት ቱሪዝም፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መስተጋብር የሚጠናከርበት፣ የከተማችንን ገፅታ የሚቀይር እና ተወዳዳሪነታችን የሚጨምር ነው ይላሉ ከንቲባዋ።

ከአረንጓዴው ስፍራ በተጨማሪ ዘመናዊ የስፖርት ማዘውተሪያ፣ ጂምናዚየም እና 7 አዳራሾችን ያካተተው የአራዳ ፓርክ በውስጡ የያዘው ስፖርት አሬናም ለወጣቶች የጤናማ ትውልድ መፍለቂያ አውድማዎች እንዲሆን ታስቦ የተገነባ ነው። እየተገባደደ ባለው ዓመት ተመርቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረው አራዳ ፓርክ ውስጥ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው ‘የስፖርት አሬና’፣ 5 ኪሎ ሜትር የመሮጫ፣ 5 ኪሎ ሜትር የብስክሌት መጋለቢያ፣ እንዲሁም 6 ኪሎ ሜትር የእግረኛ መንገዶችን የያዘ ነው። እነዚህ መሰረተ ልማቶች የማኅበረሰቡን የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ባህል ከማሳደግ አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸውም ተጠቁሟል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ መረጃ እንደሚያመላክተው በከተማዋ በርካታ የስፖርት ማዘውተሪያ ሜዳዎች ተሰርተዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ የሆነው 24 ስፖርት ሜዳ በቅርቡ ከተደረገለት የማሻሻያ ግንባታ በኋላ ለአካባቢው አዳጊዎች ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። ከዚህ ቀደም ሜዳው በክረምት ወራት ጭቃ እየሆነና ውሃ እየተኛበት ለመጫወት ቀርቶ ለመራመድ እንኳን የማያመች፣ በበጋ ወቅት ደግሞ አቧራማ ስለሚሆን ለስልጠናና ለእንቅስቃሴ አስቸጋሪ እንደነበር ተጫዋቾችና አሰልጣኞች ያስታውሳሉ። ቀደም ሲል የነበረውን አስቸጋሪ ሁኔታ ያስታወሰው አዳጊ ሙሳብ ሰይፉ ድሮ ሲጫወቱ በበጋ አፈሩ አቧራ እየፈጠረ፣ በክረምት ዝናብ ሲዘንብ ጭቃ ይሆን እንደነበረ በማስታወስ፣ አሁን ግን አርቴፊሻል ስለሆነ ሜዳው ይመቻል ሲል ገልጿል፡፡

የ24 ስፖርት ሜዳ አሁን ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል። ሜዳው በዘመናዊ የሰው ሰራሽ ሳር ተሸፍኖ፣ በጥሩ ሁኔታ ታጥሮና ለስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ምቹ ሆኖ በመሰራቱ ለአካባቢው አዳጊዎችና ወጣቶች ደስታን ፈጥሯል። አሰልጣኝ ወልደአማኑኤል ጸጋዬ፣ አዲሱ አርቴፊሻል ሜዳ አዳጊዎች ኳስን በጥሩ ሁኔታ እንዲቆጣጠሩ፣ ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉና ሙሉ አቅማቸውን እንዲያወጡ ከመርዳቱም በላይ፣ ወላጆችም ልጆቻቸውን በሙሉ እምነት ወደ እግር ኳስ ስልጠና እንዲልኩ ትልቅ መነቃቃትን ፈጥሯል ብለዋል።

በመዲናዋ የፒኬ ኤስ ስፖርት ቡድን አሰልጣኝ ያፌት ስንታየሁ በበኩሉ፣ ከዚህ ቀደም ልምምድ የሚያደርጉበት ሜዳ ጭቃና አቧራ የነበረና ለበሽታ እንደሚያጋልጥ በማንሳት፣ አሁን ግን በተሻለ መልኩ በመሰራቱ ለጤናም ሆነ ለትምህርታቸው እንደሚጠቅም ይገልፃል፡፡ ከዚህ ቀደም አቧራማና ለጤና አስጊ በነበሩ ሜዳዎች ላይ ይለማመዱ የነበሩ አዳጊዎች አሁን ላይ በተስተካከለ ስፍራ ስፖርት በመስራታቸው ደስተኞች መሆናቸውን ገልጿዋል።